233
233
233

የጠጠረኛው ጠጠረኛ



87/2002

ቁጥሩን መሆንን ይፈልጋሉ?

233

የመጨረሻው መጨረሻ

ከኢሳይያስ ፀጋዬ


አዲስ አበባ
1991 ዓ.ም.



የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

የመጀመሪያ እትም 1991 /1998/



233

ማውጫ

መግቢያ 5

1. ባቢሎን 8

2. እስራኤል 38

3. ትንሣኤና ንጥቀት 53

4. ተቃዋሚው ክርስቶስ 72

5. አሥራዊው 107

6. የመጨረሻው መጨረሻ 114

ምስጋና

- ይህን መጽሐፍ ስጽፍ ከጎኔ በመሆን ላበረታችኝና በሚያስፈልገኝ ሁሉ ለደገፈችኝ ለባለቤቴ ለትዕግሥት ተሰማ፥
- ይህ ሥራ የተሟላ እንዲሆን ጊዜውን በመስጠትና የሚያስፈልገኝን ነገር ሁሉ በማድረግ ለረዳኝ ለወንድም አስቻለው ደበበ፥
- ጽሑፉን በማረም ለረዳኝ ለወንድም ግርማዊ፥ እንዲሁም በጸሎትና በሌሎችም ተግባራት ከጎኔ ለተሰለፉት ሁሉ፥
- ከሁሉም በላይ ደግሞ ለዚህ መጽሐፍ መጻፍ ሙሉ ለሙሉ ለረዳኝ ለጌታ እግዚአብሔር ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ።

ደራሲው

233

መግቢያ

ዘመናችንን ስናስብ ሁለት ያገጠጡ እውነታዎች ማስተዋለ እይታችንን ይሞሉታል፤ በአንድ በኩል ወንጌሉ ወደ ዓለም ሁሉ እየሮጠ የእግዚአብሔር ሥራ ሲከወን፥ በአንጻሩ ደግሞ ሰይጣን ዓለማችንን በክፉት ሥራዎች አስሮ ይነዳታል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ሊያርግ ሲል ሐዋርያት፥ «የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱ ምንድነው?» ሲሉ ጠይቀውት ነበር። ጌታችን ከርሱ መመለስ በፊት እንደሚከሰቱ የተናገራቸው ምልክቶች እስካሁን በመፈጸም ላይ ናቸው። የመሬት መንቀጥቀጥ፥ የውኃ ሙላት፥ ዐውሎ ነፋስና የመሳሰሉት አደጋዎች ተፈጥሮን በቁጥጥራቸው ሥር እንደሚያውሉት ወይም እንዳዋሉት የሚያውጁትን የምዕራቡን ዓለም አገሮች ጨምሮ ዓለማችንን እየናጧት ይገኛሉ።

ከጥቂት ዓመታት በፊት የአደጋና የጦርነት ዜና መስማት ያልተለመደ አስደንጋጭ ክስተት እንደነበር ከታሪክ ገጾች ላይ መመልከት ይቻላል። ዛሬ ግን የዓለምን የመገንኛ ብዙሃን ያጨናነቁት የጥፋትና የእልቂት ዜናዎች ናቸው። የመቶዎች ሕይወት በተለያዩ አደጋዎች መርገፍ፥ ከመኖሪያ ሰፍራቸው በመፈናቀል ያለ ምግብና ልብስ መሠቃየት፥ ወዘተ. አሰልቺ ዜና እየሆነ መጥቷል።

የተፈጥሮና ሰው-ሠራሽ አደጋዎችና ችግሮች ያልዳሰሱት የዓለማችን ጓዳ አይገኝም። አንጻራዊ ሰላም እንዳላቸው በሚነገርባቸው ምዕራባውያን ዘንድ እንኳ ከፈርሃ-እግዚአብሔር-አልባነት የተነሣ የሚፈጸሙ ምግባረ-ብልሹነቶች ጆሮን የሚያሳክኩ እየሆኑ መጥተዋል። እነዚህም ሰብአዊ ክብርን እስከማዋረድ የሚደርሱ አሳፋሪ ተግባራት ናቸው።

የወንድ ከወንድ ጋር መጋባት፥ የሴት ከሴት ጋር ጎጆ መውጣት፥ የወንዶች ያታ መለወጥና ሌሎችም ቃለ እግዚአብሔር የሚያቅባቸው አስጸያፊ ኃጢአቶች በብዙ አገሮች እንደተለመደና ተገቢ ነገር እየተቆጠሩ ናቸው። እንዲያውም አንዳንድ መንግሥታት ለዚህ ዓይነቱ የክፉት ተግባር እውቅና በመስጠት ሲያበራቱት ይታያል። እንደ ቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን የሚቆጥሩ አንዳንድ ድርጅቶችም ለዚህ ዓይነቱ ድርጊት ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን፥ «ከሴት ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ፤ ጸያፍ ነገር ነውና» /ዘሌ. 18፡22/፤ «ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ ነገር አድርገዋል፤ ፈጽመው ይገደሉ፤ ደማቸው በላያቸው ነው» /ዘሌ. 20፡13/ ሲል ያወግዘዋል። ዛሬ ያታቸውን በመለወጥ ሴቶች በሆኑት አባቶች ምክንያት አባት ስለሌላቸው ባለ ሁለት እናት ልጆች መስማት የተለመደ ነገር ሆኗል። በብዙ ስፍራዎች የእግዚአብሔርን መኖር የሚክዱ ሰዎች በተለያየ አምልኮተ-ሰይጣን ውስጥ ሲሳተፉ ይታያሉ።

ከዚህ ሁሉ ባሻገር የመካከለኛውን ምሥራቅ ሁኔታ ስናጤን፥ ምንም እንኳ እስራኤል ከተቃዋሚዎቿ ጋር እየተስማማችና ከመሬቷም ለመቁረስ እየዳዳች ቢሆንም፥ በአገሪቱ ውስጥ እየታየ ያለው ውጥረትና አደጋ እየገሸበ ይገኛል።

እንግዲህ፥ እነዚህና ሌሎችም ያልጠቀስኋቸውና ዳሩ ግን ዓለማችንን እያሽከረከሩ የሚገኙ ሁኔታዎች ምንን ያመለክቱ ይሆን? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ ከተናገረውና በሌሎችም የነቢያት መጻሕፍት ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር ዘመናችንን እየተመለከትን በእግዚአብሔር መንፈስ ስንመረምር ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ወደ ፍጻሜውና ወደ ጌታችን ዳግም ምጽአት እየቀረብን መሆኑን እንረዳለን።

ስለ መጨረሻው ዘመን የዮሐንስ ራእይን ጨምሮ፥ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ አንዳንድ የእግዚአብሔር ሰዎች የተለያየ አመለካከት አላቸው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለተጠቀሱት አንዳንድ ክፍሎችም እንደዚሁ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ። ምንም እንኳ እነዚህ የአመለካከት ልዩነቶች ቢኖሩም፥ ከእግዚአብሔር ቃል የተረዳሁትንና ሌሎችን መጻሕፍት በማንበብ ትክክል እንደሆነ ያመንሁትን አሳብ «የመጨረሻው መጨረሻ» በሚል ርእስ በእግዚአብሔር ርዳታ አቅርቤአለሁ።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ እግዚአብሔርን የሚያውቁ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ያለንበትን ዘመን እየመረመሩ፥ የጊዜውን አጭርነት ተረድተው ከሚያዘናጉ ነገሮች ሁሉ በመንቃት በጥንቃቄ እንዲጓዙ ለማነቃቃትና ለማጽናት ነው። በአንጻሩ፥ እግዚአብሔርን ላላወቁት ደግሞ በመጽሐፉ ውስጥ ከተገለጹትና በእግዚአብሔርም ቃል ከሚደገፉት የዓለም ክስተቶች ግንዛቤ በመነሣት ወደ አምላካቸው እንዲመለሱና ጌታ የሰጣቸውን የንስሐ ዕድል እንዲጠቀሙበት ለመምከርና ለማስጠንቀቅ ነው። እየሆነው ያለው ሁሉ ምክንያት የሌለው ወይም በአጋጣሚ የሚከሰት እንዳልሆነ ተገንዝበው ፊታቸውን ወደ ሕያዋን ተስፋ እንዲያቀኑ ለማበረታታት እሻለሁ።

ኢ.ፀ.

1
ባቢሎን

«በፅዮን የምትቀመጥ፦ በእኔና በሥጋዬ የተደረገ ግፍ በባቢሎን ላይ ይሁን ትላለች፤ ኢየሩሳሌምም፦ ደሜ በከለዳውያን ምድር በሚኖሩት ላይ ይሁን ትላለች። ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ እምዋገትልሻለሁ፤ በቀልሽንም እበቀልልሻለሁ፤ ባሕርዋንም ደረቅ አደርገዋለሁ፤ ምንጭዋንም አደርቃለሁ። በባቢሎንም የድንጋይ ቁልልና የቀበሮ ማደሪያ መደነቂያም ማፍዋጫም ትሆናለች፤ የሚቀመጥባትም ሰው አይገኝም» /ኤር. 51፡35-37/።

ከጥፋት ውኃ ወዲህ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ የተሠራች ከተማ ባቢሎን ነች። እግዚአብሔር ከምድር ላይ እንዳስወገዳቸው እንደ ሰዶምና ገሞራ በኃጢአት ዕፅ የሰከረችና የኃጢአት ጽዋዋ በእግዚአብሔር ፊት የሞላባት ብቻ ሳትሆን፥ ከጥፋት ውኃ ወዲህ የሰው ልጆች ለመጀመሪያ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያመፁባት ከተማ ነች። ይህም ብቻ አይደለም። ለዓመፀኞች የስም ማስጠሪያ እንድትሆን የተገነባች የዓመፅ ከተማም ነች።

ይህችው ግፈኛ ከተማ ስለ ኃጢአቷ ከእግዚአብሔር ዘንድ የቅጣት ሽልግቶችን ማግበስበሷ በእግዚአብሔ ቃል ውስጥ ተጽፎአል። ይሁንና፥ ቅጣቶች ሊያስተምሯት ባለመቻላቸው አንዲያውኑ የምትወድምበትም ቀን ተቀጥሮላታል።

«የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሰፊው የባቢሎን ቅጥር ፈጽሞ ይፈርሳል፤ ረጃጅሞችም በሮቿ በእሳት ይቃጠላሉ፤ የወገኖችም ድካም ከንቱ ትሆናለች፤ የአሕዛብም ሥራ ለእሳት ትሆናለች፤ እነርሱም ይደክማሉ» /ኤር. 51:58/። «ኤርምያስም ሠራያን እንዲህ አለው፦ ወደ ባቢሎን በገባህ ጊዜ እይ፤ ይህንም ቃል ሁሉ አንብብና፦ አቤቱ፥ ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ ማንም እንዳይቀመጥባት ለዘላለም ባድማ እንድትሆን ታጠፋት ዘንድ በዚህች ስፍራ ላይ ተናግረሃል በል። ይህንንም መጽሐፍ ማንበብ ከፈጸምህ በኋላ ድንጋይን አሰርበት፤ በኤፍራጥስም ውስጥ ጣለው፤ አንተም፦ እኔ ከማመጣባት ክፉ ነገር የተነሣ እንዲሁ ባቢሎን ትሰጥማለች፤ አትነሣምም በል» /ኤር. 51:61–64/።

ባቢሎን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ብዙ ጊዜ በስም የተጠቀሰች ስትሆን፥ የተፈጸሙና ገና ያልተፈጸሙ ትንቢቶችን ጨምሮ በእግዚአብሔር ቃል ብዙ የተባለላት የአሕዛብ ከተማ ነች። ስለ ባቢሎን ስናጠና በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተገለጸ አንድ ዋንኛ ነገር እናገኛለን። ይኸውም በዚህ ስም የተጠሩ ሁለት ባቢሎኖች መኖራቸውን ነው።

ስለ ባቢሎን በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ አሥራ ሰባትና ምዕራፍ አሥራ ስምንት ተጽፎ እናገኛለን። በምዕራፍ አሥራ ሰባት ውስጥ ያለችው ምሥጢራዊቷ ባቢሎን በመባል ስትጠራ፥ የምዕራፍ አሥራ ስምንቷ ግን እንዲሁ ባቢሎን በመባል ተጠርታለች።

የሁለቱን ባቢሎኖች ተመሳሳይነትና ልዩነት ከዚህ እንደሚከተለው ከእግዚአብሔር ቃል እንመለከታለን።

ተመሳሳይነታቸው

1. ሁለቱም ታላቂቱ ባቢሎን ተብለዋል /ራእይ 17:5፤ 14:8፤ 18:2/።

2. ሁለቱም ከተማ ተብለዋል /ራእይ 17:18፤ 18:10–21/።

3. ሁለቱም በሐምራዊ ልብስ ተጎናጽፈው በወርቅ በከበሩ ድንጋዮችና በዕንቁ ተሸልመዋል /ራእይ 17:4፤ 18:16/።

4. ሁለቱም ሰዎችን በሚያስቱበት በዝሙትና በርኩሰት ተጠርተዋል /ራእይ 17:4፤ 18:3/።

5. ሁለቱም የኃጢአት ዋንጫን ይዘዋል /ራእይ 17:4፤ ኤር. 51:7፤ ራእይ 18:6/።

6. ሁለቱም ከምድረ አሕዛብና ነገሥታት ጋር ሴሰነዋል /ራእይ 17:2፤ 18:3-14/።

7. ሁለቱም የቅዱሳንን ደም አፍስሰዋል /ራእይ 17:16፤ 18:19/።

ልዩነቶቻቸው

1. አንደኛዋ ምሥጢራዊት ነች /ራእይ 17:7/።

- ሌላኛዋ ግን አይደለችም/ራእይ 16:19፤ 18:1-24/።

2. የአንደኛዋ ስም ምሥጢራዊ ተብሎ ተጽፎአል /ራእይ 17:5/።

- የሌላኛዋ ግን ምሥጢራዊ ሳይባል ታላቂቱ ባቢሎን በመባል ተገልጾአል /ራእይ 14:8/።

3. ምሥጢራዊቷ ባቢሎን ከዮሐንስ ራእይ በፊት በአንድም ነቢይ አልተጠቀሰችም።

- ሌላዋ ባቢሎን ግን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በብዙ ስፍራዎች ተጠቅሳለች።

4. ምሥጢራዊቷ ባቢሎን ለዮሐንስ አዲስ ሆናበታለች /ራእይ 17:1-7/።

- ሌላኛዋን ባቢሎን ግን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስለሚያውቃት አዲስ አልሆነችበትም።

5. መልአኩ ስለ ምሥጢራዊቷ ባቢሎን ምሥጢር ለዮሐንስ ሊነግረው ቃል ገብቶለታል/ራእይ 17:7/።

- ስለ ሌላዋ ባቢሎን ግን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በብዙ ስፍራዎች ስለተጻፈ ምሥጢራዊነት የላትምና ሊነግረው ቃል አልገባለትም።

6. ምሥጢራዊቷ በአውሬው ላይ ተቀምጣ ነበር /ራእይ 17:3-7/።

- ሴላዋ አልተቀመጠችም /ራእይ 18፡1-24/።

7. ምሥጢራዊቷ ሴትና ጋለሞታ ተብላ ተጠርታለች /ራእይ 17፡3፥ 5-6፥ 9፥ 15-18/።

- ሴላዋ አልተባለችም /ራእይ 18፡1-24/።

8. ምሥጢራዊቷ ለራሷ ብቻ ሀብታም ነች /ራእይ 17፡4/።

- ሴላዋ ሌሎችንም ሀብታም ታደርጋለች /ኤር. 51፡7፥ 13፥ 41፤ 18፡3፥ 9-19/።

9. ምሥጢራዊቷ በተቃዋሚው ክርስቶስና በአሥሩ ነገሥታት ትጠፋለች /ራእይ 17፡16/።

- ሴላኛዋን እግዚአብሔር በአንድ ሰዓት ውስጥ ያጠፋኦል /ራእይ 18፡10፥ 17፥ 19/።

ምሥጢራዊቷ ባቢሎን

«... የሰድብም ስሞች በሞሉባት ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ... በግምባርዋም ምሥጢር የሆነ ስም ታላቂቱ ባቢሎን የጋለሞቶችና የምድር ርኩሰት እናት ተብሎ ተጻፈ። ሴቲቱም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ አየኋት» /ራእይ 17፡3-6/።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ «ጋለሞታ» እና «ግልሙትና» የሚሉ ቃላት በተለያዩ ክፍሎች ተጠቅሰዋል።

«በግልሙትናዋ በመቅለልዋም ምድሪቱ ረከሰች፤ እርስዋም ከድንጋይና ከግንድ ጋር አመነዘረች»/ኤር. 3፡9፤ 3፡3፤ ሕዝ. 16፡16-22፥ 33-36፥ 39፥ 41/።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰውና በሴላም ስፍራ ስለ ጋለሞታና ግልሙትና ከሚናገረው የእግዚአብሔር ቃል እንደምንረዳው፥ «ጋለሞታ» በማለት የሚገልጸው ከአምላካቸው ርቀው ወደ ሌሎች አማልክት ፊታቸውን በማዞር የሚያመልኩትን ሕዝቦችና በሴትኛ አዳሪነት የሚኖሩትን አመንዝራዎች ነው።

«ይሁዳም ባያት ጊዜ ጋለሞታ መሰለችው። ፊትዋን ተሸፋፍና ነበርና ወደ እርስዋም አዘነበለ፡- እባክሽ ወደ አንቺ ልግባ

ወደ አንቺ ልገባ አላት። እርሰዋም ምራቱ እንደሆነች አላወቀም ነበርና። እርሰዋም፦ ወደ እኔ ብትገባ ምን ትሰጠኛለህ? አለችው። የፍየል ጠቦት ከመንጋዉ እሰድድልሻለሁ አላት። እርሰዋም፦ እስክትሰድድልኝ ድረስ መያዣ ትሰጠኛለህን? አለችው። እርሱም ምን መያዣ ልስጥሽ? አላት። እርሰዋም፦ ቀለበትህን አምባርህን በእጅህ ያለውን በትር አለችው። እርሱም ሰጣትና ከእርሰዋ ደረሰ። እርሰዋም ፀነሰችለት»/ዘፍ. 38፡15-18/።

ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት እያለ ከሌላ ወንድ ጋር ብትተኛ አመነዘረች እንደሚባል ሁሉ/ሮሜ 7፡2-3/፥ ሰዎችም ከእግዚአብሔር ውጭ ሌሎችን አማልክት ሲከተሉና ሲያመልኩ መንፈሳዊ አመንዝራነት ይባላል።

ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ውጭ ሌሎች አማልክትን ስትከተል፥ ስታጥንና ስትሠዋላቸው እግዚአብሔር፥ «ገለሞትሽ፤ አመነዘርሽ» ብሎአታል። ጌታ ይህን ቃል የተናገረው ኢየሩሳሌም በሥጋ ስላደረገችው ማመንዘር ሳይሆን፥ ለጌታ የሚገባውን ክብር ለሌላ መስጠቷን፥ የጌታን የመቅደስ የወርቅና የብር ዕቃ በኮረብታ ላይ ላሉት መስገጃዎች ማዋሏንና በመንፈስ ማመንዘሯን ለማመልከት ነው።

«ከልብሽም መስደሽ በኮረብቶች ላይ በዝንጉርጉር ልብስ ያስጌጥሻቸውን መስገጃዎች ለራስሽ ሠራሽ፤ በዚህም ገለሞትሽ፤ እንዲህም ያለ ነገር ከአሁን በፊት አልነበረም፤ ከእንግዲህም ወዲህ አይሆንም። ከሰጠሁሽም ከወርቄና ከብሬ የተሠራውን የክብርሽን ዕቃ መስደሽ የወንድ ምስሎች ለራስሽ አድርገሻል፤ አመንዝረሽባቸውግል። ወርቀ ዘቦውን ልብስሽንም መስደሽ ደረብሽላቸው፤ ዘይቴንና ዕጣኔንም በፊታቸው አኖርሽ። የሰጠሁሽንም እንጀራዬን ያበላሁሽንም መልካሙን ዱቄትና ዘይቱን ማሩንም ጣፋጭ ሽታ አድርገሽ በፊታቸው አኖርሽ፤ እንዲህም ሆኖአል ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር»/ሕዝ. 16፡16-19/።

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ አሥራ ሰባት ውስጥ የምናገኛት በግምባርዋ ላይ ምሥጢር በሆነ ስም፥ «ታላቂቱ ባቢሎን የጋለሞታዎችና የምድር ርኩሰት እናት» ተብሎ የተጻፈባት ጋለሞታ ሴት የሰሕተት ሃይማኖት ተምሳሌት/symbol/ ነች።

ይህች ሴት በየትኛውም ዘመን እንደ መንግሥት ሥልጣን ይዛ የነበረች አይደለችም። ነገር ግን ነገሥታትንና ሕዝቦችን በዝሙቷ ርኩሰት አስከራ ከእግዚአብሔር በመራቅ ከእርሷ እንዲያመነዝሩ ያደረገችና ወደፊትም እስከምትጠፋበት ቀን ድረስ በዚሁ የምትቀጥል የስሕተት አምልኮ መንገድ /የስሕተት ሃይማኖት/ ነች።

የጋለሞታዪቱ የምሥጢራዊቷ ባቢሎን ጅማሬ እንደ ከተማዋ ባቢሎን በሰናዖር ምድር ነው/ዘፍ. 11፡1–19/። በዚያን ዘመን በሰናዖር ምድር የተሰበሰቡት ሰዎች የሠሩት ሁለት ነገሮችን ነበር።

1. ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ

2. ከተማ

«እንዲሁም ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ፤ በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው አሉ»/ዘፍ. 11፡4/።

«... ስለዚህ ስምዋ ባቢሎን ተባለ፤ እግዚአብሔር በዚያ የምድርን ቋንቋ ሁሉ ደባልቋልና፤ ከዚያም እግዚአብሔር በምድር ሁሉ አንርሱን በትኖአቸዋል»/ዘፍ. 11፡9/።

ይኼ «ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ» ብለው የሠሩት ግንብ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘወር ብለው ጣዖትን እንዲያመልኩ የሠሩት የባዕድ አምልኮ መጀመሪያ ነው።

የአዳም ልጆችም ከፈጣሪያቸው ከሕያው እግዚአብሔር ዘወር ብለው ሌሎች አማልክትን ወደማምለኩና በመንፈስም ወደማመንዘር ያዘነበሉበት የጋለሞታዪቱ /የምሥጢራዊቷ ባቢሎን/ ጅማሬ ይኸው የባቢሎን ግንብ ነው። ከዚህ ግንብ መሠራት ጀምሮ በባቢሎን ብዙ የስሕተት ትምህርቶችና የጣዖት አምልኮዎች ተወልደዋል፤ አድገዋል፤ በዓለም ዙሪያም ተሰራጭተዋል። ዛሬ በዓለማችን ብዙ ሕዝቦች ከሚከተሏቸው የስሕተት መንገዶች የብዙዎቹ መነሻ ባቢሎን ነች። ግዑዝ ነገር ሠርቶ ማምለክ የተጀመረውም በጥንታዊቷ ባቢሎን ነው።

በጥንታዊቷ ባቢሎን ከሁሉ በላይ የሆነ ታላቅ አባት የሰማይ ንግሥትና ልጁ በማለት ምስልን ሠርተው ሥዕቱንም ያመልኩ ነበር። ይህም የጣዖት አምልኮ ወደ ሮም ተዛምቶ የቀድሞው

የሮም መንግሥት ይቆጣጠራቸው በነበሩት አገሮች ከክርስቶስ ልደት በፊት ተስፋፍቶ ነበር።

ዴማሱስ የተባለው በሮም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ቄስ በ378 ዓ.ም. አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ በተመረጠበት ጊዜ ይህንን የባቢሎናውያንን የጣዖት አምልኮ ሥርዓት ከቤተ ክርስቲያን ጋር በመደባለቅ በአንድነት ማካሄድ ተጀመረ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም አባት፥ ልጅና እናት ብሎ የማምለክ ሥርዓት ወደ ቤተ ክርስቲያን ዘልቆ ገባ። በባቢሎን የነበረውም ምስልን ቀርጾ የማምለክ ሥርዓት ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ የቅዱሳንን ሥዕልና ቅርጽ እየሠሩ ማክበርና ማምለክ ተጀመረ። እንዲሁም የሞቱ ቅዱሳንን ቀን በመታሰቢያነት ማክበሩ ሃይማኖታዊ ተግባር እየሆነ መጣ።

ሕይወት የሚሰጠውን የክርስቶስን ወንጌል ከመስበክና ከማስተማር ይልቅ ኖረው ያለፉትን ሰዎች ታሪክና የሕይወት ዘመናቸውን የእምነት ጉዞ እንደ ገድል እየቆጠሩ ማስተማር ተጀመረ። ከዚህም የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ከወንጌል እውነት ይልቅ የባቢሎናውያን የጣዖት አምልኮ ሥርዓት ከፍተኛውን ስፍራ መያዝ ጀመረ። እንዲሁም ኃጢአትን ለቄስ መናዘዝ፥ የመስቀልን ምልክት ማምለክና መስገድ፥ ለሌሎችም የአሕዛብ አምልኮ ወግ፥ ሥርዓቶችና በዓላት ቀስ በቀስ የክርስቲያኖች የአምልኮ ሥርዓት ክፍል ሆኑ።

ከወርቅ፥ ከብር፥ ከድንጋይ፥ ከእንጨትና ከመሳሰሉት ነገሮች የተሠሩ ምስሎችን ማምለክ ለባቢሎናውያን የተለመደ የአምልኮ ሥርዓት ነው። ባቢሎናውያን የሚያመልኩት የማይታየውን፥ መንፈስ የሆነውን፥ በእውነትና በመንፈስም ሊሰገድለት የሚገባውን እግዚአብሔርን ሳይሆን፥ በእጃቸው የቀረጹትንና የሚያዩትን ጣኦት ነው። ለአማልክቶቻቸውም ይሰግዳሉ፤ ይሠዋሉ፤ ያጥናሉ /ዮሐ. 4፡23-24/።

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የወርቅ ምስል አቁሞ ለምስሉ እንዲሰግዱ ትእዛዝ የሰጠውም ለምስል መስገድና ማምለክ ለባቢሎናውያን የተለመደ የአምልኮ ሥርዓት ስለነበረ ነው። በዚያን ጊዜም የሕያው እግዚአብሔር ባሪያዎች ከነበሩት አይሁዳውያን ከአናንያ፥ ከሚሳኤልና ከአዛርያ በስተቀር ሕዝቡ ሁሉ ናቡከደነፆር ላሠራው የወርቅ ምስል መስገዳቸውን ከእግዚአብሔር ቃል እንረዳለን /ዳን. 3፡7-12/።

በባቢሎን አምላክና የተቀረጸ ምስል አብሮ ያለና የተገናኘ ነው፤ አምላክ ካለ ምስል ሊኖር ግድ ነው።

> «... እነዚህ ሰዎች ትእዛዝህን እምቢ ብለዋል፤ አማልክትህንም አያመልኩም፤ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል አይሰግዱም»/ዳን. 3:12/።
>
> «... አምላኬን አለማምለካችሁ ላቆምሁትም ለወርቁ ምስል አለመስገዳችሁ እውነት ነውን?»/ዳን. 3:14/።

ዛሬም በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት መልኩን ቀይሮ እየተሠራበት ያለው ምስልን ቀርጾና አስቀምጦ የማምለክና የመስገድ ሥርዓት የመጣው ከጥንታዊቷ ባቢሎን ነው።

ዮሐንስ በአሥራ ሰባተኛው ምዕራፍ ውስጥ የተመለከታት ሴት በቅዱሳንና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ ነበር።

> «ሴቲቱም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ አየኋት»/ራእይ 17:6/።

ጋለሞታዪቱ ባለፉት ዘመናት ያለፉትን ስድስት ታላላቅ መንግሥታት ዘመን መርምሮ ለተመለከተ ብዙ ቅዱሳንንና የኢየሱስ ምስክሮችን ገድላለች።

በዓል የተባለውን ጣዖት ታመልክ የነበረችው የእስራኤል ንጉሥ የአክአብ ሚስት አልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት አስገድላለች/1ኛ ነገ. 18:13፥ 22/። ሌሎችም የእግዚአብሔር ነቢያትና ቅዱሳን በተለያዩ ጣዖት አምላኪዎች ተገድለዋል። ከታሪክ እንደምንረዳው፥ ጴጥሮስ በሮም ተሰቅሏል፤ ሌሎችም የክርስቶስ ሐዋርያትና ቅዱሳን በጣዖት አምላኪዎች ተገድለዋል።

ጋለሞታዪቱ ባለፈት ስድስት መንግሥታት ዘመን ብዙ ቅዱሳንን እንደገደለች እንዲሁ በአሕዛብ ዘመን ሰባተኛ በሚሆነው በአሥሩ መንግሥታት ዘመንና በአሕዛብም ዘመን ስምንተኛና የመጨረሻ በሚሆነው በተቃዋሚው ክርስቶስ መንግሥትም ላይ ለጥቂት ጊዜ ተቀምጣ ቅዱሳንን ትገድላለች። ተቃዋሚው ክርስቶስ በበረታ ጊዜ ግን የራሱን አዲስ ሃይማኖት ለማስፋፋት ጋለሞታዪቱን ያጠፋታል፤ አሥሩም ነገሥታት ይተባበሩታል።

> «ታየሃቸውም አሥር ቀንዶችና አውሬው ጋለሞታዪቱን ይጣላሉ። ባዶዋንና ራቁትዋንም

ያደርጉአታል። ሥጋዋንም ይበላሉ። በእሳትም ያቃጥሉአታል። እግዚአብሔር አሳቡን እንዲያደርጉ አንድንም አሳብ እንዲያደርጉ የእግዚአብሔርም ቃል እስኪፈጸም ድረስ መንግሥታቸውን ለአውሬው እንዲሰጡ በልባቸው አግብቶአልና» /ራእይ 17:16–17/።

ጋለሞታዪቱና ኃይሏ

«ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጎናጽፋ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቁዎችም ተሸልማ ነበር። በእጅዋም የሚያስጸይፍ ነገር የዝሙትዋም ርኩሰት የምላበትን የወርቅ ጽዋ ያዘች»/ራእይ 17:4/።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል ሴቲቱ ከለበሰችውና ከተሸለመችበት ውድ ልብስና የከበሩ ድንጋዮች ባለጠግነቷን እንረዳለን።

ወርቅና የከበሩ ድንጋዮች በመጽሐፍ ቅዱሳችን፥ የእግዚአብሔር የክብሩ ምሳሌ፥ የርሱ የሆነው ነገርም መግለጫዎች በመሆን በተለያዩ ስፍራዎች ተገለጸዋል/ዘጸ. 11:12፥ 28፤ 1ኛ ቆሮ. 3:1–2፤ ራእይ 21:18፥ 21፤ ሕዝ. 1:27፤ 8:2/።

ቀይና ሐምራዊ ልብስ የእግዚአብሔር ታቦት ማደሪያ መጋረጃዎች የተሠሩበትም ነው/ዘጸ. 26:31/።

ጋለሞታዪቱ ነገሥታትና አሕዛብ እግዚአብሔርን እንዳያዩና ወደ አምላካቸው እንዳይመለሱ በዝሙቷ የወይን ጠጅ አስክራ ለመጣል የምትጠቀምበት ኃይሏ፥ ራሷን ከእግዚአብሔር እንደሆነች የምታስመስልበት ውጫዊ ልብስና ሀብቷ ነው።

በስናዖር ምድር ያለችው የባቢሎን ከተማ /ባቢሎን/

ባቢሎንን በመጽሐፍ ቅዱሳችን መጀመሪያ የምናገኛት በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አሥር ውስጥ ነው። ባቢሎን በስናዖር

ምድር የምትገኝ አገር ስትሆን፥ የኖኅ የልጅ ልጅ የሆነው የኩሽ ልጅ የናምሩድ የመጀመሪያው ግዛት ከሆኑት አገሮች አንዱ ነች።

> «ኩሽም ናምሩድን ወለደ። እርሱም በምድር ላይ ኃያል መሆንን ጀመረ። እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ኃይል አዳኝ ነበር። ስለዚህም፦ በእግዚአብሔር ፊት ኃያል አዳኝ እንደ ናምሩድ ተባለ። የግዛቱም መጀመሪያ በሰናዖር አገር ባቢሎን፥ ኤሬክ፥ አርካድ፥ ካልኔ ናቸው»/ዘፍ. 10:8-10/።

ከጥፋት ውኃ ወዲህ የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ዓመፅ ያደረገውም በባቢሎን ነው።

> «... ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ። በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው አሉ»/ዘፍ. 11:2-4/።

ባቢሎን በሰው ልጆች ታሪክ የመጀመሪያው የባዕድ አምልኮ ማምለኪያ ግንብ የተሠራባትና ከዚህም ጋር ለሠሪዎቹ ስም ማስጠሪያና መኖሪያ ልትሆን አብራ የተሠራች ከተማ ነች።

ባቢሎንና ጣዖት አብረው የተወለዱ፥ አብረው ያደጉ፥ አብረው የኖሩና በተቃዋሚው ክርስቶስ ዘመንም አብረው የሚጠፉ ናቸው።

እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ቋንቋ የደበላለቀው በባቢሎን ሲሆን፥ በጣዖት አምላኪዎቹ መበተን ምክንያት የባዕድ አምልኮ ወደ ሌላው ዓለም የተዛመተውና በዓይነትም ይሁን በቁጥር ያደገው ከባቢሎን ተነሥቶ ነው።

> «እግዚአብሔርም ከዚያ በምድር ሁሉ ላይ በተናቸው። ከተማዪቱንም መሥራት ተው። ስለዚህም ስሟ ባቢሎን ተባለ፤ እግዚአብሔር በዚያ የምድርን ቋንቋ ሁሉ ደባልቋልና፤ ከዚያም በምድር ሁሉ ላይ በትኖአቸዋል»/ዘፍ. 11:8-9/።

ባቢሎን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ከዚህ በታች ባሉት ስሞች ተጠርታለች፤

1. ሰናዖር/ዘፍ. 11:2/
2. ባቢሎን/ዘፍ. 11:9/

3. ከለዳይ/ዘፍ. 11:28–31/
4. ሼሽክ/ኤር. 25:26/
5. ምራታይም/ኤር. 50:21/

የእግዚአብሔር ከተማና የሰዎች ከተማ

የእግዚአብሔር ከተማ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ኢየሩሳሌምን ለመጀመሪያ ጊዜ የምናገኛት በዘፍጥረት 14:18 ላይ ነው። በዚህም ስፍራ ሳሌም ተብላ ተጠርታ እንመለከታለን።

አምስቱ የመሰጴጦምያ ነገሥታት አራቱን ነገሥታት ድል አድርገው ምርኮም ይዘው ሄዱ። አብራም የወንድሙን ልጅ ሎጥንና አብቱን ለማስመለስ በቤቱ የነበሩትን ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ብላቴኖች አሰለፈ። ከዚያም ነገሥታቱን ወግቶ በድል ሲመለስ የሰዶምና የሳሌም ነገሥታት አቀባበል አድረጉለት።

ሁለቱም ነገሥታት ስጦታ አቀረቡለት። • ይሁንና፥ አብራም የተቀበለው ከሳሌም ንጉሥ ከመልከ ፄዴቅ ብቻ ነበር። የሰዶም ንጉሥ አቀባበል ያደረገለት ጠላቶቹን ስለወጋለትና ምርኮውን ስላስመለሰለት ሲሆን፥ የሳሌም ንጉሥ ግን አብራም የሚኖርባት ከጦርነቱ በኋላም በድል የተመለሰበት የሳሌም ከተማ ንጉሥ በመሆኑ ነበር።

ሳሌም፥ የእግዚአብሔር ሰው አብራም በጦርነት ከእርስዋ ወጥቶ እንደገና በድል የገባባት ከተማ ነች።

የሳሌም ንጉሥ መልከ ፄዴቅ አብራም በዘፍጥረት 14:22 የጠራውን እግዚአብሔርን በዘፍጥረት 14:18–19 በመጥራት አብራምን ባረከው።

የሳሌም ንጉሥ መልከ ፄዴቅ ከአብራም አሥራትን ተቀብሏል። «አብራምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው።»

የሳሌም ንጉሥ መልከ ፄዴቅ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ። በሺህ ዓመቱ መንግሥት በኢየሩሰሌም ለሚነግሠውና በአዲስቱ ኢየሩሳሌምም ለዘላለም ለሚነግሠው ለዘላለሙ ሊቀ ካህናችን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተምሳሌት ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ተገልያአል።

> «የሳሌም ንጉሥ መልከ ፄዴቅ እንጆራንና የወይን ጠጅን አወጣ፤ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር»/ዘፍ. 14፡18/።

> «የሰሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው። ኋላም የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው። አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም። ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱ ፍጻሜ የለውም። ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል»/ዕብ. 7፡2-3/። «ሳሌም» ማለት ሰላም ማለት ነው።

ሳሌም የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያርፍባት፥ በእግዚአብሔር የተመረጠች ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠች የእግዚአብሔር የሰላም ከተማ ስትሆን፥ ለቅዱሳን የተዘጋጀችው የሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ጥላ ነች።

> «እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ። ስሙም በእስራኤል ታላቅ ነው። ስፍራው በሳሌም ማደሪያውም በፅዮን ነው»/መዝ. 76፡1-2/።

ከአብርሃም ዘመን በኋላ ኢያቡስ በመባል በምትታወቀው ከተማ ኢያቡሳውያን በሰላም ይኖሩ ነበር።

ኢያሱ የእስራኤልን ልጆች ርስታቸውን ባወረሳቸው ጊዜ የብንያም ልጆች ኢያቡስን ወርሰው ነበር።

> «የብንያምም ልጆች ነገድ ከተሞች በየወገኖቻቸው እነዚህ ነበሩ። ኢያሪኮ... ኢየሩሳሌም የምትባል የኢያቡስ ከተማ ቂርያት ጊብዓት አሥራ ሦስት ከተሞችና መንደሮቻቸው። የብንያም ልጆች ርስት በየወገኖቻቸው ይህ ነበር»/ኢያ. 18፡21-28/።

ኢየሩሳሌም ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ከእስራኤል ልጆች ነገድ ከብንያም እጅ ወጥታ እንደገና በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ የይሁዳ ልጆች በጦርነት ሲያዙአት እንመለከታለን/መሳ. 1፡8/።

ከዚህም በኋላ ከእስራኤል ነገድ ውጭ ሆና እስከ ዳዊት ዘመን ድረስ የኢያቡሳውያን ከተማ ሆና ቆየች።

> «ሰውዬው ግን በዚያ ሌሊት ለማደር አልፈቀደም። ተነሥቶም ሄደ። ኢየሩሳሌምም ወደተባለች ወደ ኢያቡስ ፊት ለፊት ደረሰ... አሽከሩም ጌታውን፦ ና ወደዚህ ወደ ኢያቡሳውያን ከተማ እባክህ እናቅና በእርስዋም እንደር አለው። ጌታውም ከእስራኤል ወገን ወዳልሆነች ወደ እንግዳ ከተማ አንገባም። እኛ ወደ ጊብዓ እንለፍ አለው»/መሳ. 19፡10–12/።
>
> «ዳዊትም እስራኤልም ሁሉ ኢያቡስ ወደምትባል ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። በአገሪቱም ተቀመጡ። ኢያቡሳውያን በዚያ ነበሩ»/1ኛ ዜና 11፡4/።

ኢየሩሳሌም በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በሚከተሉት ስሞች ተጠርታለች፤

1. ሳሌም/ዘፍ. 14፡18/
2. ኢየሩሳሌም/ኢያ. 10፡1/
3. ኢያቡስ/መስ. 10፡10–11/
4. የዳዊት ከተማ/2ኛ ሳሙ. 5፡7/
5. ፅዮን/1ኛ ነገ. 8፡1፤ ዘካ. 9፡13/
6. የአይሁድ ከተማ/2ኛ ዜና 25፡28/
7. ቅድስቲቱ ከተማ/ነህ. 11፡1/
8. የታላቁ ንጉሥ ከተማ/መዝ. 48፡2/
9. የእግዚአብሔር ከተማ/መዝ. 46፡4/
10. አርኤል/ኢሳ. 29፡1/
11. የበዓላችን ከተማ/ኢሳ. 33፡16/
12. የእግዚአብሔር ዙፋን/ኤር. 3፡17/
13. እግዚአብሔር ጽድቃችን/ኤር. 33፡16/
14. ኦሐሊባ/ሕዝ. 48፡35/
15. እግዚአብሔር በዚያ አለ/ሕዝ. 48፡35/
16. ቅዱስ ተራራ/ዳን. 9፡16/

የሰዎች ከተማ

የሰዎች ከተማ የሆነችው ባቢሎን መሠራት የተጀመረችው በዘፍጥረት አሥራ አንድ ነው። ስለ ባቢሎን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በብዙ ስፍራዎች ተጽፎ እናገኛለን። ባቢሎን ተሸንፋለች እንጂ አልጠፋችም። እንደገናም እንደምትሠራና በመጨረሻው ዘመን ፈጽሞ እንደምትጠፋ በእግዚአብሔር ቃል ተጽፎአል።

አስቀድሞ ተነሥታ እንደነበረችው አነሣስ በዓለም ላይ ኃያል መንግሥት ሆና አትነሣም። ነገር ግን የራሷን ግዛት ዘመን ጨምሮ ከርሷ በፊትና በኋላ በነበሩት አምስት ታላላቅ መንግሥታት ዘመን የመንግሥታቱ ታላቅ ማዕከል እንደነበረች፥ እንዲሁም በሰባተኛውና በስምንተኛው መንግሥታት ዘመን እስከምትጠፋበት ቀን ድረስ የመንግሥታቱ የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካና የሃይማኖት ታላቅ ማዕከል ትሆናለች።

> *«... እርሱም ይህች ክፋት ናት አለኝ። በኢፍ መስፈሪያ ውስጥ ጣላት... ዓይኖቼንም አንሥቼ አየሁ። እነሆም ሁለት ሴቶች ወጡ። ነፋስም በክንፎቻቸው ነበረ... እነዚህ የኢፍ መስፈሪያውን ወዴት ይወስዱታል? አልሁ። እርሱም፦ በሰናዖር ምድር ቤት ይሠሩለት ዘንድ ይወስዱታል። በተዘጋጀም ጊዜ በዚያ በስፍራው ይኖራል አለኝ»/ዘካ. 5:5-11/።*

ክፋት በመባል ለተገለጸችው ሴት በሰናዖር ምድር ቤት ይሠሩላታል።

የንጉሥ ናቡከደነፆር ከተማ የነበረቸው ባቢሎን በዛሬዋ ኤራቅ ውስጥ ትገኛለች። ከጥንታዊ ግንቦቿ ዛሬም ድረስ ያልፈራረሱ የሚኖሩ ሲሆን፥ በኢራቅ ፕሬዚዳንት በሳዳም ሁሴን ትእዛዝ የናቡከደነፆር ቤተ መንግሥትና ሌሎችም ጥንታዊቷ ባቢሎንን የሚያንጸባርቁ ሐውልቶችና ሕንጻዎች ታድሰው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል።

የኤራቁ ፕሬዚዳንት ሳዳም ሁሴን ወደ ሥልጣን ከመጡበት እ.ኤ.አ. 1979 ጀምሮ የመላው ዓረብ አዳኝና መሪ የመሆን አሳብ ነበራቸው። ይህንኑ አሳባቸውንና እንደ መጨረሻ ግብ የሚያዩትን መላውን ዓረብ አንድ አድርጎ የመምራት

ፍላጎታቸውን በተለያዩ ጊዜያት በሚያደርጉት ንግግራቸውና እንቅስቃሴያቸው ሲያሳዩ ቆይተዋል።

ሳዳምን ወደ ሥልጣን ያመጣቸው የባዝ ፓርቲ የተመሠረተው እ.ኤ.አ. 1963 ሲሆን፥ የአይሁድን ወደ ተስፋዪቱ ምድር መመለስ አጥብቆ የሚቃወምና እስራኤልን በመንግሥትነት የማይቀበል ፓርቲ ነው።

ኤራቅ ሁልጊዜ እስራኤልን የምትቃወምና በየትኛውም የዓረብ–እስራኤል ጦርነት ላይ ወታደሮቿን ትልክ የነበረች አገር ነች።

ሳዳም በውስጣቸው ባደገው የመስፋፋትና የታላቅነት ምኞት የመጀመሪያ ዕቅዳቸው ያደረጉት የባሕረ ሰላጤውን አካባቢ መቆጣጠር ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ እስራኤልን ከምድረ ገጽ ማጥፋት ነው።

ይህንንም ዕቅዳቸውን እውን ለማድረግ እ.ኤ.አ. በ1980 የመጀመሪያውን ጦርነት በኤራን ላይ ከፍተዋል።

ሳዳም ኤራንን ለመውጋት ሦስት ዋና ዋና ዓላማዎች ነበሯቸው።

1. ከሺዎች ዓመታት በፊት የነበራቸው ጠላትነት

ከ1728–1686 ዓ.ዓ. በፊት በባቢሎን ነግሦ የነበረው ሐሙራቢ በ1700 ውስጥ ፋርስን ወግቶ ያሸነፋት ሲሆን፥ የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ ደግሞ በ539 ባቢሎንን አሸንፎ ይዟት ነበር። በዚህም ምክንያት የጥንቱ የጠላትነት አሻራ በዛሬዪቱ ኤራቅና እራን መካከል መኖሩ፥

2. የኤራን በኤራቅ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት

የኤራኑ ሼህ ከሥልጣን ከተወገዱ በኋላ ሥልጣኑን የያዘውና የሻይት እስልምና ተከታይ የሆነው የኮህሚኒ የእስላም ሪፑብሊክ መንግሥት በአብዛኛው የሱኒ እስልምና ተከታይ የሆነውን የኤራቁን የባዝ ፓርቲ ለመጣልና የሻይት እስልምናን በኤራቅ ውስጥ ለማስፋፋት በሰሜናዊ ኤራቅ የሚገኙትን የኩርድ አማፅያን መደገፉ፥ /ኩርዶች ዓረብ ያልሆኑና ከዓረቡ ተፅዕኖ ነጻ ለመውጣት የሚታገሉ ሕዝቦች ናቸው።/

ኤራቅ በዓለም ላይ በታላቅነቱ አራተኛ ደረጃን እንደሚይዝ በምታምንበት የጦር ኃይሏ በሳምንታት ጊዜ ውስጥ ኤራንን እንደምታንበረክክ ሳዳም አምነውበት ነበር። ዳሩ ግን ጦርነቱ ሳምንታትን አልፎ ወራትንም በማከል ስምንት ዓመታት በማስቆጠር የሳዳምን ዓላማ ከግቡ ሳያደርስ ተጠናቋል።

በጦርነቱ 130,000 ኤራቃውያን ሲሞቱ 300,000 የሚያህሉ ደግሞ ቆስለዋል። ጦርነቱ እያንዳንዱን የኤራቅ ቤተሰብ በሞት ሳይነካ እንዳልቀረ ይገመታል።

ጦርነቱ እንዳሰቡት ያልሄደላቸው ሳዳም ሁሴን ከሕዝባቸው ድጋፍ ለማግኘት በሕዝቡ ልብ ውስጥ የእስራኤልንና የኤራንን የጥንት ጠላትነት፥ እንዲሁም የኤራቅን ሕዝብ ታላቅነት ለማስቀመጥ በአካባቢው አገሮች ጭምር የነበራቸውን ከብርና ታላቅ ታሪክ የምታሳየውን የሜሴፖታሚውን ክልል ገዥ የናቡከደነፆርን ከተማ ባቢሎንን በጦርነቱ መሀል መገንባት ጀመሩ።

የንጉሥ ናቡከደነፆር ከተማ የነበረችው ባቢሎን በዛሬዋ ኤራቅ ውስጥ የምትገኝ ሲሆን፥ ከጥንታዊ ግንቦቿ ዛሬም ድረስ ያሉና ቤተ መንግሥቷ የባቢሎናውያን መቅደስና ሌሎችም የጥንታዊቷ ባቢሎን ቅሬታዎች በሳዳም ሁሴን ታድሰው ለጥንታዊት ባቢሎን መታሰቢያነት ቆመዋል።

እ.ኤ.አ. በ1987 ለባቢሎንና ለንጉሥ ናቡከደነፆር ክብር በተዘጋጀው የባቢሎን ፌስቲቫል ላይ ከመላው ዓለም የተጋበዙ እንግዶች ሲገኙ፥ የባሕል ተወዛዋዦች ከሳውዲ ዓረቢያ፥ ከቱርክ ከሆላንድና ከግሪክ፥ የጀብሲ ተወዛዋዦችና ተዋንያውን ከስፔይን፥ የባሌት ተጨዋቾች ከቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረትና ከፈረንሳይ፥ ኦርኬስትራ ከሶቭየት ኅብረት፥ እንዲሁም የኦፔራ ዘፋኞች ተገኝተው ዝግጅቶቻቸውን አቅርበዋል።

በወቅቱ ዘፈኗን ባታቀርብም አሜሪካዊቷ ማዶናም በኤራቆች ተጋብዛ በፌስቲቫሉ ላይ ተገኝታ ነበር።

በዚያን ጊዜ ሎስ አንጀለስ ታይምስ ስለ ፌስቲቫሉ ካቀረበው የሰዎች አስተያየት የሚከተለው እና ሌሎችም ይገኙበታል።

«ይህ የኤራቆች ብቻ ፌስቲቫል አይደለም የመላው ዓለም እንጂ። ምክንያቱም ባቢሎን ሥልጣኔን ለዓለም ያበረከተች የሥልጣኔ ዋና ከተማ ነች። በመላው ዓለም ያሉ ሰዎችም ባቢሎንን ለማየት ይፈልጋሉ።»

በወቅቱ ዘፈኗን ባታቀርብም አሜሪካዊቷ ማዶና በኤራቆች ተጋብዛ በፌስቲቫሉ ላይ ተገኝታ ነበር።

በዚያን ጊዜ ሎስ አንጀለስ ታይምስ ስለ ፌስቲቫሉ ካቀረበው የሰዎች አስተያየት የሚከተለው እና ሌሎችም ይገኙበታል።

«ይህ የኤራቆች ብቻ ፌስቲቫል አይደለም የመላው ዓለም እንጂ። ምክንያቱም ባቢሎን ሥልጣኔን ለዓለም ያበረከተች የሥልጣኔ ዋና ከተማ ነች። በመላው ዓለም ያሉ ሰዎችም ባቢሎንን ለማየት ይፈልጋሉ።»


ፕሬዚዴንት ሳዳም ሁሴን በፌስቲቫሉ መክፈቻ ላይ ባደረጉት ንግግር ከለዳውያን በጥንቱ ታሪካቸው ላይ ለመጨመር ዛሬ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በሚጠይቅ ሁኔታ እንዲህ ብለው ነበር።

> *«በሰው ልጅ ታሪክ ሕግን እንዳወጣውና በሥርዓት እንደመራው እንደ ሐሙራቢ የሚጠቀስ ማን አለ? ወይስ በከነዓን ምድር ላይ የነበሩትን ጠላቶቻችንን አሸንፎ ወደ ባቢሎን በምርኮ እንዳፈለሳቸው ብሔራዊ ጀግናችን እንደ ናቡከደነፆር ያለ ማን አለ? ለእኛስ በዚህ ታሪክ ላይ ለመጨመር የሚያስፈልገን ምንድነው?»*

ናቡከደነፆር እስራኤልን በጦርነት ያሸነፈና ግዛቷንም በኃይል ወስዶ የነበረ ብቸኛ የዓረብ መሪ ነበር። ሳዳም ሁሴንም ባቢሎንን በመገንባት የአካባቢው አገሮች የበላይ መሪ በመሆንና እስራኤልን በማሸነፍ የጥንቱን ታሪክ ለመድገም ይፈልጋሉ። ስለዚህም ራሳቸውን እንደ «አዲሱ ናቡከደነፆር» አድርገው ያስባሉ። ለባቢሎን ፌስቲቫል በታተሙ ፖስተሮችና ብሩሸሮች ላይ የናቡከደነፆር ሥዕልና የሳዳም ሁሴን ፎቶ ጎን ለጎን ተቀምጠው ነበር። /ገጽ .... ይመልከቱ/።

ሚስስ ጃፋር የተባለች የከርሰ-ምድር ተመራማሪ፥ «ኤራቃውያን ሳዳም ሁሴንን እንደ አዲሱ ናቡከደነፆር አድርገው ይቆጥሯቸዋል ወይ?» ተብሎ ለቀረበላት ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥታለች።

> *«አዎን በርግጥ ያስባሉ። ናቡከደነፆር ሦስት ጊዜ ኢየሩሳሌምን ያሸነፈና በብዙ አሥር ሺዎች የሚቆጠሩ አይሁዶችን ወደ ባቢሎን በማፍለስ በዓረቦች መካከል የሚታወቅና የሚታወስ ታላቅ መሪ ነበር።»*



እ.ኤ.አ. በ1987 ውስጥ ለነበረው የባቢሎን ፌስቲቫል የተዘጋጀ ፖስተር የጥንቱ ንጉሥ ናቡከደነፆርና የዛሬው ሳዳም ሁሴን

Babylon City Government Information Bureau & Public Library Zone 4




ሀ.

ለ.



ሀ. በደቡብ በኩል ያለው የባቢሎን መንግሥት መግቢያ

ለ. የታደሰው ደቡባዊው የንጉሥ ናቡከደነፆር ቤተ መንግሥት



ሀ.


ለ.




ሀ. በደቡብ በኩል ያለው የባቢሎን ቤተ መንግስት መግቢያ

ለ. የታደሰው ደቡባዊው ይንጉስ ናቡከደነፆር ቤተመንግስት

City Government Addis Ababa
Information Bureau Culture & Tourism
Public Library Zone 4




ወደ ደቡባዊው ቤተመንግስት የሚያስገባ መንገድ



በደቡብ ቤተመንግስት ወደ ንጉስ ናቡከደነፆር የዙፋን ክፍል መግቢያ*

የዞን ፩ ሕዝብ ግ.ኡ. መጻሕፍት
Zone 1 Public Library



በሳዳም ሁሴን የታደሰው የባቢሎናውያን አምላክ ቤት መግቢያ

ከባቢሎን ወደ ባቢሎን

እስራኤል ከከለዳውያን ምድር

እግዚአብሔር አምላክ አብራምን ከካራን ከመጥራቱ በፊት አብርሃምና የአባቱ ቤት ይኖሩ የነበረው በተወለደበት በከለዳውያን ዑር ነበር።

ዑር ከባቢሎን ከተማ አቅራቢያ የምትገኝ ዛሬም በዚሁ ስሟ የምትጠራ አነስተኛ የኤራቅ ከተማ ነች።

> *«የታራም ትውልድ እነሆ ይህ ነው። ታራ አብራምንና ናኮርን ሐራንንም ወለደ። ሐራንም ሎጥን ወለደ። ሐራንም በተወለደበት አገር በከለዳውያን ዑር በአባቱ በታራ ፊት ሞተ»/ዘፍ. 11፡27-28/።*

የአብርሃም አባት ታራም አብርሃምንና ሚስቱን ሣራን የልጁንም ልጅ ሎጥን ይዞ ወደ ከነዓን ምድር ሊሄድ ከዑር ወጣ። ወደ ካራንም መጥተው ተቀመጡ። አብርሃምም እግዚአብሔር እስኪጠራው ድረስ ከአባቱና ከቤተሰቡ ጋር በካራን ተቀመጠ።

> *«ታራም ልጁን አብርሃምንና የልጅ ልጁን የሐራንን ልጅ ሎጥን የልጁንም የአብራምንም ሚስት ምራቱን ሣራን ወሰደ። ከእርሱም ጋር ወደ ከነዓን ምድር ይሄዱ ዘንድ ከከለዳውያን ዑር ወጡ፤ ወደ ካራንም መጡ። ከዚያም ተቀመጡ»/ዘፍ. 11፡31/።*

ምንም እንኳን አብርሃም የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰሞቱ ከአገሩና ከዘመዶቹ ተለይቶ የወጣው ከካራን ቢሆንም፥ አስቀድሞ ከአባቱ ከታራና ከሎጥ ጋር ሆኖ ከከለዳውያን ዑር የወጣውም በእግዚአብሔር አሳብና ፈቃድ ነበር። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር፥ «ይህችን ምድር ትወርሳት ዘንድ እንድሰጥህ ከከለዳውያን ዑር ያወጣህ እግዚአብሔር ነኝ አለው»/ዘፍ. 15፡7/ ይላል። ከዚህ ቃል እንደምንረዳው፥ እግዚአብሔር አብርሃምን በመጀመሪያ ያወጣው ከካራን ሳይሆን ከዑር ነበር።

እስራኤል ከሦርያ

አብርሃም ከአባቱ፥ ከሚስቱና ከወንድሙ ልጅ ጋር ሆኖ ከዑር ከወጣ በኋላ እግዚአብሔር እስኪጠራው ድረስ የቆየው የሦርያ ከተማ በነበረችው በካራን ነበር።

እግዚአብሔር አብርሃምን ጠርቶት ወደ ከነዓን ምድር ካስገባው በኋላም ይሁን ከዚያ በፊት ጊዜው በእግዚአብሔር ቃል ውሰጥ ባይገለጽም፥ የአብርሃም ወንድም ናኮርና ሚስቱ ሚልካም ወደ ሦርያዋ ካራን ሄደው መኖር ጀምረው ነበር።

ካራን በሜሴጦጦሚያ ክልል ስትሆን፥ ናኮርና ሚስቱ ሚልካ ልጃቸው ባቱኤል የልጅ ልጆቻቸው ርብቃና ላባ/ርብቃ ወደ ይስሐቅ እስክትሄድ ድረስ/ የላባ ልጆች ሊያና ራሔል እንዲሁም ያዕቆብ ለሃያ ዓመታት በካራን ኖረዋል።

ርብቃ ልጇን ያዕቆብን ከሜሳው እንዲሸሽና ሚስትንም እንዲያገባ ወደ ወንድሟ ወደ ላባ አገር እንዲሄድ ስትነግረው፥ «አሁንም ልጄ ሆይ፥ ቃሌን ስማ፥ ተነሣና ወደ ካራን ምድር ወደ ወንድሜ ወደ ላባ ሂድ»/ዘፍ. 27፡43/ በማለት ላባ የሚኖርበት አገር ካራን መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል።

ያዕቆብ ወደ ላባ ከሄደ በኋላ በካራን ሃያ ዓመት ሲኖር ከብንያም በስተቀር አሥራ አንዱም ልጆች በሜሴጦጦምያ ክልል በሚገኘው በካራን ነው የተወለዱት። ይህንን የያዕቆብ ልጆች የተወለዱበትን አገር /ካራን/ ሦርያ እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል።

> *«... እነዚህ በሁለቱ ወንዞች መካከል በሶርያ የተወለዱለት የያዕቆብ ልጆች ናቸው»/ዘፍ. 35፡26/።*
>
> *«ሊያ በሜሴጦጦምያ በሶርያ ለያዕቆብ የወለደቻቸው ልጆችና ሴቲቱ ልጅዋ ዲና እነዚህ ናቸው»/ዘፍ. 46፡15/።*

በካራን ይኖር የነበረው ላባ ሶርያዊ ተብሎም ተጠርቷል። «ይስሐቅም አርባ ዓመት ሲሆነው ርብቃን አገባ። እርስዋም

በሁለቱ ወንዞች መካከል ያለ የሶርያዊው የባቱኤል ልጅና የሶርያዊው የላባ እህት ናት»/ዘፍ. 25:20/።

> «እግዚአብሔርም ወደ ሶርያዊው ሰው ወደ ላባ በሌሊት በሕልም መጥቶ ያዕቆብን በክፉ ነገር እንዳትናገረው ተጠንቀቅ አለው»/ዘፍ. 31:24/።

እስራኤል በአባታቸው በአብርሃም ወገብ ሆነው፥ የነገድ አለቆች በሆኑት በያዕቆብ ልጆች ወገብ ሆነውና እንዲሁም ሕዝብ ሆነው በአሕዛብ ዘመን ከነበሩት ስድስት ታላላቅ መንግሥታት ከሦስቱ ውስጥ የወጡ ሕዝቦች ናቸው። ከባቢሎንና ከአሦር ሲወጡ በተሰፋዱቱ ምድር የተቀመጡት በእንግድነት ነበር። በመጨረሻም የተስፋዱቱን ምድር ሊወርሱ የለቀቋትን ግብጽን ጨምሮ፥ ከሦስቱም አገሮች የወጡት በእግዚአብሔር ጥሪና ትእዛዝ ነው።

1. ከባቢሎን – በአብርሃም ወገብ ሆነው ከከለዳውያን ዑር ወጥተዋል። «ይህችን ምድር ትወርሳት ዘንድ እንድሰጥህ ከከለዳውያን ዑር ያወጣሁህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ»/ዘፍ. 15:7/።

2. ከሶርያ – የእስራኤል የነገድ አባቶች ከሆኑት ከአሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች አሥራ አንዱ በካራን ተወልደው አባታቸው እስራኤልን ጨምሮ ከአሶር ወጥተዋል። «እግዚአብሔርም ያዕቆብን ወደ አባትህ ምድር ወደ ዘመዶችህም ተመለስ። ከአንተም ጋር እሆናለሁ አለው»/ዘፍ. 31:3/። «ሐውልት የተቀባህባት በዚያም ለእኔ ስዕለት የተሳልህባት የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ። አሁንም ተነሥተህ ከዚህ አገር ውጣ። ወደ ተወለድህባትም ምድር ተመለስ»/ዘፍ. 31:13/።

3. ከግብፅ – እስራኤል ሕዝብ ሆነው በሙሴ መሪነት ከግብፅ ወጥተዋል። «እንዲህም ሆነ፥ አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ በዚያ ቀን የእግዚአብሔር ሠራዊት ሁሉ ከግብፅ ምድር ወጣ»/ዘጸ. 12:41/።

> *«እስራኤል ሕጻን በነበረ ጊዜ ወደድሁት። ልጄንም ከግብፅ ጠራሁት»/ሆሴ. 11:1/።*

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ በኋላ ነበር ባቢሎን እስራኤልን ከተስፋ ምድራቸው አስወጥታ እንደገና ወደ ባቢሎን ልታፋልሳቸው የሞከረችው።

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በ605፥ በ598/97 እና በ588 ዓመተ ዓለም ሦስት ጊዜ ኢየሩሳሌምን ወግቶ አሸንፎአታል። ዳንኤልን፥ ነህምያን፥ ዕዝራን፥ ኢያሱን፥ ዘሩባቤልንና ሌሎችንም የእግዚአብሔር ሰዎችና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አይሁድ ለባርነት በምርኮ ወስዷል።

ባቢሎንን ከሌሎች የአሕዛብ መንግሥታት ልዩ የሚያደርጋት በአብርሃም ወገብ ሆነው ከባቢሎን የወጡትን እስራኤልን እንደገና ለባርነት ወደ ባቢሎን ልትመልስ የሞከረችና በብዙ አሥር ሺህ የሚቆጠሩትንም የመሰለች ጠላት መሆኗ ነው።

ባቢሎን በመጨረሻው ዘመን እንደገና ትሠራለች።

> *«ከእኔም ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ ወጥቶ፦ ዓይኖችህን አንሣ። ይህችም የምትወጣው ምን እንደሆነች እይ አለኝ። እኔም፦ ምንድናት? አልሁ። እርሱም፦ ይህች የምትወጣው የኢፍ መሰፈሪያ ናት አለኝ። ደግሞም በምድር ሁሉ ላይ ያለ በደላቸው ይህ ነው አለ። እነሆም፥ የእርሳሱን መክሊት አነሡት። በኢፍ መሰፈሪያው ውስጥ አንዲት ሴት ተቀምጣ ነበር። እርሱም፦ ይህች ክፋት ናት አለኝ። በኢፍ መሰፈሪያው ውስጥ ጣላት። የእርሳሱንም ጠገራ በመሰፈሪያ አፍ ላይ ጣለ። ዓይኖቼንም አንሥቼ አየሁ። እነሆም ሁለት ሴቶች ወጡ፥ ነፋስም በክንፎቻቸው ነበረ። ክንፎቻቸውም እንደ ሽመላ ክንፎች ነበሩ። የኢፍ መሰፈሪያውንም በምድርና በሰማይ መካከል አነሡት። ከእኔም ጋር ይነጋገር የነበረውን መልአክ፦ እነዚህ የኢፍ መሥፈሪያውን ወዴት ይወስዱታል? አልሁት። እርሱም፦ በሰናዖር ምድር ቤት ይሠሩለት ዘንድ ይወስዱታል፤ በተዘጋጀም ጊዜ በዚያ በሰፍራው ይኖራል አለኝ» /ዘካ. 5፡5-11/።*

ባቢሎን ታላቅ የሃይማኖትና የንግድ ማዕከል

> *«አሕዛብ ሁሉ ከዝሙቷ ወይን ጠጅ የተነሣ ወድቀዋልና የምድርም ነገሥታት ከእርሷ ጋር ሴሰኑ፤*

የምድርም ነጋዴዎች ከቅምጥልነትዋ ኃይል የተነሣ ባለ ጠጋዎች ሆኑ ብሎ ጮኸ»/ራእይ 18:3/።

ከሀብቷ ኃይል የተነሣ የምድር ነጋዴዎች ባለ ጠጋ እንደሆኑና የንግዳቸውና የሀብታቸው ማዕከልና ምክንያት ባቢሎን እንደምትሆን ከላይ ከተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል እንረዳለን።

ባቢሎን በጣዖት አምላኪነት፥ በመተት፥ በጥንቆላና በሰይጣናዊ አምልኮዋ የታወቀች ነች። ይህ የሰይጣን አምልኮዋ ከሕጻንነቷ ማለትም ከተሠራችበት ጊዜ ጀምሮ የነበረና አሁንም ያለ ነው። እስከምትጠፋበትም ቀን ድረስ አብሮአት ይኖራል። ከተቃዋሚው ክርስቶስ መምጣት በፊትና በኋላም የተለያዩ የስሕተት ሃይማኖቶች ማዕከል ትሆናለች።

«አሁን ግን በአንድ ቀን እነዚህ ሁለት ነገሮች የወላድ መካንነትና መበለትነት በድንገት ይመጡብሻል። ስለ መተትሽ ብዛትና ስለ አስማትሽ ፅናት ፈጽመው ይመጡቡሻል»/ኢሳ. 47:9/።

ባቢሎን በሰው ልጆች ታሪክ ከጥፋት ውኃ ወዲህ በሃይማኖትና በፖለቲካ ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ ዓመፃ የተጀመረባት የመጨረሻውም ዓመፅ የሚካሄድባት አገር ነች።

ባቢሎን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከምትጠፋበት ቀን ድረስ በውስጧም ሆነ ከእርሷ ውጭ ለተፈጸመውና ለሚፈጸመው ሽብርና ግድያ ለፈሰሰውና ለሚፈሰውም ደም ተጠያቂ ነች።

በባቢሎን የባዕድ አምልኮ፥ በመተቶቿና በተለያዩ ዓመፆቿ ምክንያት የብዙ ቅዱሳን ደም ፈስሶአል። ከምድር አሕዛብም ብዙዎች ተገድለዋል።

በማናቸውም ምክንያት በምድር ላይ ለፈሰሰውና ለሚፈሰው ደም የዓመፃ መጀመሪያዋ ባቢሎን ተጠያቂ ነች።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ 23:35-36 በፈሪሳውያንና በዚያ ትውልድ ላይ ከጻድቁ ከአቤል ጀምሮ እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ድረስ የጻድቅ ደም ሁሉ እንደሚደርስባቸው ተናግሯል። የእግዚአብሔር ጻድቃንና ነቢያት ይገደሉ የነበረው እግዚአብሔርን በማይታዘዙና በባዕድ አምልኮ ተከታዮች ነበር። ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት ያስገደለችው በዓል

የተባለውን ጣዖት እያመለከች ነበር። ስለዚህም ምክንያት ፈሪሳውያንና በጌታ ዘመን የነበሩት ለሚጠየቁበትም ደም ከጥፋት ውኃ ወዲህ ላሉት ባቢሎንም ተጠያቂ ነች።

> «በእርሰዋም ውስጥ የነቢያትና የቅዱሳን ደም በምድርም የተረዱ ሁሉ ደም ተገኝባት» /ራእይ 18፡24/።

ጌታ እግዚአብሔር ባቢሎንን ስለ ትዕቢቷ ይቀጣታል። ከመጥፋቷም በፊት ትዋረዳለች። የአጋንንትና የአራዊት መኖሪያም ትሆናለች።

> «እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ባፈረሰ ጊዜ እንደነበረው የመንግሥታት ክብር የከለዳውያንም ትዕቢት ጌጥ ባቢሎን እንዲሁ ትሆናለች። ለዘላለም የሚቀመጥባት አይገኝም። ከትውልድም እስከ ትውልድ ድረስ ሰው አይኖርባትም። ዓረባውያንም ድንኳንን በዚያ አይተክሉም፤ እረኞችም መንጎቻቸውን በዚያ አያሳርፉም። በዚያም የምድረ በዳ አራዊት ያርፋሉ። ጉጉቶችም በቤቶቻቸው ይሞላሉ። ሰጎኖችም በዚያ ይኖራሉ፤ በዚያም አጋንንት ይዘፍናሉ። ተኩላዎችም በግንቦቻቸው ቀበሮችም በሚያምሩ አዳራሾቻቸው ይጮሃሉ፤ ጊዜዋም ለመምጣት ቀርቦአል፤ ቀንዋም አይዘገይም» /ኢሳ. 13፡19-22/።

> «በእነርሱ ላይ እነሣለሁ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ከባቢሎን ስምንና ቅሬታን ዘርንና ትውልድን እቆርጣለሁ ይላል እግዚአብሔር። የኛርት መኖሪያ የውኃም መቆሚያ አደርጋታለሁ፤ በጥፋትም መጥረጊያ እጠርጋታለሁ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር» /ኢሳ. 14፡22-23/።

> «... ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች ወደቀች፤ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች። የርኩሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኩሳንና የተጠሉም ወፎች ሁሉ መጠጊያ ሆነች» /ራእይ 18፡2/።

በመጨረሻም እግዚአብሔር አምላክ ስለ ባቢሎን የተናገረውን ይፈጽመዋል። ባቢሎን በአንድ ሰዓት ውስጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ በእሳት ትጠፋለች። ለዘላለምም አትገኝም።

«ከእርስዋም ጋር የሴሰኑና የተቀማጠሉ የምድር ነገሥታት የመቃጠልዋን ጢስ ሲያዩ ስለ እርስዋ ዋይ ዋይ እያሉ ያለቅሳሉ። ሥቃይዋንም ከመፍራት የተነሣ በሩቅ ቆመው፦ አንቺ ታላቂቱ ከተማ ብርቱዪቱ ከተማ ባቢሎን መዮልሽ መዮልሽ፥ በአንድ ሰዓት ፍርድሽ ደርሶአልና እያሉ ይናገራሉ» /ራእይ 18፡9-10/።

«የመቃጠልዋንም ጢስ ባዩ ጊዜ፦ ታላቂቱን ከተማ የምትመስላት ምን ከተማ ነበረች? እያሉ ጮኹ። በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነስንሰው እያለቀሱና እያዘኑ፦ በባሕር መርከቦች ያሉአቸውን ሁሉ ከባለጠግነትዋ የተነሣ ባለጠጋዎች ላደረገች ለታላቂቱ ከተማ ወዮላት። ወዮላት፥ በአንድ ሰዓት ጠፍታለች እያሉ ጮኹ» /ራእይ 18፡18-19/።



2
እስራኤል

እስራኤል በአብርሃም ወገብ ሆነው ከባቢሎናውያን ዑር የወጡ፥ ከሥርያ የተወለዱ፥ በከነዓን ያደጉና በግብፅ የተበራከቱ ሕዝቦች ናቸው።

በዚህ ስም በመጀመሪያ የተጠራው የአሥራ ሁለቱ የነገዶች አባት የሆነው ያዕቆብ ነው። «እንዲሁም አለው ስምህ ማን ነው? እርሱም ያዕቆብ ነኝ አለው። አለውም፦ ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል። ከእግዚአብሔር ከሰውም ታግለህ አሸንፈሃልና» /ዘፍ. 32፡27-28።

እግዚአብሔርን ያዕቆብን በዚህ ስም ከጠራው በኋላ የያዕቆብ ነገድ የሆኑት ሕዝቦች እስራኤል ተብለው ተጠርተዋል። ነገር ግን በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር በሁለቱም ስሞች ሲጠራቸው እናገኛልን። «አሁንም ባሪያዬ የመረጥሁህም እስራኤል ሆይ ስማ» /ኢሳ. 44፥1፤ ኢሳ. 41፥8፤ ኢሳ. 43፥1፥ 22/።

እስራኤል እግዚአብሔር የመረጠውና በአሕዛብ ዘመንም ሕግንና ሥርዓትን ተቀብሎ እግዚአብሔርን ያመልክ የነበረ ብቸኛ ሕዝብ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ቃል የገባላቸውንና በእንግድነት ይኖሩበት የነበረውን የከነዓን ምድር በኢያሱ አማካኝነት ጠላቶቻቸውን አውጥቶ አውርሷቸዋል።

ከግብፅ ምድር ወጥተው በምድረበዳ በነበሩ ጊዜም በሚወርሱአት ምድር የሚኖሩበትን ሕግና ሥርዓት በሙሴ አማካኝነት ተቀብለዋል። የእግዚአብሔርን ሥርዓትና ፍርዱን ቢጠብቁ፥ የእግዚአብሔርን በረከት እንደሚቀበሉና የአምላካቸውን ሥርዓትና ፍርድ በመጣስ ቢያምፁ ግን በቃሉ ተጽፎ የሚገኘው መርገም ሁሉ እንደሚደርስባቸው ተገልጾአል። እግዚአብሔር ካወረሳቸው ምድር ፈጥነው እንደሚጠፉና እንደሚበተኑም ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል።

> *«...ከተሞቻችሁንም ባድማ አደርጋለሁ መቅደሶቻችሁንም አፈርሳለሁ መልካሙንም መዐዛችሁን አላሸትም። ምድሪቱንም የተፈታች አደርጋለሁ የሚቀመጡበት ጠላቶቻችሁም በእርሷ የተንሣ ይደነቃሉ። እናንተንም ከአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ...» /ዘሌ. 26፡27-33/።*

ሙሴና ኢያሱ ከዮርዳኖስ ወዲህና ማዶ ያለውን ምድር ካወረሷቸው በኋላ፥ እስራኤል በተለያዩ ጌዜያት በተደጋጋሚ ፊታቸውን ከአምላካቸው በመመለስና ጣዖታትን በማምለክ እግዚአብሔርን አስቆጥተዋል። በዚህ ሁልጊዜ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸው እንዲያስጨንቋቸው አሳልፎ ሲሰጣቸው፥ እንደገናም ፊታቸውን ወደ አምላካቸው ሲመልሱ ፈራጆችንና ነገሥታትን እያስነሣ ከጠላቶቻቸው ሊታደጋቸው በመጣፍንትና እንዲሁም በነገሥታት ዘመን ቆይተዋል። ይሁንና፥ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ወግቶ እስካሸነፋት ድረስ በምርኮ ወደሌላ ምድር ብዙ ሕዝቦች አልተወሰዱም ነበር። ነገር ግን በአምላካቸው ላይ በማመፃቸው እግዚአብሔር የተናገረባቸው ቃል በባቢሎናውያን ዘመን በተደጋጋሚ ደርሶባቸዋል።

> *«እንዲሁም ይሆናል እኔ በፊትህ ያኖርሁት ይህ ነገር ሁሉ በረከቱና መርገሙ በወረደብህ ጊዜ አምላክህም እግዚአብሔር በሚበትንህ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ሆነህ በልብህ ባሰብኸው ጊዜ ወደ አምላክህም ወደ እግዚአብሔር ተመልሰህ እኔ ዛሬ እንደማዝዝህ ሁሉ አንተና ልጆችህ በፍፁም ልብና በፍፁም ነፍስ ለቃሉ*

በታዘዝህ ጊዜ አምላክህ እግዚአብሔር ምርኮህን ይመልሳል ይራራልህማል። አምላክህም እግዚአብሔር አንተን ከበተነበት ከአሕዛብ ሁሉ መካከል መልሶ ይሰበስብሃል። ሰዎችህም እስከ ሰማይ ዳርቻ ድረስ ፈልሰው እንደ ሆነ አምላክህ እግዚአብሔር ከዚያ ይሰበስብሃል ከዚያም ያመጣሃል። አባቶችህም ወደ ወረሱአት ምድር አምላክህ እግዚአብሔር ያገባሃል። ትወርሳትማለህ መልካምም ያደርግልሃል ከአባቶችህም ይልቅ ያበዛሃል። በሕይወትም እንድትኖር አምላክህን እግዚአብሔርን በፍፁምም ነፍስህ እንድትወድድ አምላክህ እግዚአብሔር ልብህን ይገርዛል። አምላካህም እግዚአብሔር ይህችን መርገም ሁሉ በጠላቶችህና በሚጠሉህ በሚያሳድዱህም ላይ ያመጣል። አንተም ተመልሰህ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ትሰማለህ ዛሬም እኔ የማዝዝህን ትእዛዙን ሁሉ ታደርጋለህ» /ዘዳ. 30፥1–8/።

እግዚአብሔር ለእስራኤል እንደተናገረው እንደዚሁ ቃል፥ እ.እ.አ. በ1948 የእስራኤል መንግሥት ፓለስታይን ተብሎ በሚጠራው ምድር ላይ ተመሥርቷል። ይህም ምድር እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ያወረሰው ነበር። ጌታ በሚቃወሟቸው ጠላቶቻቸው ሁሉ ላይ አስደናቂ ድልን እያጎናጸፋቸው ዛሬም በጠላቶቻቸው መካከል ተፈርተው ይኖራሉ።

በ70. ዓ.ም. ኢየሩሳሌም በሮማውያን ከተቃጠለችና አይሁድም ወደ አሕዛብ ከተበተኑ በኋላ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ቴዎዶር ኧርዝል የተባለው የፅዮናውያን ንቅናቄ መሥራች አይሁዶችን በፓለስታይን የማስፈሩን ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ ሞክሮ ነበር።

እንዲሁም በ1917 ዓ.ም. በወጣው የባልፎር መግለጫ የእንግሊዝ መንግሥት የአይሁዶች የመኖሪያ አገር በፓለስታይን እንዲሆን እንደሚደግፍ አስታውቆ ነበር።

በ1920ዎቹ ውስጥም የአይሁዶች ወደ ፓለስታይን መመለስ ቀስ በቀስ ቀጥሎ ነበር። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ በኋላም አይሁዶች ወደ ፓለስታይን እንዲገቡ ጥረት ተደርጎ ነበር። በወቅቱ ይህንን ሠፈራ ትቃወም የነበረችው እንግሊዝ

የድንበር ቁጥጥር ማድረጓንና የያዘቻቸውንም በየካምፑ ማጎሯን እንድታቆም ዓለም አቀፍ ግፊትም ተደርጎ ነበር።

ከዚህ ሁሉ በኋላ በእግዚአብሔር ታላቅ ተአምራት ግንቦት 14/ 1948 የእስራኤል መንግሥት መመሥረት ለዓለም ይፋ ሆነ።

ከአዲሱ መንግሥት ምሥረታ በኋላ የእስራኤልን ባለርስትነትና መንግሥትነት ያልተቀበሉ ጎረቤቶቿና ሌሎችም የዓረብ አገሮች በእስራኤል ላይ ጦርነት አወጁ። የእነዚህ ጦርነቶች ውጤት ግን እስራኤል ተጨማሪ መሬቶችንና የወራሪዎቿን ግዛት በቁጥጥሯ ሥር እንድታውል አድርጓታል።

> *«እግዚአብሔርም ያዕቆብን ይመራዋል። እስራኤልንም ደግሞ ይመርጠዋል። በአገራቸውም ያኖራቸዋል። መጻተኛም ከእርሱ ጋር ይተባበራል። ከያዕቆብም ቤት ጋር ይጣበቃል። አሕዛብም ይዘው ወደ ስፍራቸው ያመጡአቸዋል፥ የእስራኤልም ቤት በእግዚአብሔር ምድር እንደ ሎሌዎችና እንደ ገረዶች አድርገው ይገዙአቸዋል። የማረኩአቸውን ይማርካሉ፥ አስጨናቂዎችንም ይገዛሉ»* /ኢሳ. 14፡1–2/።

ከ1948–49 በተደረጉት ጦርነቶች ብቻ የእስራኤል ግዛት ምዕራብ ኢየሩሳሌምን ጨምሮ ኃምሳ በመቶ አድጓል። በጥቅምት 1956 የጋዛን አካባቢና ሲናን በመያዝ በፈረንሳይና በእንግሊዝ ዕርዳታም የስዊዝ ካናልን የተቆጣጠረች ሲሆን፥ የተባበሩት መንግሥታት ጦር ተቋቁሞ ክልሉን እስከተረከበበት እስከ መጋቢት 1957 ድረስ በእስራኤል ሥር ቆይቷል።

በግንቦት 30/1967 ግብፅና ሶርያ ጎብረት በመፍጠር ጠላታቸው የሆነችውን እስራኤልን ለማንበርከክ ጠንካራ ዝግጅት አድርገው ነበር። በዚህም ወቅት የግብፅ ፕሬዚዳንት ናሲር 80,000 ጦር አሰልፈው የተባበሩት መንግሥታት ኃይል የያዘውን ስፍራ ለቆ እንዲወጣ ትእዛዝ አስተላልፈዋል። ከዚህም በተጨማሪ የቴራንን የባሕር መንገድ በመዝጋት የእስራኤል መርከቦች በዚያ በኩል እንዳያልፍ ከልክለዋል።

እስራኤልም ሰኔ 5 ቀን ጦርነቱን ጀምራ በሶርያ፥ በግብፅና በዮርዳኖስ ላይ ጥቃት አድርሳለች። በስድስት ቀን ጦርነት ሲናን፥ የጋዛን ክልል፥ የጎላንን ተራራ፥ በዌስት ባንክ ያለውን የዮርዳኖስን ወንዝና ምሥራቅ ኢየሩሳሌምን ተቆጣጥራዋለች።

የ... መጻሕፍት
Zone ... Public Library

ቀደም ሲል የዮርዳኖስ ወንዝ በዮርዳኖስ መንግሥት እጅ ነበር።

> «በዚያን ቀን ግብፃውያን እንደ ሴቶች ይሆናሉ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ ከሚያንቀሳቅሳት ከእጁ መንቀሳቀስ የተነሣ ይሸበራሉ ይፈሩማል። የይሁዳም ምድር ግብፅን የምታስደነግጥ ትሆናለች የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከመከረባት ምክር የተነሣ ወሬዋን የሚሰማ ሁሉ ይፈራል» /ኢሳ. 19:16-17/።

አይሁድም በ1969-70 እስራኤል በስዊዝ ካናል ጦርነት አድርጋለች። አይሁድ የመቤዠት ቀን ብለው በሚያከብሩት በጥቅምት 6 ቀን 1973 በተባበሩት የሦርያና የግብፅ ጦር አዲስ ጥቃት ተሠንዝሮባቸዋል። ይህ ጦርነት እስራኤል ያላሰበችበት ቢሆንም፥ አስቀድማ ይዛባቸው በነበረው ግዛታቸው ላይ ተጨማሪ ይዞታዎችን ልትቆጣጠር ችላለች።

> «የደቡብም ሰዎች የዔሳውን ተራራ የቆላውም ሰዎች ፍልስጤማውያንን ይወርሳሉ የኤፍሬምንም አገር የሰማርያንም አገር ይወርሳሉ። ብንያምም ገለዓድን ይወርሳል። ይህም የእስራኤል ልጆች የሞፍራቸው ምርኮ የከነዓንን ሰፍራ ሁሉ እስከ ሰራጵታ ድረስ ይወርሳል በሰፋራድም የሚኖሩ የኢየርሳሌም ምርኮኞች የደቡብን ከተሞች ይወርሳሉ» /አብድዩ 19-20/።

ከዚህ ሁሉ በኋላ አሜሪካና ሶቭየት ኅብረት የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲካሄድ ጥሪ አቅርበው ነበር። እስራኤል ከግብፅና ከሦርያ ጋር በመጋቢት 5 እና ግንቦት 31 ባደረገችው ስምምነት መሠረት፥ የእስራኤል ጦር ኃይል ከስዊዝ የባሕር ቦይ ለቆ ክልሉን ግብፅ ተቆጣጥራዋለች። የጎላን ተራራም የተባበሩት መንግሥታት ባቋቋመው የሰላም አስከባሪ ኃይል ቁጥጥር ሥር ውሏል።

በተጨማሪም መስከረም 1975 እስራኤል ሲናን ለግብፅ ለቃ እንድትወጣና በግብፅና በእስራኤል መካከል የሰላም ስምምነት እንዲደረግ አሜሪካን ግፊት አድጋለች። በጎዳር 1977 የግብፅ ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳት የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናሂም ቢጌን ባደረጉላቸው የወዳጅነት ጥሪ መሠረት ኢየሩሳሌምን ጎብኝተዋል። በዚህም ጊዜ ሳዳት እስራኤልን በመንግሥትነት በመቀበላቸውና ከእስራኤል ጋር ቀጥተኛ

ግንኙነት ለማድረግ በመስማማታቸው፥ በእስራኤልና በጎረቤቶቻ መካከል የነበረው የመካከለኛው ምሥራቅ ችግር ለጊዜው ጋብ ሊል ችሏል።

በመስከረም 1978 በአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር አደራዳሪነት ለዘለቄታው በእስራኤልና በግብፅ መካከል የሰላም ስምምነት እንዲኖርና ሁለቱም አገሮች ለመካከለኛው ምሥራቅ ሰላም የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ የካምፕ ዴቪዱ ስምምነት በቤጊንና በሳዳት ተደርጓል። በተጨማሪም በዌስት ባንክ ለፍልስጤም ሕዝብ ነዋሪዎች ሙሉ የራስ ገዝ አስተዳደር እንዲሆን ተስማምተዋል።

ይህም ስምምነት በመጋቢት 26/1979 በሁለቱ አገሮች መሪዎች የተፈረመ ሲሆን፥ ፕሬዚዳንት ካርተርም የምስክርነት ፊርማቸውን አኑረዋል። በዚህም ስምምነት መሠረት በሚያዝያ 1982 እስራኤል ሲናን ለግብፅ መልሳለች።

ምንም እንኳን እስራኤል ከግብፅ ጋር ባደረገችው የሰላም ስምምነት ለረዥም ዓመታት በመካከላቸው የነበረው ግጭት ቢረግብም፥ በቀጥታና በሽምቅ ጦርነት ከከፈቱባት ከጎረቤት አገሮቿ ጋር ተደጋጋሚ ፍልሚያዎችን አድርጋለች።

በመጋቢት 1978፥ በሐምሌ 1981 እና በሌሎችም ዓመታት ከፍልስጤም ነፃ አውጪ ሽምቅ ተዋጊዎች ጋር ተደጋጋሚ ውጊያዎችን አድርጋለች።

በጥር 1991 በኢራቅና ኩዌት (የባሕር ሠላጤው) ጦርነት፥ የተባበሩት መንግሥታት ጦር ኢራቅ ከኩዌት ለቃ እንድትወጣ ጥቃት በሰነዘረባት ወቅት ኢራቅ በርካታ ሰኮድ ሚሳይሎችን ወደ እስራኤል ወንጭፋለች። ዛሬም ድረስ አደጋ በመጣልና አንዳንዴም በቀጥታ ውጊያ በመክፈት ከሚወጓት ከሀማስና ከመሳሰሉት ኃይሎች ጋር በመፋለም ላይ ትገኛለች።

ዛሬ ያለንበት ዘመን ከምን ላይ እንደደረሰ ለመመርመርና ስለመጨረሻው ዘመን ለመረዳት የመካከለኛው ምሥራቅ ሁኔታን መከታተል ያስፈልጋል።

ምንም እንኳን የእስራኤል መሪዎች ከፍልስጤምና ከሌሎች አገር መሪዎች ጋር ተደጋጋሚ የሰላም ውል ቢፈራረሙም፥ በእስራኤል ላይ እየታየ ያለው ውጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው። በመጨረሻው ዘመን ላይ

ተቃዋሚው ክርስቶስ ጦሩን ወደ እስራኤል እንደሚያስገባ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተጽፎአል።

> «እነሆ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል። ብዝበዛሽንም በውስጥሽ ይካፈላሉ። አሕዛብንም በኢየሩሳሌም ላይ ለሰልፍ እሰበስባለሁ ከተማይቱም ትያዛለች...» /ዘካ. 14፥1-2/።

ዛሬ ከእስራኤል ጎን ያለችው አሜሪካን ነገ አብራት ላትቆም ትችላለች። አሁንም እንኳን ባካባቢው ሰላምን ለማምጣት በማለት እስራኤል ግዛቶቿን ለፍልስጤማውያን እንድትሰጥና ሌሎችንም ህልውናዋን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ስምምነቶችን እንድታደርግ በአሜሪካን መንግሥት ግፊት እየተደረገባት ነው። ብዙዎቹን የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ስንመለከት ከዓረብ አገሮች ጋር ያላችውን ጥቅም ለመጠበቅም ይሁን ለሌላ ጉዳይ ለእስራኤል መንግሥት ያላቸው አመለካከት ብዙም ጤናማ አይደለም። በተለይም ግዛቷን ላለመስጠት ባላት አቋም ላይ ተቀናቃኝነታቸው ጎልቶ ይታያል።

ወዳጆቿ ሰላምን ለማምጣት፥ ጠላቶቿ ለማጥፋት በሚወስዱት እርምጃ ሁሉም ግዛቷን የሚደፈር ድርጊት እየፈጸሙ ናቸው።

ተቃዋሚው ክርስቶስ በቀድሞው የሮም መንግሥት ግዛት ሥር ከነበሩት ሃያ አራት አገሮች በአሥሩ መንግሥታት ከሚመሠረተው መንግሥት ውስጥ እንደሚመጣ ይታወቃል። ዛሬ ምዕራባውያኑ ለእስራኤል ያላቸው ቀዝቃዛ ወይም የተቃውሞ አመለካከት ተቃዋሚው ክርስቶስ ተገልጦ በእስራኤል ላይ በሚነሣበት ጊዜ ከርሱ ጋር አንድ አሳብ ለሚያደርጋቸው ርእስ እየተዘጋጁና እየተመቻቹ ይሆን? የዛሬዎቹ የእስራኤል ወዳጆችስ ነገ ጠላቶች ሆነው ከተቃዋሚው ክርስቶስ ጎን ላይቆሙ ይችሉ ይሆን?

እስራኤል በመጨረሻው

ዘመን / ራእይ 12፥1-2/

> «ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ፤ ፀሐይን ተጎናጽፋ ጨረቃ ከእግሮቿ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት

ነበረች፤ እርስዋም ፀንሳ ነበር፤ በምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች።»

- ይኼ በሰማይ የታየው ምልክት (symbol) ሲሆን፥ ምልክቱ የሚያሳየው በምድር ስለሚከናውነው ነገር ነው።
- በቁጥር 1 ላይ የተገለጸችው ሴት እስራኤል ነች። ይህች ሴት እስራኤል እንጂ ቤተ ክርስቲያን ወይም ሌላ አለመሆኗን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1. እስራኤል በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን እንዳገባች ሴት ሆና ከእግዚአብሔር ጋር ባደረገችው ቃል ኪዳን ትታወቃለች /ኢሳ. 54፡4-6፤ ኤር. 3፡11-14፤ ሆሴ 2፡16-22/።

«ፈጣሪሽ ባልሽ ነው ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው...» /ኢሳ. 54፡4/። ቤተ ክርስቲያን ግን በየትኛውም ሰፍራ ያገባች ሴት በሚል ተምሳሌት አልተጠቀሰችም። በኤፌሶን 5፡21-33 ባለው ክፍል የጌታ ቃል የባልና ሚስትን ጥምረት ከክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን ጋር በማነጻጸር ያቀርባል። በዚህ ክፍል ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ግንኙነት የባልነትና የሚስትነት ጉዳይ ከመሆኑ ላይ አይደለም። ዋናው ሊገለጽ የተፈለገው አሳብ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደሆነ ሁሉ ባልም የሚስት ራስ እንደሆነ ለመግለጽ ነው። ይህም ራስነት ከጋብቻ ውጪም ይሆናል። ይህም ሲባል ባልና ሚስት ባይሆኑም፥ ወንድ የሴት ሁሉ ራስ ነው። ክርስቶስ ደግሞ የወንድ ራስ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ የክርስቶስ ራስ ነው። «ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ የሴትም ራስ ወንድ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ እወዳለሁ» /1ኛ ቆሮ. 11፡3/።

ራስ መሆን ጋብቻን የሚያመለክት ሲሆን፥ በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት የወንድ ባል ክርስቶስ የክርስቶስ ባል እግዚአብሔር ነው ልንል ነው ማለት ነው። ነገር ግን ይህ ራስነትን እንጂ ጋብቻን አይመለከትም።

በኤፌሶን ምዕራፍ 5 ቁጥር 29 እና 30 ውስጥ፥ «ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለ ሆንን ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት

ይመግበዋል። ይንከባከበውማል» /29-30/። ይህም ክፍል የሚገልጸው ሰው እናቱንና አባቱን እንደሚተው፥ ከሚስቱም ጋር እንደሚተባበርና ሁለቱም አንድ ሥጋ እንደሆኑ ነው። ከዚያ በኋላ ባል ከሚስቱ ጋር አንድ ሆኗልና ሚስቱ የአካሉ ክፍል ነች። ስለዚህ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ የለም። ነገር ግን የገዛ ሥጋውን ይመግባል ይንከባከውማል። እንግዲህ ባልና ሚስት በጋብቻቸው አንድ አካል ሆነው ባል እንደራሱ አካል ሚስቱን እንደሚንከባከብ ሁሉ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የአካሉ ክፍል እንደመሆኗ መጠን እኛን (ቤተ ክርስቲያን) እንደሚከባከብ የሚያሳይ ነው። እውነተኛ የወይን ግንድ (አካል) ክርስቶስ ነው ቅርንጫፎቹ (የአካል ክፍሎቹ) እኛ (ቤተ ክርስቲያን) ነን /ዮሐ. 15፥5/።

በዚህ ቃል መሠረት ቤተ ክርስቲያን በሚስትነት አልተጠቀሰችም ማለት ነው። በራእይ 17 ላይ የተጠቀሰችው ሐሰተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን (ጋለሞታይቱ) ብቻ ሴት ተብላ የተገለጸች ስትሆን፥ እሷ ደግሞ በራእይ ምዕራፍ አሥራ ሁለት የተመለከተችውን ሴት ልትሆን አትችልም።

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የ3 ዓይነት ክፍል ሕዝቦች አሉ /1ኛ ቆሮ. 10፡32/፡-

1. አይሁድ
2. ቤተ ክርስቲያን
3. አሕዛብ

በራእይ 12፥6፥ ሴቲቱ ለዘመን ለዘመናትና ለዘመን እኩሌታ ($3^{1/2}$ ዓመት) ወደምትቆይበት በረሃ ከዘንዶው ፊት እንደ ሸሸች ይናገራል። ስለዚህ ይህ ጊዜ በዳንኤል ራእይ በተገለጸው በ70ኛው ሳምንት አጋማሽ ማለትም የ7 ዓመቱ አጋማሽ ላይ መሆኑን ያሳያል። በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ቀደም ብላ ስለተነጠቀች በምድር የለችምና ቤተ ክርስቲያን ልትሆን አትችልም። በዚህ ጊዜ ማለትም በመጨረሻው 7 ዓመት አጋማሽ ላይ በምድር የሚኖሩት ሁለቱ ክፍሎች አይሁድና አሕዛብ ናቸው።

- ሴቲቱ አሕዛብንም ልትሆን በፍጹም አትችልም። ምክንያቱም አሕዛብ ሴቲቱን ከሚያሳድዱት ወገን ናቸውና።

- ስለዚህ የዚህች ሴት ተምሳሌትነት ለ.ሆን የሚችለው እስራኤልን ብቻ ነው።

3. ፀሐይ ጨረቃና 12 ከዋክብት (በዘፍ. 37።9-11) እንደተገለጸው የእስራኤል ተምሳሌቶች ናቸው።

4. በመጽሐፍ ቅዱሳችን፥ በመጨረሻው ዘመን በምጥ የሚጋዙና የሚወለዱ ሕዝቦች በመባል የተጠቀሱት አይሁድ ብቻ ናቸው /ራእ. 12፥2-5፤ ማቴ. 24፥8፤ ማር. 13፥8፤ ኢሳ. 66፥7-8፤ ኤር. 30፥6-8፤ ሚክ. 5፥2-6/።

> *«ሳታምጥ ወለደች። ምጥም ሳያገኛት ወንድ ልጅን ወለደች ከቶ እንዲህ ያለ ነገር ማን ሰምቶአል? እንዲህስ ያለ ነገር ማን አይቶአል? በውኑ አገር በአንድ ቀን ታምጣልችን? ወይስ በአንድ ጊዜ ሕዝብ ይወለዳልን? ፅዮን እንዳማጠች ወዲያው ልጆችዋን ወልዳለችና /ኢሳ. 66፥7-8/።*

- በኢሳይያስ 66፥7-8 አገር የሆነችው እስራኤል አምጣ ሕዝቦችን እንደምትወልድ ተጠቅሶአል።

- ሴቲቱ ዘንዶው ሊያሳድዳት ከንፍ ተሰጥቷት ወደ ምድረ በዳ እንደበረረችና እንዳመለጠች እንዲሁ እስራኤል (አይሁድ) በመጨረሻው ዘመን ከሚያሳድዱዋቸው ከጠላቶቻቸው ፊት ወደ ምድረ በዳ እንደሚሸሹ በእግዚአብሔር ቃል በተለያዩ ስፍራዎች ተጽፎአል።

  ስለዚህ በራእ. 12 ላይ የምንመለከታት ሴት እስራኤል ነች ማለት ነው።

የሴቲቱ ልጅ /ራእይ 12፥5/

- በራእይ 12፥1 ላይ የተጠቀሰችው ሴት እስራኤል (Natinal Israel) ከሆነች፥ በእግዚአብሔር የፍጥረት ሕግ መሠረት የወለደችውም ልጅ የእርሷ ዘር እስራኤል መሆን አለበት። የተወለደውን ልጅ ቤተ ክርስቲያን ነው እንድንል ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ሥራ 15፥13-15 በተገለጸው መሠረት የአሕዛብም ሁሉ ስብስብ እንጂ የእስራኤል ዘር ብቻ አይደለችም።

- ሴቲቱ ሕዝብ (እስራኤል) እንደሆነች ሁሉ የወለደችውም ልጅ ሕዝብ (እስራኤል) መሆን አለበት።

- በተጨማሪም ከራእይ. 4÷1 ጀምሮ ያለው ሂደት በሙሉ ከቤተ ክርስቲያን ንጥቀት በኋላ የሚካሄድ ነው። ቤተ ክርስቲያን በራእይ ውስጥ የተገለጸችው ከ2÷1 እስከ 3÷22 ባለው ክፍል ነው። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ከራእይ 4÷1 በፊት ተነጥቃለች። ይህ ልጅ የተወለደው በሰባቱ የመከራ ዘመን የመጀመሪያው 3 ዓመት ተኩል መጨረሻ ላይ ስለሆነ÷ ያኔ ቤተ ክርስቲያን አልነበረችምና ቤተ ክርስቲያን ልትሆን አይችልም።

  «ከእባቡም ፊት ርቃ አንድ ዘመን ዘመናትም የዘመንም እኩሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሃ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት» /ራዕ. 12÷14።

- ይህ ልጅ ክርስቶስም አይደለም።

1. በቁጥር 5 ላይ «አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች» ይላል። በዚህ ስፍራ አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር የሚገዛው ክርስቶስ ነውና ይህ የተወለደው ሕፃን ክርስቶስ ነው ልንል እንችል ይሆናል። ነገር ግን በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የመኖር ዕድል ያላቸው ሁሉ ከበጉ ከክርስቶስ ጋር ሆነው አሕዛብን በብረት በትር ይገዛሉ /ራእይ 2÷26-27/። «ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻው ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፤ በብረትም በትር ይገዛቸዋል... »

2. ይህ ወቅት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ዘመን አልፎ በመከራው ዘመን አጋማሽ የሚሆን ነው። ታዲያ በዚህ ወቅት ዮሐንስ እንዴት ክርስቶስን ገና ሲወለድ ያየዋል?

3. ይህ ሕፃን ዘንዶው ሊበላው ቢፈልግም ሞትን ያላየ ገና እንደ ተወለደ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የተነጠቀ ነው። ክርስቶስ ግን በዚህ ዓለም ተወልዶ ከመጣ በኋላ ሞትን ቀምሷል። ቤተ ክርስቲያንም ብትሆን በክርስቶስ አምነው የሞቱና በሕይወት ያሉ ቅዱሳን ስብስብ ነች እንጂ በሕይወት ያሉ ብቻ አይደለችም /1ኛ ተሰ. 4:13-18/።

- እንግዲህ ይህን ሕፃን ሊሆን የሚችለው አሕዛብን በብረት በትር ከሚገዙት ከአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ማለትም ከክርስቶስ፥ ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳን፥ ከቤተ ክርስቲያን፥ ከ144,000 አይሁድ፥ ከመከራው ዘመን ቅዱሳንና ከሁለቱም ምስክሮች ሆኖ ሞትን ያላየ የእስራኤል ልጅ የሆነ ነው ማለት ነው።

ይህን ሊያሟላና ሊሆን የሚችሉት 144ሺው የእስራኤል ልጆች ብቻ ናቸው። ምናልባትም ከዚህ በፊት ሕያዋን ሆነው በእግዚአብሔር ዘንድ ያሉትን የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳንን ቅዱሳን ነው እንዳንል እነዚህ ሁሉ የሚሞተው የማይሞተውን፥ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ለብሰው (1ኛ ቆሮ. 15፥ 51–55) ሕያዋን ሆነዋል። ሞትም ከዚያ ወዲያ ሊይዛቸው አይችልምና ዘንዶው ሊበላቸው የሚሞክርበት መንገድ አይኖረውም። ስለዚህ ሕፃኑ ልጅ እነርሱን ሊወክል አይችልም።

ነገር ግን በራእይ 7፥1–8፤ 9፥4፤ 14፥1–5፥ ስለ 144,000 እስራኤላውያን ስንመለከት ምድርንና ባሕርን ሊጎዱ የተሰጣቸው አራቱ መላእክት ከሚያመጡት መከራና የመጀመሪያዎቹ 6 መለከቶች በሚነፉበት ጊዜ በምድር የሚሆነው መከራ እንዲያገኛቸው ከዚያ በፊት ግንባራቸው ሲታተም እንመለከታለን።

> *«የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጉዱ አላቸው። የታተሙትንም ቁጥር ሰማሁ ከእስራኤል ልጆች ነገድ ሁሉ የታተሙት መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ» /ራእይ 7፥3–4/።*

- እነዚህ አይሁድ በመለከቶች በምድር ላይ ከሚመጣው ፍርድ የተነሣ ጉዳት እንዳያገኛቸው ሲታተሙ እናያለን። ወዲያው ከሰባተኛው መለከት በኋላ /ከራእይ 11፥15–18/ በቀጥታ (በራእይ 14፥1–5፥ 12፥ 5) ላይ በሰማይ ሆነው እናገናቸዋልን።

እነዚህ 144,000 አይሁድ ምንም መከራና ሞት ሳያገኛቸው ግንባራቸውን ታትመው ከዚያም በሰማይ ሆነው እናያቸዋለን።

- እግዚአብሔር ሰይጣን ሊያመጣባቸው ከነበረው ጉዳት ጠብቆ ወደ እርሱ ዙፋን ይወስዳቸዋል /ራዕይ 12፥4–5/። ሰይጣንም ወደ ምድር ይጣላል። ሰይጣን በመጀመሪያዎቹ 6

መለከቶች ስለተጠበቁ እጅግ ተቆጥቶ በሰባተኛው መለከት ሥር ሊያጠፋቸው ፈልጎ ነበር /ራእይ. 12፥4-5/። ሰይጣን እነርሱን ሳያገኝ ሲቀር በመቆጣት ሴቲቱንና ዘርዋን ለማጥፋት እርሷን አሳደደ /ራእይ 12፥13-17፤ ዳን. 8፥9-14፤ ዘካ. 14፥1-2/።

- በራእይ 12 ውስጥ የተገለጹት ሴቲቱ፥ ልጁና የሴቲቱ ዘር የሚወክሉት አይሁድን ብቻ ነው /ራእይ 12፡1-2፥ 5፥ 17/።

እንግዲህ በአዲስቱ ኢየሩሳሌም ከሚኖሩት የቅዱሳን ቡድን (የፊተኛው ትንሣኤ ልጆች) የሴቲቱን ልጅ መሆን የሚችሉት 144 ሺው እስራኤላውያን ብቻ ናቸው።

- መቶ አርባ አራት ሺው በሰማይ የታዩበት ሰዓትና /ራእይ 14፥1/ የሴቲቱ ልጅ ወደ ሰማይ የተነጠቀበት (ራእይ 12፥5) ጊዜ አንድ ነው። ሁለቱም ከመጀመርያው 3 ዓመት ተኩል በኋላ ነው።

- ቤተ ክርስቲያንና የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን የተነጠቁት ከሰባቱ ዓመት በፊት ነው።

- በመከራው ዘመን የሚያልፉትና የሚገደሉት ቅዱሳን ደግሞ ተነጥቀው በሰማይ የምናያቸው 144ሺውን በሰማይ ካየናቸው በኋላ ነው /ራእይ 6፥9-11፤ 7፡9-17/።

- ከነዚህ የመከራው ዘመን ብዙ ሰማዕት ሌላ ከእነርሱ በፊት በሰማይ ሆነው የምናያቸው 144 ሺውን ነው። እንግዲህ እነዚህ 144,000 ወደ ሰማይ የሚነጠቁት በራእይ 12፥5 ላይ ካልሆነ ምንጊዜ ሊሆን ነው? ከቤተ ክርስቲያን ንጥቀት በኋላ ከታላቁ መከራ በፊት የመነጠቅን ተራ ይዘው የምናገኛቸው 144ሺዎቹን ነው።

- እንግዲህ 144ሺውና የሴትቱ ልጅ አንድ ካልሆኑ፥ 144ሺው እንዴት ወደ ሰማይ እንደተነጠቁና የሴቲቱም ልጅ ማንን እንደሚወክል አናውቅም ማለት ነው። ነገር ግን በቅደም ተከተል ስናስቀምጠው /ራእይ 7፥1-8፤ 9፥4፤ 12፥5፤ 14፥15/ ለ144ሺው ሙሉ የሆነ መገለጥ ይሆንልናል።

- በመጀመሪያዎቹ ስድስት መለከቶች ቁጥራቸው፥ ደኅንነታቸው፥ መታተማቸውና በመከራ ውስጥ እንዳይጎዱ

የተደረገላቸው ጥበቃ የተገለጸ ሲሆን፥ በሰባተኛው መለከት አማካኝነት የሴቲቱን ልጅ በመሆን ወደ ሰማይ ሊነጠቁና ከንጥቀት በኋላ በሰማይ የተሰጣቸውን ስፍራና ክበር እናያለን። ይህ እንዲህ ሲሆን የ144 ሺውና የሴቲቱ ልጅ ምሥጢር መገለጥ ሙሉ ይሆናል።

- በራእይ 14፥1–5 እንደተገለጸው፥ 144,000 በመጨረሻው የ3 1/2 የመከራ ጊዜ እነርሱ በሰማይ ናቸው። *የፅዮን ተራራ* ተብሎ የተጠቀሰው ሰማያዊውን ስለሆነ፥ እነዚህ 144ሺው የሴቲቱ ልጅ ካልሆኑና /በራእይ 12፥5/ ላይ ካልተነጠቁ ወደ ሰማይ የሄዱት ምን ጊዜ ሊሆን ነው?

  144ሺው ለእግዚአብሔር በኩራት ናቸው። ከእነርሱ በፊት በጌታ ኢየሱስ አዳኝነት አምነው ከአሕዛብ ጋር በቤተ ክርስቲያን የተነጠቁት አይሁድ በቤተ ክርስቲያን ነው የሚጠቃለሉት። ቤተ ክርስቲያን ስትነጠቅ ማለትም ከሰባቱ የመከራ ዘመን በፊት እነዚህ 144ሺው አልዳኑም ነበር። ያኔ ቢድኑ ኖሮ እንደ እግዚአብሔር ቃል በቤተ ክርስቲያን ይነጠቁ ነበር /1ኛ ተሰ.4፥15፤ 1ኛ ቆሮ. 15፥23/። ስለዚህ እነርሱ ከመጨረሻው 3 1/2 ዓመት የመከራ ዘመን በፊት ድነው በሰማይ ስለታዩ እነርሱ አምነው የዳኑት በመጀመሪያው 3 1/2 ውስጥ ነው ማለት ነው። እንግዲህ /የራእይ 12፥5/ የሴቲቱ ልጅ 144ሺውን ሳይሆን ሌሎቹን እስራኤላውያን የሚወክል ከሆነ እነርሱ ለእግዚአብሔር ከእስራኤል በኩራት ይሆኑ ነበር። እናም 144ሺው በኩራት አይሆኑም ነበር።

- ከቤተ ክርስቲያን ንጥቀትና ከታላቁ መከራ ቅዱሳን ንጥቀት መካከል የሚነጠቅ አንድ ቡድን ብቻ ነው። ነገር ግን 144 ሺው የሴቲቱ ልጅ አይደለም ካልን በቤተ ክርስቲያንና በመከራው ዘመን ቅዱሳን መካከል ሁለት ቡድኖች ሊኖሩ ነው ማለት ነው። ሁለቱም ቡድኖች ለየብቻቸው ሲሆኑ፥ ሙሉያልሆኑና የማይታወቁ ምሥጢራዊ ይሆናሉ።

- 144ሺውን እንዴት እንደተነጠቁ አናይም።

- የሴቲቱ ልጅ እንዴት እንደተነጠቀ እናያለን።

- 144ሺውን በሰማይ በስፍራቸው እናገኛቸዋለን።

- የሴቲቱን ልጅ በሰማይ በየትኛው ስፍራ አናገኘውም።

- የ144ሺው ማንነት ከነታሪኩ በግልጽ ተቀምጧል።
- የሴቲቱ ልጅ ማንነት ግን አይታወቅም።

ስለዚህ እነዚህን ሁለት የተለያዩ ቡድኖች ካደረግናቸው የማይፈታ ምሥጢር ሆነው እናገኛቸዋለን። አንዱን ከአንዱ ጋር ስናገናኛቸው ግን ሙሉና ትክክል ይሆናል።


144ሺው እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ከእስራኤል በኩራት ሆነው ይድናሉ።

- የሴቲቱን ልጅ በመሆን ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ።
- በሰማይ በጌታ ዙፋን ፊት 144ሺው ሆነው እናገኛቸዋለን።

ስለዚህ የሴቲቱ ልጅ መሆን የሚችሉት 144ሺው ብቻ ናቸው።

- የሴቲቱ ልጅና 144ሺው ሁለቱም የሚወክሉት የተወሰነ የሕዝብን ክፍል ነው።
- ሁለቱም የሚወክሉት የእስራኤልን ልጆች ነው።
- ሁለቱንም ዘንዶው ሊያጠፋቸው ፈልጎ ከዘንዶው ተጠብቀዋል /ራእይ 12፥ 4–5፤ 7፥1–8፤ 9፥4፤ 14፥ 1–5/።
- ሁለቱም ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ሄደዋል /ራእይ 12፥5፤ 14፥1–5/።
- ሁለቱም ሰማያዊ ሕዝቦች ይሆናሉ። /ራእይ 12፥5፤ 14፥1–5/። በእነዚህ ሁሉ ሁለቱም አንድ ናቸው።
- በኢሳይያስ 66።7–8 እንደተገለጸው ሴቲቱ ፅዮን በአንድ ጊዜ የወለደቻቸው ልጆች ከእስራኤል የሚድኑት 144,000 የእስራኤል ልጆች ናቸው።

ስለዚህ ይህን ሁሉ መረጃ ከእግዚአብሔር ቃል ስንመለከት (በራእይ. 12፥5) ላይ የተጠቀሰው የሴቲቱ ልጅ (በራእይ 7፥3–8) እና (በራእይ 14፥1–5) የተጠቀሱትን 144,000 አይሁዶች የሚወክል መሆኑን እናውቃለን።



3

ትንሣኤና ንጥቀት

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ሁለት ዓይነት ትንሣኤዎች እንዳሉ ተገልጾአል፤

- ፊተኛው ትንሣኤ (ለሕይወት)
- ሁለተኛው ትንሣኤ (ለፍርድ፥ ለሁለተኛው ሞት)

«ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው»/ራእይ 20፡14/። «የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም» (ራእይ 20፡5)።

በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 20 ቁጥር 5 እና 6፥ «ይህ የፊተኛው ትንሣኤ ነው። በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም...» ይላል።

በፊተኛው ትንሣኤ የሚነሡ ሁሉ የትንሣኤ ጊዜያቸው ከክርስቶስ የሺህ ዓመቱ መንግሥት በፊት የሚፈጸም ይሆናል። ከዚያም ከክርስቶስ ጋር ሺውን ዓመት ይነግሣሉ። «በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው። ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም። ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ። ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።»

የመጨረሻው መጨረሻ

ራእይ 20:6 እንደሚያስመለክተው፥ በፊተኛው ትንሣኤ የማይነሡ ሁሉ ፍርድ የሚጠብቃቸውና የሁለተኛው ሞት ሰለባዎች ይሆናሉ። «የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም» /ራእይ 20:5/። ከዚህ ቀጥሎ የፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያላቸውንና ሺህውን ዓመት ከክርስቶስ ጋር በምድር የሚነግሡትን እንመለከታለን፤

1. ጌታ ኢየሱስ
2. ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ የተነሡት የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን
3. ቤተ ክርስቲያን
4. 144,000 አይሁዳውያን
5. በመከራው ዘመን የሚድኑ ቅዱሳን
6. ሁለቱ ምስክሮች

- እነዚህ ቡድኖች በሙሉ የሚነሡት በመጀመሪያው ትንሣኤ ነው። የመጀመሪያ ስንል አንደኛው ቡድን አንደኛ፥ ሁለተኛው ቡድን ሁለተኛ... እያልን በመቁጠር የመጨረሻውን ስድስተኛ ትንሣኤ አንልም።
- ያለው ትንሣኤ ሁለት ብቻ ነው፤

ፊተኛው ትንሣኤ ለሕይወት

ኋለኛው ትንሣኤ ለሁለተኛው ሞት

የጌታ ቃል <u>በራእይ 20:6</u>፥ «በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያላቸው ብፁዓን ናቸው። ሁለተኛው ሞት አይሠለጥንባቸውም» ሲል፥ ከፊተኛው ትንሣኤ ውጭ (በኋላ) የሚሆነው ትንሣኤ ሁለተኛው ሞት የሚሠለጥንበት ትንሣኤ ነው ማለት ነው።

የዚህ የፊተኛው ትንሣኤ ዕድለኞች የሆኑት 6 ቡድኖች የሚነሡት በአንድነት ነው ወይስ በየተራ?

መልሱ <u>በየተራ ነው</u>። ይሁንና የሚነሡበትን ጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል እንመለከታለን፤

በመጀመሪያ በተራ መሆኑን የጌታ ቃል እንዲህ ሲል ይናገራል፤

> *«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቷል። ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ*

እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል። ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው» /1ኛ ቆሮ. 15:2023/።

- በቁጥር 22 እና 23፥ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ ሁሉ በክርስቶስ ሕያዋን እንደሚሆኑና ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ እንደሚነሣ ይናገራል።

- ክርስቶስ ላንቀላፉት የትንሣዔ መጀመሪያ በኩር ሆኖ ተነሥቷል /ቁጥር 20/።

እንግዲህ ሌሎቹ እያንዳንዳቸው ከበኩሩ ከክርስቶስ በኋላ በየተራ ይነሣሉ ማለት ነው።

«ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው» /ቁጥር 23/።

የእግዚአብሔር አሳብ ሁሉን በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው /ኤፌሶን 1:10/።

- በዚሁ መሠረት ፊተኛው ትንሣኤ የኃይማኖታችን ሊቀ ካህናትና ሐዋርያ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አስቀድሞ፥ ከሺህ ዓመቱ በፊት የመጨረሻ እስከሚሆነው እስከ ሁለቱ ምስክሮች ትንሣኤ ድረስ ያለውን ይሸፍናል።

የጊዜውን ቅደም ተከተል ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1ኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

ጌታችን ኢየሱስ ስለ ዓለም ሁሉ ኃጢአት ከሞተ በኋላ በወጎኒ ለሚገኙት ነፍሳት (ለብሉይ ኪዳን ቅዱሳን) ወንጌልን ሰብኮላቸው በ3ኛው ቀን ከሙታን ተነሥቷል /1ኛ ጴጥ. 3:18–19፤ ማር. 16:6/።

«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆነ ተነሥቷል» /1ኛ ቆሮ. 15:20/።

2ኛ ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ

የተነሡት ቅዱሳን

ጌታችን ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በቡሉይ ኪዳን ከሞቱት ቅዱሳን ከመቃብር ወጥተው (በትንሣኤው ተነሥተው) ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ለብዙዎች ታይተዋል።

> *«...ዓለቶችም ተሰነጠቁ፤ መቃብሮችም ተከፈቱ። ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ። ከትንሳኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ» /ማቴ. 27:52-53።*

3ኛ ቤተ ክርስቲያን

ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ በፊተኛው ትንሣኤ ውስጥ የመጀመሪያዋ ተነሺና ተነጣቂ ቤተ ክርስቲያን ነች።

ቤተ ክርስቲያን የምትነጠቅበት ጊዜ በራእይ 4:1 ላይ ከመጨረሻው 7 ዓመት በፊት፥ ማለትም ከተቃዋሚው ክርስቶስ ዘመን በፊት ነው።

ይህን የቤተ ክርስቲያን ጊዜ እንደሚከተለው እንመለከታለን፤

> *«እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለንው ጻፍ» /ራዕይ 1:19/።*

በዚህ ስፍራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዮሐንስ እንዲጽፍ ሦስት የተለያዩ ክፍሎችን (Parts) ሲነግረው እንመለከታለን።

1. ያየኸውን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ቃል ለዮሐንስ ሊነግረው ሲል ዮሐንስ ጌታን በታላቅ ክበር አይቶት በመደንገጥ እንደ ሞተ ሰው በድን ሆኖ ነበር። ጌታም ካበረታታው በኋላ ይህን ያየውን እንዲጽፍ ነገረው። «ያየኸውን ጻፍ» ለሚለው የጌታ ትእዛዝ ዮሐንስ ምላሽ ለመስጠትና

የተባለውን ለመጻፍ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ያየው የጌታን ክበር ብቻ ነበር።

2. አሁንም ያለውን፤ ጌታ ይህን ቃል ሲናገር ይናገር በነበረበት ወቅት የነበረው ዘመን የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነበር። ይህንም በሚመለከት ከራእይ 2፡1 – ራእይ 3፡22 ድረስ ለቤተ ክርስቲያን የተጻፈውን መልእክት እናገኛለን።

3. ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን፤ ጌታ ይህን ሲል በምዕራፍ 2 እና 3 ላይ ለቤተ ክርስቲያን መልእክቱን፥ ተግሣጹን፥ ምክሩን፥ ቅሬታውን፥ ማበረታታቱን፥ ማጽናናቱን ካስተላለፈ በኋላ የእያንዳንድን ቤተ ክርስቲያን መልእክት ምክንያታዊ በሆነ ቃል ኪዳን ዘግቶ በምዕራፍ 4፡1 ላይ አዲስ ራእይ ይጀምራል።

> *«ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ» /ራይይ 2፡7/።*

ያም «ይሆን ዘንድ ያለውን» በማለት ለዮሐንስ የነገረውን ነው። «ይሆን ዘንድ ያለው» የተባለው ከቤተ ክርስቲያን ዘመን በኋላ የሚከሰተው ነው።

ዮሐንስ በምዕራፍ 4፡1 ላይ መልእክቱን ሲጀምር በምዕራፍ ሁለት እና ሦስት ውስጥ የተጠቀሰውንና ያኔ የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ዘመን በመቋጨት ስለ አዲስ ራእይ ይናገራል።

> *«ከዚህም በኋላ አየሁ። እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ።»*

በዚህን ጊዜ ጌታ ለዮሐንስ በሰማይ የተከፈተ ደጅ አሳይቶ ከላይ የተጠቀሰውን ቃል በመናገር ከዚያ በኋላ በዓለም ሁሉ ስለሚሆነው መከራ ሊያሳውቀው ወደሚቀጥለው ራእይ ሊያሸጋግረው እንመለከታለን።

የዞን 4 ሕዝብ ግንኙነት መምሪያ
Zone 4 Public Relations

በሰማይ የታየው የተከፈተ ደጅ የተከፈተው ለማን ነው?

ጌታ ለቤተ ክርስቲያን በመከራ ውስጥ እንደሚታልፍ ቃል ገብቶላታል።

> *«የትዕግሥቴን ቃል ስለጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ» /ራዕይ 3፡10/።*

ቤተ ክርስቲያን ዘመኗን በራእይ 3 መጨረሻ ላይ ጨርሳ በራእይ 4፡1 በተከፈተው ደጅ ወደ ጌታ ተነጥቃለች። ይህንን እውነት የሚገልጹ ሌሎችም ተጨማሪ ማስረጃዎች ከእግዚአብሔር ቃል አብረን እንመለከታለን።

1. በራእይ 4፡1፥ «ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ» ይላል። «ከዚህ በኋላ» ሲል ከምን በኋላ ማለት ነው? ዮሐንስ ከዚህ ቃል በፊት በራእይ ካያቸው ነገሮች ሁሉ በኋላ ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ከራእይ 2፡1 ጀምሮ እስከ ራእይ 3፡22 ድረስ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ወደ 19 ጊዜ ሲጻፍ፥ ከዚያ በኋላ ግን ከራእይ 4፡1 ምሥጢራዊ አገላለጽ በስተቀር እስከ ራእይ 22፡15 ድረስ ቤተ ክርስቲያንን በምሥጢራዊም ሆነ በግልጽ አጠራር ተጠቅሳ አናገኛትም። ከዚያ በኋላ የምናገኛት ከመከራው ዘመንና ከሺህ ዓመቱ የክርስቶስ ዘመን በኋላ በራእይ 22፡16–21 ባለው የዮሐንስ ራእይ የማጠቃለያ ክፍል ውስጥ ብቻ ነው።

እንዲሁም እስራኤልን በራእይ 2 እና 3 ውስጥ የትም ስፍራ አናገኛትም። ከራእይ 4፡1 በኋላ ግን በምሥጢራዊና በቀጥተኛ አጠራር ተጠቅሳ በብዙ ስፍራዎች እናገኛታለን። ስለዚህ የእስራኤልንና የቤተ ክርስቲያንን ዘመን በሁለት ከፍለን ስንመለከተው፥

- ራእይ 2 እና 3 – ቤተ ክርስቲያን
- ራእይ 4፡2– ራእይ 19 እስራኤል ሆነው እናገኛቸዋለን።

2. በዳንኤል 9:24-27 የተጠቀሰው 70ኛው ሳምንት በማቴዎስ 24 እና 25 እና በዮሐንስ ራእይ 6-19 የተጠቀሱት የመከራ ዘመናት የሚመለከቱት እስራኤልንና አሕዛብን እንጂ ቤተ ክርስቲያንን አይደለም።

> «ጠይቁ፥ ወንድ ይወልድ እንደሆነ ተመልከቱ ስለ ምን ሰው ሁሉ እንደ ወላጅ እጅን በወገቡ ላይ አድርጎ ፊቱም ሁሉ ወደ ጥቁረት ተለውጦ አየሁ? ወዮ! ያ ቀን ታላቅ ነውና እርሱንም የሚመስል የለምና ያ የያዕቆብ መከራ ዘመን ነው... » /ኤር. 30:6-7/።
>
> «ዓመፃን ይጨርስ ኃጢአትንም ይፈጽም በደልንም ያስተሰርይ የዘላለምንም ጽድቅ ያገባ፥ ራእይንና ትንቢትን ያትም ቅዱስ ቅዱሳኑንም ይቀባ ዘንድ በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቀጥሮአል። ስለዚህ እወቅ አስተውልም። ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሢሑ ድረስ ሰባት ሱባዔና ሰድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል። እርስዋም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች። ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሢሑ ይገደላል። በእርሱም ዘንድ ምንም የለም። የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ። ፍጻሜውም በጎርፍ ይሆናል። እስከ መጨረሻውም ድረስ ጦርነት ይሆናል። ጥፋትም ተቀጥሮአል። እርሱም ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባዔ ያደርጋል። በሱባዔውም እኩሌታ መሥዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል። በርኩሰትም ጫፍ ላይ አጥፊው ይመጣል። እስከ ተቆጠረውም ፍጻሜ ድረስ መቅሠፍት በአጥፊው ላይ ይፈስሳል» /ዳን. 9:24-27/።

ሰባው ሱባዔ የተቀጠረው ለእስራኤል ነው።

«በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቀጥሮአል» /ዳን. 9:24/። ይህን በዝርዝር ከማየታችን በፊት «ሱባዔ» የሚለው ቃል ምን አሳብ እንደሚያስተላልፍ እንመለከታለን። «ሱባዔ» የሚገልጸው ሰባትን ነው።

በዳንኤል 9:25 ላይ ስለተጻፈው 62 ሱባዔ ቁጥር 26 ላይ «ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ» በማለት ሱባዔ ሰባትን

እንደሚያመለክት ያሳያል። ይህ ስለ ሱባዔ የሚገልጸው 70 ጊዜ ሰባት ዓመታትን ነው።

ኢየሩሳሌምን ለመጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አለቃው መሢሕ ድረስ ሰባት ሱባዔና (49 ዓመታትና) ስድሳ ሁለት ሱባዔ (434 ዓመታት) ይሆናል። ስድሳ ሁለት ሱባዔ ማለትም ኢየሩሳሌምን የመጠገንና የመሥራት ጊዜ ካለቀ ከ434 ዓመታት በኋላ መሢሕ ይገደላል።

እነዚህ ዓመታት መቼ እንደነበሩ በትክክለኛው ቁጥር ማስቀመጥ ባይቻልም 404 ዓ.ዓ. አካባቢ ኢየሩሳሌምን የመጠገኑ ሥራ ቢያልቅ፥ ከ62 ሱባዔ ማለትም ከ434 ዓመታት በኋላ በ30 ዓ.ም. መሢሑ ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተገድሏል።

ከመሢሑ መሞት ከ69ኛው ሱባዔ መጨረሻ ጀምሮ እስከ 70ኛው ሱባዔ መጀመሪያ ድረስ ባለው ጊዜ መካከል የቤተ ክርስቲያን ዘመን አለ። ይህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የእስራኤል ዘመን ስላልሆነ በሱባዔዎቹ ውስጥ አይካተትም። የእስራኤል ዘመን በ69 ሱባዔ ያቆምና እንደገና ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በኋላ በ70ኛው ሱባዔ ይጀምራል። ይኸ የመጨረሻው 70ኛው ሱባዔ (ሰባት ዓመታት) የሚመጣው አለቃ (ተቃዋሚው ክርስቶስ) ከእስራኤል ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን የሚያደርግበትና በሱባዔውም አጋማሽ ላይ ቃል ኪዳኑን የሚያፈርስበት የመከራው ዘመን ነው /ዳን. 9:27/። ስለዚህ ይህ የመጨረሻው ዘመን 70ኛው ሱባዔ የእስራኤልና የአሕዛብ ዘመን እንጂ የቤተ ክርስቲያን ዘመን አይደለም።

ሰባቱ የመከራ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን እንደማያገኛት ከጌታ ኢየሱስ የጸና የተስፋ ቃል አለን። ሉቃስ 21:34–36 እንዲህ ይላል፤

> *«ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ስለትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ በምድር ሁሉ ላይ በሚቀመጡ ሁሉ እንደወጥመድ ይደርስባቸዋልና እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁልጊዜ ትጉ።»*

እንዲሁም በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፥1–11 እና በሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከራእይ 6–19 ያለው የመከራ ዘመን እንደማያገኘን የጸና የተስፋ ቃል አለን።

በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡9–11 እግዚአብሔር በጌታችን በኢየሩስ ክርስቶስ መዳንን እንድናገኝ እንጂ ለቁጣ እንዳልመረጠን ይናገራል።

በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡18ም እርስበርሳችን በተሰጠን የተስፋ ቃል አንዱ ሌላውን፥ «ወንድሜ ሆይ፥ አይዞህ ጌታ ይመጣል፤ ወደ እርሱም ይወስደናል። እህቴ ሆይ፥ አይዞሽ፤ ጌታ ይመጣል። ወደ እርሱም ወስዶ ለዘላለም በዕረፍትና በደስታ ያኖረናል» እያልን እንድንጽናና ይነግረናል። እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን በመከራ ውስጥ የምታልፍ ከሆነ ቅዱሳን አንዱ ሌላውን እንዴት ነው የሚያጽናኑት?

በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡6–8 የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ከራእይ 6–19 ከሚሠራው ከተቃዋሚው ክርስቶስና ከዳንኤል 70ኛው ሳምንት በፊት እንደሆነ በሚገልጽ ሁኔታ በመከራው ዘመን የሚገለጠው የዓመፅ ሰው ምሥጢር አሁን እንዳይገለጥ የምትከለክል ቤተ ክርስቲያን እንዳለች ይነገራል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን የምትነጠቅበትና የዓመፅ ምሥጢር ተገልጦ የሚሠራበት ዘመን እንደሚመጣ ይጠበቃል።

> *«በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ። የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ። በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል»/2ኛ ተሰ. 2፡6፥ 8/።*

አሁን ያለንበት የቤተ ክርስቲያን ዘመን የጸጋና የምሕረት ዘመን ነው። የመጨረሻው ዘመን ደግሞ በማጎተሞች፥ በመለከቶችና በጽዋዎች የሚገለጥ ታላቅ መከራ የሚነግሥበት የቁጣና የፍርድ ዘመን ነው። ዛሬ ጌታ በቃሉና በነቢያት እንዲሁም በሌሎች መንገዶች ያጽናናናል፤ ይመክረናል፤ ይገሥጸናል፤ ያበረታታናል። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ስም ወደ 19 ጊዜ ያህል በተጠቀሰበት በራእይ ምዕራፍ 2 እና 3 ባለው ክፍል የምንመለከተውም ይህንኑ ነው። የፍርድ ዘመንም ከጸጋ ዘመን ጋር በምንም የማይገናኝና የተለየ ነው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች ከእግዚአብሔር ቃል ስንመለከት፥ ቤተ ክርስቲያን በመከራው ዘመን ውስጥ እንደማታልፍና ከመከራው ዘመን በፊት እንደምትነጠቅ እንረዳለን። እንግዲህ በመከራው ዘመን ውስጥ የማታልፈው ቤተ ክርስቲያን በራእይ 4፡1 ካልተነጠቀች ሌላ የመነጠቂያ ስፍራ አናገኝላትም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በራእይ 4፡1 ላይ ተነጥቃለች። በሰማይ ተከፍቶ የታየውም ደጅ ቤተ ክርስቲያን ትገባበት ዘንድ ነው።

4ኛ 144,000 አይሁዶች

እነዚህ ከመጀመሪያው 3 ተኩል ዓመት መጨረሻ ላይ ከእስራኤል የሚድኑና የሚነጠቁ ናቸው /ራእይ 7፡1–8፤ 12፡5፤ 14፡1–5፤ ዳን. 12፡1/።

> *«አየሁም እነሆም በጉ በፅዮን ተራራ ቆም ነበር። ከእርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም በግምባራቸው የተጻፈላቸው መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ» /ራዕይ 14፡1/።*

5ኛ በታላቁ የመከራ ዘመን የሚድኑ ቅዱሳን

እነዚህ ቅዱሳን በሰባቱ የመከራ ዘመን የሚያልፉና በዚያ ውስጥ ደኅንነትን የሚጎናጸፉ ናቸው። እነዚህ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ዘመን አማኞች ያልነበሩና ያልዳኑ ነበሩ። ያኔ ደኅንነትን አግኝተው ቢሆን ኖሮ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ይነጠቁ ነበር።

እነዚህ ሰዎች በመከራው ዘመን ጌታን አምነው የሚድኑ፥ ለአውሬውና ለምስሉ የማይሰግዱ፥ ምልክቱንም በግምባራቸውና በቀኝ እጃቸው የማይቀበሉ ናቸው። ከዚህም በላይ ጋለሞታይቱ በኃይል በምትሰለጥንበት በአሥሩ ነገሥታት መንግሥትና በተቃዋሚው ክርስቶስ የመጀመሪያው ሦስት ዓመት ተኩል ዘመን ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር ስደትና ግድያ የሚደርስባቸው ናቸው። ተቃዋሚው ክርስቶስ ጋለሞታይቱን ገድሎና ከእስራኤል ጋር ያለውን ቃል ኪዳን

አፍርሶ ራሱ እንዲመለክ ሰዎችን በሚያስገድድበት በመጨረሻው ሦስት ዓመት ተኩል ውስጥ ለአውሬውና ለምስሉ ባለመስገዳቸውና ምልክቱን በግምባራቸውና በቀኝ እጃቸው ላይ ባለመቀበላቸው በአውሬው የሚገደሉና የሚሰደዱ ናቸው።

> «አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ። በታላቅ ድምፅም እየጮሁ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም? ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ። ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው። እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀሮቻቸውና የወንድሞቻቸው ቁጥር እስኪፈጸም ደረስ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው» /ራእይ 6:9-11/።

ከዚህ በኋላ የእነዚህን ሰዎች ነፍሳት የምናየው በሰማይ ላይ ነው /ራእይ 7:9-17/። እነዚህ ከበጉ ጋር በምድር ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።

> «ዙፋኖችንም አየሁ፥ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው። ስለ ኢየሱስ ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ» /ራእይ 20:4/።

6ኛ ሁለቱ ምስክሮች

> «በመቅደሱ ውጪ ያለው አድም ለአሕዛብ ተሰጥቶአልና ተወው፤ አትለካውም። እነርሱም አርባ ሁለት ወር የተቀደሰችውን ከተማ ይረግጡአታል። ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ሰድስ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ» /ራእይ 11:2-3/።

እነዚህ ሁለት ምስክሮች ሰዎች ናቸው። ነቢያትም ናቸው።

በመጨረሻው 42 ወራት መጀመሪያ ላይ ተነሥተው ለ3 ዓመት ተኩል ትንቢት ይናገራሉ። ሰዎችንም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይመልሳሉ። እነዚህ ሁለት ምስክሮች አሁን በእግዚአብሔር ዘንድ ያሉ ናቸው። ስለዚህ ዘካርያስ በትንቢቱ ሲናገር እንዲህ ይላል፤

> «እኔም መልሼ በመቅረዙ በሰተቀኝና በሰተ ግራ ያሉ እነዚህ ሁለት የወይራ ዛፎች ምንድናቸው? አልሁት። ሁለተኛም መልሼ፦ በሁለቱ የወርቅ ቧንቧም አጠገብ ሆነው የወርቁን ዘይት የሚያፈሰሱ እነዚህ ሁለት የወይራ ቅርንጫፎች ምንድናቸው? አልሁት።
>
> «እርሱም፦ በምድር ሁሉ ጌታ አጠገብ የቆሙት ሁለቱ የተቀቡት እነዚህ ናቸው አለኝ» /ዘካርያስ 4፡11-14/።

በራእይ 11፡4 ላይም የእግዚአብሔር ቃል ስለ እነዚህ ሁለት ምስክሮች ሲናገር፥ «እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለት መቅረዞች ናቸው» ይላል። ዘካርያስ ይህን ትንቢት የተናገረው ከክርስቶስ ልደት 500 ዓመት በፊት ገደማ ነው። ዘካርያስ እነዚህን ሰዎች በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት እንዳሉ ስለተናገረ፥ ሰዎቹ ቢያንስ ከዘካርያስ ትንቢት በፊት ጀምሮ በሰማይ በእግዚአብሔር አጠገብ እንዳሉ እንረዳለን። እነዚህ ሁለት ሰዎች ወደ ምድር መጥተው ምስክርነታቸውን ከጨረሱ በኋላ በአውሬው እንደሚገደሉ በእግዚአብሔር ቃል ተጽፎአል /ራእይ 11፡7-10/።

ስለዚህ እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው?

1. እነዚህን ሰዎች ከዚህ በፊት ሞተው ነፍሳቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ካሉት ቅዱሳን ሁለቱን ልናደርጋቸው አንችልም። ለሰው አንድ ጊዜ ሞት ከዚያም ፍርድ አለ እንጂ በምድር ላይ ዳግም መሞት አይቻልም። እነዚህ ሰዎች ግን ወደ ምድር መጥተው ምስክርነታቸውን ከጨረሱ በኋላ በአውሬው ይገደላሉ /ራእይ 11፡7/።

2. ክርስቶስ የትንሣኤ በኩር እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። እነዚህን ሰዎች ከዘካርያስ ዘመን በፊት ካለፉት ቅዱሳን ሁለት ናቸው ካልን፥ በዘካርያ ዘመን ሁለቱ በእግዚአብሔር አጠገብ ታይተዋልና በትንሣኤ አካል

በእግዚአብሔር ፊት በመሆን ክርስቶስን ስለሚቀድሙ በኩር እነርሱ ሊሆኑ ነው።

እውነቱ ግን ክርስቶስ በወጎኒ ለነበሩት ነፍሳት ስብኮላቸው ነጻ እስኪያወጣቸው ድረስ ከክርስቶስ በፊት የነበሩ ቅዱሳን በወጎኒ ነበሩ እንጂ በእግዚአብሔር አጠገብ አልነበሩም። በኩሩ ክርስቶስ ነው። ከዚያም በመምጣቱ ለእርሱ የሆኑት ናቸው /1ኛ ቆሮ. 15:23/። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ከዚህ በፊት ሞተው ከነበሩት ቅዱሳን ሁለቱን ሊሆኑ አይችሉም።

እነዚህን ሁለት ሰዎች ሊሆኑ የሚችሉት፤

1. ነቢይ የሆኑ

2. በሥጋ ሞትን ያልቀመሱ

3. ከዘካሪያስ ትንቢት በፊት በእግዚአብሔር ዘንድ የነበሩ መሆን አለባቸው።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ነቢያት ሆነው ሞትን ያላዩና ከዘካርያስ ትንቢት በፊት የኖሩት ሄኖክና ኤልያስ ብቻ ናቸው። እነዚህን ሁለት ሰዎች መሆን የሚችሉትም ሄኖክና ኤልያስ ብቻ ናቸው።

1. ሁለቱም ነቢያት ነበሩ፤

«ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ፦ እነሆ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ በኃጢያተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢያተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም ኃጢያተኞች በእርሱ ላይ ስለተናገሩ ስል ጭከና ነገር ሁሉ ኃጢያተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ» /ይሁዳ 14-15/።

«ኤልያስም ሕዝቡን አለ፦ ከእግዚአብሔር ነቢያት እኔ ብቻ ቀርቻለሁ...» /1ኛ ነገሥ. 18:22/።

2. ሁለቱም በሥጋ ሞትን አላዩም፤

«ሄኖክ ሞትን እንዳያይ በእምነት ተወሰደ፤ እግዚአብሔርም ስለወሰደው አልተገኝም» /ዕብ. 11:5/።

«እነሆ የእሳት ሰረገላና የእሳት ፈረሶች በመካከላቸው ገብተው ከፈሏቸው። ኤልያስም በአውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ወጣ» /2ኛ ነገ. 2:11/።

3. ሁለቱም ከዘካርያስ ትንቢት ዘመን በፊት በእግዚአብሔር ዘንድ ነበሩ፤

«ሄኖክም ኣካሄዱን ከእግዚኣብሔር ጋር ኣደረገ... ሄኖክም ኣካሄዱን ከእግዚኣብሔር ጋር ስላደረገ ኣልተገኘም። እግዚኣብሔር ወስዶታልና... » /ዘፍ. 5:22-24/። «እንዲህም ሆነ እግዚኣብሔር ኤልያስን በአውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ሊያወጣው በወደደ ጊዜ ኤልያስ ከኤልሳዕ ጋር ከጌልጌላ ተነሣ» /2ኛ ነገሥ. 2:1/።

ከዚህ በተጨማሪም ነብዩ ኤልያስ በመጨረሻው ዘመን ይህ አገልግሎት እንሚኖረው በእግዚአብሔር ቃል ተጽፎአል።

«እነሆ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚኣብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የልጆችን ልብ ወደ አባቶች ይመልሰላል» /ሚል. 4:5-6/።

ከዚህ ቃል እንደምንረዳው ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር ለአገልግሎት ነቢዩ ኤልያስን እንደሚልክ ነው። ይህ የሚሆነው በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 11:3 እንደተገለጸው፥ በመጨረሻው 7 የመከራ ዘመን የመጨረሻው 3 ዓመት ተኩል ላይ ነው።

ነቢዩ ኤልያስ ከዚህ በፊት መጥምቁ ዮሐንስን ሆኖ ወደ ምድር መጥቶአል ወይ?

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ 11:14፤

«ልትቀበሉትስ ብትወዱ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነው።» እንዲሁም በማቴዎስ 17:10-12 ደቀ መዛሙርቱ፥ **«ጻፎች ኤልያስ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል ለምን ይላሉ?»**

ብለው ሲጠይቁት «ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀናል። ነገር ግን እላችኋለሁ ኤልያስ ከዚህ በፊት መጣ የወደዱትንም አደረጉበት እንጂ አላወቁትም» በማለት ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ይናገራል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ 17 ቁጥር 11 እና 12 ላይ ስለ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ነው የሚናገረው።

በቁጥር 11 ላይ ገና ስለሚመጣውና ሁሉንም ስለሚያቀናው ኤልያስ «ኤልያስ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀናል» ሲል ይናገራል። በቁጥር 12 ላይ «ነገር ግን እላችኋለሁ ኤልያስ ከዚህ በፊት መጣ። የወደዱትንም አደረጉበት እንጂ አላወቁትም» በማለት ከርሱ በፊት ስለመጣው ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ይናገራል።

አይሁድ እስከአሁን ድረስ መሢሑ እንደሚመጣና የእስራኤልን መንግሥት እንደሚመልስ ያምናሉ። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትም መሢሑ ለእስራኤል መንግሥትን እንደሚመልስ ይጠባበቁ ስለነበር፥ የሚመጣው መሢሕ ኢየሱስ መሆኑን ካወቁ በኋላ ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት የጠየቁት የመጨረሻ ጥያቄ ስለ እስራኤል መንግሥት መመለስ ነበር።

> *«እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ፦ ጌታ ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው ጠየቁት» /የሐዋ. 1፡6/።*

ክርስቶስም ሲመልስ የእስራኤል መንግሥት መመለስ እነርሱ እንደጠበቁትና እንደጠየቁት በመጀመሪያው የክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ጊዜ ሳይሆን በዳግም ምጽአቱ ጊዜ መሆኑን፥ ያንን ቀን ደግሞ ማንም ሊያውቅ እንዳልተሰጠው በሚገልጥ ሁኔታ፥ «አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም» ብሎ ሲመልስላቸው እናያለን። አይሁድ ከመሢሑ መምጣትና ከእስራኤል መንግሥት መመለስ አስቀድሞ ነቢዩ ኤልያስ እንደሚመጣም ያምናሉ። ስለዚህም ነው ጻፎች ነቢዩ ኤልያስ አስቀድሞ ይመጣል ብለው የሚናገሩት።

አይሁድ በዳንኤል 9፡24-27 የተጻፈውን ሰባውን ሱባዔ የሚያምኑትና የሚጠብቁት ቢሆንም፥ በስድሳ ዘጠነኛውና በሰባኛው ሱባዔ መካከል ያለውን የቤተ ክርስቲያን ዘመን አያምኑም፤ አይጠብቁትም፤ አይቀበሉትም። ስለዚህም ነው

እነርሱ የሚጠብቁትን የእስራኤልን መንግሥት ለመመለስ ሳይሆን፥ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ለመሞት፥ ለዓለም ሁሉ መንግሥትን ለመመለስና ለአባቱ መንግሥትና ካህናት እንድንሆን /ራእይ 1፡6/ ሊያደርገን የመጣውን ኢየሱስን ያልተቀበሉት። ነገር ግን ክርስቶስ በዳግም ምጽአቱ አይሁድ እንደሚጠብቁት፥ ነቢያትም እንደተናገሩት፥ ለእስራኤል መንግሥትን ይመልሳል። በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ /ኢሳ. 14፡1-2/፥ ጌታ የእስራኤልን ኃጢአት ይቅር ይላል /ዘካ. 13፡1፤ ኤር. 50፡20/። ለኢየሱስም ያለቅሱለታል /ዘካ. 12፡10/። የኤልያስ አስቀድሞ መምጣት ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፤

ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ 17፡12፥ «ኤልያስ ከዚህ በፊት መጣ። የወደዱትንም አደረጉበት እንጂ አላወቁትም» ብሎ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ እንደተናገረው፥ መጥምቁ ዮሐንስ በኤልያስ መንፈስና ኃይል መጥቷል።

የእግዚአብሔር ቃል በመጨረሻው ዘመን ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት ስለሚመጣው ኤልያስ የሚከተለውን ይናገራል፤

> *«እነሆ፥ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል»* ይላል /ሚል. 4፡5-6/።

በእግዚአብሔር ቃል ላይ «ታላቁ ቀን» ተብሎ የተገለጸው ሊመጣ ያለው የመጨረሻው ዘመን እንደሆነ ግልጽ ነው። «ወዮ! ያ ቀን ታላቅ ነውና እርሱንም የሚመስል የለምና ያ የያዕቆብ መከራ ዘመን ነው...» /ኤር. 30፡7/።

እንዲሁም ከመጀመሪያው የክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት በፊት ስለ መጣው ዮሐንስ የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር «እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል» ይላል /ሉቃስ 1፡17/።

እንግዲህ መጥምቁ ዮሐንስ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች በመመለስና ከክርስቶስ ፊት ቀድሞ የጌታን መንገድ በማዘጋጀት፥ አገልግሎቱ በመጨረሻው ዘመን ከሚመጣው

ከኤልያስ ጋር የሚመሳሰል መንፈስና ኃይል ያለው ነቢይ እንጂ ራሱ ኤልያስ አለነበረም።

መጥምቁ ዮሐንስ ራሱ ኤልያስ እንዳልሆነ ተናግሯል።

> «እንኪያስ ማነህ? ኤልያስ ነህን? ብለው ጠየቁት። አይደለሁም አለ። ነቢዩ ነህን? አይደለሁም ብሎ መለሰ። እንኪያስ ማን ነህ? ለላኩን መልስ እንድንሰጥ ስለ ራስህ ምን ትላለህ? አሉ። እርሱም፦ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ› /ዮሐ. 1፡21-23፤ ኢሳ. 40፡3/።

ሄኖክና ኤልያስ

ዘካርያስ ትንቢትን ከተናገረበት ዘመን ቀደም ብለው ሞትን ሳይቀምሱ በእግዚአብሔር ፊት የነበሩ ነቢያት ሄኖክና ኤልያስ ናቸው። እነርሱ ደግሞ የሚሞተው ገላቸው የማይሞተውን ለብሶ አልተለወጠም። እንዲህ ቢሆን ኖሮ፤

1ኛ የማይሞተው የትንሣኤ አካል እንደገና ሊሞት ስለማይችል፥ ወደ ምድር ከመጡ በኋላ አውሬው ሊገድላቸው ባልተቻለው ነበር /1ኛ ቆሮ. 15፡53-55/።

2ኛ የተለወጡ ቢሆን ኖሮ በተለወጠ ዘላለማዊ አካል በመነጠቅ ከክርስቶስ ይቀድማሉና ክርስቶስ በኩር ባልሆነ ነበር። ነገር ግን እነዚህ ሁለት ሰዎች አሁንም በሰማይ ያሉት በዚያው አካላቸው ነው። በመጨረሻም ዘመን ወደ ምድር መጥተው ምስክርነታቸውን ከጨረሱ በኋላ ሞተው በትንሣኤ የማይበሰብሰውን አካል ለብሰው ወደ ሰማይ ይወጣሉ።

> «ከሦስት ቀን ተኩልም በኋላ ከእግዚአብሔር የወጣ የሕይወት መንፈስ ገባባቸው፤ በእግሮቻቸውም ቆሙ። ታላቅ ፍርሃት በሚመለከቱት ላይ ወደቀባቸው። በሰማይም፦ ወደዚህ ውጡ የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ሰሙ። ጠላቶቻቸውም እየተመለከቷቸው ወደ ሰማይ በደመና ወጡ» /ራእይ 11፡11-12/።

በዚህ በፊተኛው ትንሣኤ፥ ክርስቶስ የበኩርነቱን ስፍራ ይይዛል። ከዚያም እነዚህ የትንሣኤ ልጆች ተራ በተራ ከሺህ

የመጨረሻው መጨረሻ

ዓመቱ የክርስቶስ መንግሥት መጀመር በፊት ይነሣሉ። በመጨረሻም ሁለቱ ምስክሮች ከሙታን በመነሣት የፊተኛውን ትንሣኤ ያጠቃልላሉ።

የዞን 4 ሕዝብ ቤተ መጻሕፍት
Zone 4 Public Library

4

ተቃዋሚው ክርስቶስ

«ልጆች ሆይ፥ መጨረሻው ሰዓት ነው። የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደ ሰማችሁ አሁን እንኳን ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል። ስለዚህም መጨረሻው ሰዓት እንደሆነ እናውቃለን»/1ኛ ዮሐ. 2፤18/።

«ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው። ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል። አሁንም እንኳ በዓለም አለ»/1ኛ ዮሐ. 4፤3/።

«ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና፥ እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምኑ ናቸው። ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚው ነው»/2ኛ ዮሐ. 7/።

ከዚህ የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደምንረዳው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደተገለጠ የማያምኑ የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ የሚሠራባቸው አሳቾች ተነሥተዋል፤ አሁንም እንኳን

በዓለማችን አሉ፤ ወደፊትም ይነሣሉ። ይሁንና፥ በመጨረሻው ዘመን የሚገለጸው ተቃዋሚው ክርስቶስ /አውሬው/ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ከሌሎች ሁሉ የላቀ ስፍራ ተሰጥቶት እንመለከታለን። ይኸው የክርስቶስ ተቃዋሚ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በሚከተሉት በርካታ ስሞች ተጠርቷል፤

1. ፈተ ጨካኝ ንጉሥ /ዳን. 8፤23/

2. የባቢሎን ንጉሥ /ኢሳ. 14፤4/።

3. አሦር /ኢሳ. 31፥8፤ ሚክ. 5፤6/።

4. የሰሜን ንጉሥ /ዳን. 11፤7/።

5. አውሬው /ዳን. 7፤11፤ ራእይ 13፤1–2፥ 4፥ 12፥ 14–18/።

6. የዓመፅ ሰው /2ኛ ተሰ. 2፡3፥ 8–10/።

7. የጥፋት ልጅ /2ኛ ተሰ. 2፡3/።

8. ክፉው /ኢሳ. 11፡4/።

9. አጥፊው /ኢሳ. 16፡4/።

10. የሞሳህና የቶቤል አለቃ ጎግ /ሕዝ. 38፡2–3/።

11. ትንሹ ቀንድ /ዳን. 7፡8/።

12. የሚመጣው አለቃ /ዳን. 9፡26–27/።

የዮሐንስ ሁለት አውሬዎችን እንደተመለከተ ከዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 13 እናያለን፤ ከነዚህም ሁለት አውሬዎች አንደኛው የወጣው ከባሕር ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ከምድር ነበር። ስለ መጀመሪያው አውሬ የሚከተለው ተጽፎ ይገኛል።

> *«አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፥ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፤ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ፤ ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር። እግሮቹም እንደ ድብ እግሮች አፉም እንደ አንበሳ አፍ ነበሩ፤ ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው»* /ራእይ 13፡1–2/።

በመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃቀም፥ ባሕር በምድር የሚኖሩ የብዙ ሰዎች /ማለትም አሕዛብ/ ተምሳሌት ነው። በመሆኑም፥ ይህ ከባሕር የወጣው አውሬ ከአሕዛብ መካከል እንደሚነሣ ግልጽ ነው። በራእይ 17፡1 ላይ የጌታ ቃል ስለ ታላቂቱ ጋለሞታ ሲናገር፥ «... ና በብዙም ውኃዎች ላይ የተቀመጠችውን የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ» ይላል። ስለዚሁ የብዙ ውኃዎች ምንነት በቁጥር 15 ሲያብራራ፥ «አለኝም ጋለሞታዪቱ የተቀመጠችባቸው ያየሃቸው ውኃዎች ወገኖችና ብዙ ሰዎች አሕዛብም ቋንቋዎችም ናቸው» ይላል።

ወደ ዳንኤል 7፡3 ስንገልጥ ደግሞ፥ «አራት ታላላቅ አራዊት ከባሕር ወጡ» ይላል። ቀጥሎም በቁጥር 17፥ «እነዚህ አራቱ ታላላቅ አራዊት ከምድር የሚነሡ አራት ነገሥታት ናቸው» ሲል ከባሕር የወጡት አራዊት ከምድር የሚነሡ ነገሥታት መሆናቸውን ይገልጻል። ስለዚህ ይህ ባሕር በምድር የሚኖሩ የብዙ ሕዝቦች ተምሳሌት ወይም ምሳሌ ነውና ዮሐንስ ከባሕር ሲወጣ ያየው አውሬ ከምድር አሕዛብ መካከል የሚወጣው ሰው ነው። ይህ አውሬ በዚህች ምድር ላይ ንጉሥ ሆኖ ይነግሣል/ዳን. 7፡3፥ 17፤ ራእይ 17፡11–13/።

ተቃዋሚው ክርስቶስ ማነው?

የተቃዋሚው ክርስቶስ ማንነት ከአወጣጡ ጀምሮ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተገልጾአል። ከባሕር የሚወጣው አውሬ እንደሚከተለው ተገልጾ እናያለን።

- አሥር ቀንዶች አሉት/ራእይ 13፡1፤ 17፡3፥ 7/።
- ሰባት ራሶች አሉት/ራእይ 13፡1፤ 17፡3፥ 7/።
- ነብር ይመስል ነበር/ራእይ 13፡2/።
- በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበር/ራእይ 13፡1/።

ይህ አውሬ ዳንኤል በባቢሎን ንጉሥ በብልጣሶር በመጀመሪያው ዓመት በአልጋው ላይ ሆኖ በሕልምና በራእይ ያያቸውን ከባሕር የወጡ አራት አራዊትን ይመስላል።

- የመጀመሪያዪቱ አንበሳ ትመስል ነበር/ዳን. 7፡4/።
- ሁለተኛዪቱ ድብ ትመስል ነበር/ዳን. 7፡5/።

- ሦስተኛዪቱ ነብር ትመስል ነበር/ዳን. 7:6/።
- አራተኛዪቱም የምታስፈራና የምታስደነግጥ፥ እጅግ የበረታች፥ ታላላቅም የብረት ጥርሶች የነበሩአት አውሬ ነበረች/ዳን. 7:7/። ይህች አራተኛዪቱ አውሬ አሥር ቀንዶች ነበሩአት /ዳን. 7:7/። ከመካከላቸውም ሌላ ትንሽ ቀንድ ብቅ አለ፥ በፊት ከነበሩት ደግሞ ሦስት ቀንዶች ተነቃቀሉ፥ «እነሆም በዚያ ቀንድ ላይ እንደ ሰው ዓይኖች የነበሩ ዓይኖች፥ በትዕቢትም የሚናገር አፍ ነበሩበት»/ዳን. 7:8/።

ዳንኤል በሕልምና በራእይ ያያቸው እነዚህ የተለያዩ አራዊት ከባሕር የወጡት በየተራ ተከታትለው ነበር። ስለሆነም፥ አራዊቱ ከምድር በየተራ የሚነሡትን አራት ነገሥታት የሚያመለክቱ ናቸው /ዳን. 7:17/።

እነዚህ አራት ነገሥታት እነማናቸው?

እነዚህ በወቅቱ በምድር ላይ ገናና ከነበረው ከባቢሎን መንግሥት ጀምሮ፥ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብና ምድር የሆነችውን እስራኤልን በመቃወም በዓለም ላይ በየተራ የተነሡ ታላላቅ መንግሥታት ናቸው።

- አንበሳ የሚመስለው አውሬ የባቢሎንን መንግሥት ያመለክታል።
- ድብ የሚመስለው አውሬ የሜዶንና ፋርስ መንግሥት ተምሳሌት ነው።
- በነብር የተመሰለው የግሪክ መንግሥት ነው።
- የምታስፈራውና የምታስደነግጠው አውሬ የሮምን መንግሥት ታመለክታለች።

ከሮም መንግሥት በኋላ ከውስጡ የሚወጡ አሥር መንግሥታት ይነሣሉ።

> *«አራተኛዪቱ አውሬ በምድር ላይ አራተኛ መንግሥት ትሆናለች። እርሱም ከመንግሥት ሁሉ የተለየ ይሆናል። ምድሪቱንም ሁሉ ይበላል፤ ይረግጣታል፤*

ያደርቃትማል። አሥሩም ቀንዶች ከዚያ መንግሥት የሚነሡ አሥር ነገሥታት ናቸው»/ዳን. 7:23-24/።

እንደ ዳንኤል ሁሉ፥ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆርም በሁለተኛው የንግሥና ዓመቱ አንድ ሕልም አይቶ ነበር። በዚህም ሕልሙ አንድ ታላቅና ብልጭልጭልታው የበዛ ምስል ተመለከተ/ዳን. 2:1፥ 31-45/።

ምስሉም፥

- ራሱ ጥሩ ወርቅ/ቁ. 32/
- ደረቱና ክንዶቹ ብር/ቁ. 32/
- ሆዱና ወገቡ ናስ/ቁ. 33/
- ጭኖቹም ብረት/ቁ. 33/
- እግሮቹና የእግሮቹ ጣቶች እኩሉ ብረት እኩሉም ሸክላ/ቁ. 33፥ 41/ ነበሩ። ነቢዩ ዳንኤል ስለዚህ ሕልም ትርጉም ለንጉሥ ናቡከደነፆር የሚከተለውን ተናግሯል።

የወርቁ ራስ በዚያን ዘመን የባቢሎን ንጉሥ የነበረውና ሕልሙንም ያለመው ናቡከደነፆር እንደሆነና ብሩ፥ ናሱ፥ ብረቱ፥ ከፊል ብረትና ከፊል ሸክላ የሆነው ደግሞ ከእርሱ በኋላ የሚነሡ ሌሎች አራት ነገሥታት እንደሆኑ ገልጾለታል/ዳን. 1:36-43/።

በተጨማሪም፥ በራእይ ምዕራፍ 17 ታላቂቱ ጋለሞታ ስለተቀመጠችበት አውሬ የተጠቀሰውን እውነት ልብ ማለቱ መልካም ነው፤ ጋለሞታዪቱ የተቀመጠችበት አውሬ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ነበሩት። መልአኩ ለዮሐንስ እንደነገረው፥ «ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች፥ ሰባት ነገሥታትም» ናቸው።

«ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች ናቸው፤ ሰባት ነገሥታት ደግሞ ናቸው። አምስቱ ወድቀዋል፤ አንዱም አለ፤ የቀረውም ገና አልመጣም፤ ሲመጣም ጥቂት ጊዜ ሊቆይ ይገባዋል። የነበረውና የሌለውም አውሬ ራሱ ደግሞ ስምንተኛው ነው፤ ከሰባቱም አንዱ ነው፤ ወደ ጥፋትም ይሄዳል»/ራእይ 17:9-11/።

ሰይጣን ሁልጊዜ የክፋት ዓላማውን የሚያነጣጥረው የእግዚአብሔር አሳብና ክብር ሊገለጥ ባለበት ስፍራ ላይ ነው። የተቃዋሚው ክርስቶስ ዋነኛ ዓላማውም በእግዚአብሔር አሳብና ዓላማ ላይ ነው።

እነዚህም በራእይ 17፡9–10 የተጠቀሱትና ዮሐንስ ራእዩን ካየበት ጊዜ አስቀድመው የወደቁ አምስት ራሶችም /ነገሥታት/ ሆኑ ዮሐንስ ራእዩን ባየበት ዘመን የነበረው አንድ ራስ /ንጉሥ/፥ እግዚአብሔር የመረጣትን እስራኤልንና ክብሩን የገለጠባትን ኢየሩሳሌምን ተራ በተራ በየራሳቸው ዘመን አፍርሰዋል። እስራኤል የምትባለውን አገር ከምድረ ገጽ ለማጥፋት የየበኩላቸውን እኩይ እርምጃ ወስደዋል። እነዚህን እስራኤልን በየዘመናቱ ያፈራረሱትን ስድስት መንግሥታትና ወደፊት የሚመጣውን ሰባተኛውን መንግሥት ቀጥለን እንመልከታለን።

1ኛ ግብፅ

በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን ካስጨነቁትና ፀረ–እስራኤላዊ ድርጊቶችን ከፈጸሙት አገሮች አንዱ ግብፅ ነች። እስራኤላውያን ሕዝብ ሆነው በውስጧ ከተመሠረቱበት ማለትም ዮሴፍን የማያውቅ ፈረያን ከተነሣበት ጊዜ አንሥቶ ዮሐንስ ራእዩን እስካየበት ወቅት ድረስ ግብፅ የእስራኤላውያን ጠላት ሆና ቆይታለች። /ዘፍ. 15፡13–14፤ ዘጸ. 1፡7–11፤ 2፡23/። ይህችው ግብፅ ለጥፋት የተዘጋጀው የኃጢአት ዓለም ምሳሌ እንደሆነች ልብ ልንል ያሻል /ኤር. 31፡1–3/።

2. አሦር

በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን ካስጨነቁትና ፀረ–እስራኤላዊ ተግባራትን ከፈጸሙ አገሮች ሁለተኛው አሦር ነው። የአሦር መሠረቱ የኩሽ ልጅ ናምሩድ ነው።

> *«ኩሽም ናምሩድን ወለደ፤ እርሱም በምድር ላይ ኃያል መሆንን ጀመረ። እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ኃያል አዳኝ ነበረ፤ ስለዚህም፥– በእግዚአብሔር ፊት ኃያል አዳኝ እንደ ናምሩድ ተባለ። የግዛቱም መጀመሪያ በሰናዖር አገር ባቢሎን፥ ኦሬክ፥ አርካድ። ካልኔ*

ናቸው። አሦርም ከዚያች አገር ወጣ፤ ነነዌን፥ የረሆቦትን ከተማ፥ ካለህን፥ በነነዌና በካለህ መካከልም ሬሴንን ሠራ፤ እርስዋም ታላቂቱ ከተማ ናት»/ዘፍ. 10:8–12/።

«... አሦራዊውም ወደ አገራችን በገባ ጊዜ ዳርቻዎቻችንንም በረገጠ ጊዜ እርሱ ይታደገናል»/ሚክ. 5:5–6/።

አሦራውያን እስራኤላውያንን ለሰባ አምስት ዓመታት ያህል ገዝተው አስጨንቀዋቸዋል/ኤር. 50:17/።

3ኛ ባቢሎን

በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን ካስጨነቁት ታላላቅ መንግሥታት ሦስተኛው የባቢሎን መንግሥት ነው። በዳንኤል መጽሐፍ ንጉሡ ናቡከደነፆር በሕልም ባየው ታላቅ ምስል ውስጥ የመጀመሪያው የወርቁ ራስ ባቢሎንን የሚያመለክት ነበር /ዳን. 2:32፥ 38/። ዳንኤልም ከባሕር ሲወጡ ካያቸው አራት ታላላቅ አራዊት የመጀመሪያዋና አንበሳ የምትመስለው የባቢሎን መንግሥት ተምሳሌት ነች /ዳን. 7:4፥ 17/።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን የዳንኤልን መጽሐፍ በመመርኮዝ፥ በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን ያስጨነቁት መንግሥታት ቁጥር ከወርቁ ራስ /ዳን. 2:32፥ 38/፥ አንበሳ ከምትመስለው አውሬ/ዳን. 7:4/ ከባቢሎን ይጀምራል ይላሉ። ነገር ግን በዳንኤል ራእይም ይሁን በናቡከደነፆር ሕልም የተገለጹት አራት ታላላቅ መንግሥታት /ዳን. 7:17/ እና ከአራተኛው መንግሥት የሚወጡት አምስተኛው ባለ አሥር ነገሥታት መንግሥት /አሥሩ የእግር ጣቶችና ዳንኤል 2:41–43 አሥሩ ቀንዶች ዳንኤል 7:7፥ 24/፥ በሕልምና በራእይ የታዩት በባቢሎን መንግሥት ዘመን ነው።

ስለሆነም ከባቢሎን ጀምሮ ከተቃዋሚው ክርስቶስ በፊት እስከሚመጡት እስከ አሥሩ ነገሥታት መንግሥት ድረስ አምስት መንግሥታት ይቀያየራሉ። ከባቢሎን ቀደም ሲል የዳንኤል መጽሐፍ ሕልምና ራእይ ከመከሰታቸው በፊት፥ እስራኤልን የተቃወሙና ያስጨነቁ ሁለት ታላላቅ መንግሥታት ግብፅና አሦር አልፈዋል።

በዮሐንስ ራእይ 17 ሴቲቱ ስለተቀመጠችበት ባለ አሥር ቀንዶችና ባለ ሰባት ራሶች አውሬ ስናንብ፥ መልአኩ የቀንዶቹንና የራሶቹን ምሥጢር ለዮሐንስ እንዲህ ሲል ይነግረዋል፤ «ሰባት ራሶች ሰባት ተራራዎች ናቸው፤ ሰባት ነገሥታት ደግሞ ናቸው። አምስቱ ወድቀዋል፤ አንዱም አለ፤ የቀረውም ገና አልመጣም... »/ራእይ 17:9–10/።

ይህን ከፍል ስንመለከት ዮሐንስ ራእዩን ባየበት ዘመን እስራኤልን በመግዛት ላይ የነበረው የሮም መንግሥት ነው፤ ይህም ብቻ ሳይሆን የሮም መንግሥት በዘመኑ የዓለም ገናና መንግሥት ነበር/የሐዋ. 1:6፤ 25:21፤ ሉቃ. 23:2፤ ማቴ. 27፤ 11–14/። መልአኩ፥ «አንዱም አለ» ያለው የሮምን መንግሥት ነበር።

«የቀረውም ገና አልመጣም» ያለው ከተቃዋሚው ክርስቶስ በፊት የእስራኤል ተቃዋሚ በመሆን በአንድነት የሚነሡትን ባለ አሥር ነገሥታቱን መንግሥት ነው።

«አምስቱ ወድቀዋል» ሲል በዚያን ዘመን ገዥ ከነበረው ከሮም መንግሥት በፊት የነበሩትን አምስት ታላላቅ መንግሥታት ማመልከቱ ነው። ባቢሎንን የመጀመሪያው መንግሥት ካደረግን ከሮም ወደ ኋላ ስንቆጥር የወደቁት መንግሥታት ሦስት ብቻ ሊሆኑ ነው፤ እነዚህም ከሮም በፊት ግሪክ፥ ከግሪክ በፊት ፋርስና ሜዶን፥ ከዚያ በፊት ባቢሎን ነበሩ። ነገር ግን በራእይ 17 መልአኩ የወደቁት መንግሥታት አምስት መሆናቸውን ተናግሯል፤ ይኸውም ከባቢሎን በፊት የነበሩትን አሥርንና ግብፅን በመጨመር ነው። ስለሆነም፥ *ዮሐንስ ራእዩን ካየበት ዘመን ቀደም ብለው የወደቁት አምስት መንግሥታት የሚከተሉት ናቸው።



1. ግብፅ
2. አሦር
3. ባቢሎን
4. ፋርስና ሜዶን
5. ግሪክ

ስድስተኛው ዮሐንስ ራእዩን ባየበት ዘመን ይገዛ የነበረው የሮም መንግሥት ሲሆን፥ ሰባተኛው ደግሞ ከተቃዋሚው ክርስቶስ ቀደም ብሎ የሚመጣና ከቀድሞው የሮም መንግሥት

ግዛት በወጡ አሥር ነገሥታትና አገሮች የሚመሠረተው መንግሥት ነው /ራእይ 17:10፤ ዳን. 7:24/።

ባቢሎን ወደፊትም እስራኤልን የምትቃወምበት ጊዜ እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል /ኢሳ. 13–14፤ ኤር. 50–51/።

4ኛ ፋርስና ሜዶን

በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን ካስጨነቁትና ካፈራረሱት ታላላቅ መንግሥታት አራተኛው የፋርስና የሜዶን መንግሥት ነው። ይህም መንግሥት በዳንኤል መጽሐፍ ደረቱና ክንዶቹ ብር /ዳን. 2:32፥ 39/፥ ድብ የምትመስል ሁለተኛዪቱ አውሬ /ዳን. 7:5/፥ ብሎም ብልጣሶር በነገሠ በሦስተኛው ዓመት ዳንኤል ባየው ራእይ ውስጥ ባለ ሁለት ቀንድ በግ /ዳን. 8:3–4፥ 20/ ሆኖ የተገለጸው ነው። የፋርስና ሜዶን መንግሥት ለአንድ መቶ ዓመታት ያህል እስራኤልን በመያዝና በመልቀቅ ሲያስጨንቅ ኖሯል።

5ኛ ግሪክ

በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን ከገዙት ታላላቅ መንግሥታት አምስተኛው የግሪክ መንግሥት ነው። ይህም መንግሥት በትንቢተ ዳንኤል ሆዱና ወገቡ ናስ እንደሆነ ተገልጾ በሦስተኛ ደረጃ የተጠቀሰው /ዳን. 2:33፥ 39/፥ ነብር የምትመስለው ሦስተኛዋ አውሬ/ዳን. 7:6/፥ እንዲሁም ብልጣሶር በነገሠ በሦስተኛው ዓመት ዳንኤል ባየው ራእይ ውስጥ በዓይኖቹ መካከል አንድ ታላቅ ቀንድ ያለው ፍየል /ዳን. 8:5–9፥ 21–25/ ሆኖ የታየው ነው።

ታላቁ የግሪክ መንግሥት በግዛቱ ሥር አድርጎ ይቆጣጠራቸው ከነበሩት አገሮች መካከል ከቀድሞዎቹ ታላላቅ መንግሥታት ግብፅና አሦር ይገኙበታል። የግሪክ መንግሥት ከሁለት መቶ ሃምሳ ዓመታት በላይ እስራኤልን በመያዝና በመልቀቅ ሲያስጨንቃት ኖሯል። ዮሐንስ ራእዩን ባየበት ዘመን ያልነበረው ከወደቁት አምስት ታላላቅ መንግሥታት የመጨረሻው ነው። በራእይ 13:3 ከራሶቹ አንዱ ለሞቱ የነበረው ቁስል የተፈወሰለት ይኼ የግሪክ መንግሥት ነው።

ተቃዋሚው ክርስቶስንም የሚያስነሣው ይኸው የዚሁ የግሪክ መንግሥት አለቃ ነው።

ይህ መንግሥት ዮሐንስ ራእዩን ካየበት ዘመን በፊት የነበረ ሲሆን፥ በዚያን ጊዜ ግን አልነበረም። ይሁንና፥ ወደፊት ስምንተኛ ሆኖ የሚመጣውን የተቃዋሚው ክርስቶስን መንግሥት የሚያስነሣው የግሪክ መንግሥት አለቃ ነው /ራእይ 17፡8–11፤ 13፡2/። ይህንን አስመልክቶ የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ወደፊት ሰፋ አድርገን እንመለከታለን።

6ኛ ሮም

በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን ካስጨነቁት ታላላቅ መንግሥታት ስድስተኛው የሮም መንግሥት ነው። ይህም መንግሥት በትንቢተ ዳንኤል ጭኖቹ ብረት እንደሆኑ ተደርጎ በአራተኛነት የተጠቀሰው /ዳን. 2፡33፥ 40/ እና ታላላቅ የብረት ጥርሶች በነበሯትና እጅግ በበረታች፥ በምታስፈራዋና በምታስደነግጠው አውሬ የተመሰለው ነው /ዳን. 7፡7–8፥ 23–24/። በተጨማሪም በዮሐንስ ራእይ ዘመን «አንዱም አለ» /ራእይ 17፡10/ የተባለለትና በወቅቱ እስራኤልን ያውክ የነበረ መንግሥት ነው። የሮም መንግሥት እስራኤላውያንን ለሁለት መቶ ዓመታት ያህል በማስጨነቅ ገዝቷል። ቀጣዩና ሰባተኛው ባለ አሥሩ ነገሥታት መንግሥትና ስምንተኛ ሆኖ በመምጣት በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን በመቃወም የመጨረሻው የሚሆነው የተቃዋሚው ክርስቶስ መንግሥት የሚመጣው ከቀድሞው የሮም መንግሥት ግዛቶች ነው /ዳን. 7፡24/።

7ኛ ከቀድሞው የሮም መንግሥት ግዛት በወጡ አሥር መንግሥታት የሚመሠረተው መንግሥት

/ዳን. 7:24/

በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን ገዝቶ እንዳስጨነቀ በእግዚአብሔር ቃል ከተገለጸው ከስድስተኛው የሮም መንግሥት ቀጥሎ ከተቃዋሚው ክርስቶስ መንግሥት /The kingdom of AntiChrist/ በፊት የሚመጣው ከቀድሞው የሮም መንግሥት ግዛት ከወጡ አሥር አገሮች አሥር መንግሥታት የሚመሠረተው ሰባተኛው መንግሥት ነው። ይህ መንግሥት ገና ወደፊት የሚመጣ የመሆኑ እውነታ በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ተገልጾአል።

> *«... የቀረውም ገና አልመጣም፥ ሲመጣም ጥቂት ጊዜ ሊቆይ ይገባዋል»/ራእይ 17:10/።*

ምንም እንኳ እነዚህ አሥር ነገሥታት የሚወጡት ከስድስተኛው የሮም መንግሥት ቢሆንም/ዳን. 7:24፤ 2:42/፥ የራሳቸው መንግሥትና ግዛት ያላቸው አሥር አገሮች ናቸው። አሥሩ መንግሥታት ከስድስተኛው መንግሥት ከሮም የወጡ ለመሆናቸው የእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ያረጋግጥልናል።

1. በዳንኤል 2:42 እኩሉ ሸክላና እኩሉ ብረት ሆነው የተገለጹት አሥሩ የእግር ጣቶች

   ሀ. ጣት በተፈጥሮው የእግር ክፍል መሆኑና እነዚህም ጣቶቹና እግሮቹ በጭኑ ላይ መሆናቸው፥

   ለ. ጭኑ ብረት ከሆነው ማለትም ከስድስተኛው መንግሥት ጋር እኩል ሆኖ በመልክ መመሳሰላቸው /ዳን. 2:33፥ 41-43/፥

   ሐ. እነዚህ እግሮችና ጣቶች ጭኑ ብረት ከሆነው ከስድስተኛው መንግሥት እግሮችና ጣቶች መሆናቸውና ዳሩ ግን ከፊል ብረት ከፊል ሸክላ



መባላቸው የተከፋፈሉ መንግሥታት እንደሚያደርጋቸው ተገልጾአል /ዳን. 2:41-43/። ስለዚህ እነዚህ በዮሐንስ ራእይ ዘመን በሮም ግዛት ሥር የነበሩትና አሁን ግን ራሳቸውን ችለው ያሉ አሥር መንግሥታት መሆናቸው ግልጽ ነው።


2. በዳንኤል 7:23-24፥ አሥሩ ቀንዶች ከአራተኛው መንግሥት የሚነሡ አሥር መንግሥታት መሆናቸው ተገልጾአል።


> *«እንዲህም አለ፦ አራተኛዪቱ አውሬ በምድር ላይ አራተኛ መንግሥት ትሆናለች፤ እርሱም ከመንግሥታት ሁሉ የተለየ ይሆናል፤ ምድሪቱንም ሁሉ ይበላል፥ ይረግጣታል፥ ያደቅቃታልም። አሥሩም ቀንዶች ከዚያ መንግሥት የሚነሡ አሥር ነገሥታት ናቸው» /ዳን. 7:23-24/።*

ይህንን ክፍል ስንመለከት፥ አሥሩ ቀንዶች የሚወጡት በዳንኤል ምዕራፍ ሰባት ከተገለጹት አራት አራዊት ከአራተኛው ውስጥ እንደሆነ ልብ ልንል እንችላለን።


ንጉሡ ናቡከደነፆርና ነቢዩ ዳንኤል በሕልምና በራእይ ያዩትን የመንግሥታት ቅደም-ተከተል እነርሱ ከነበሩበት ዘመን ቀደም ብሎ ከነበሩት ሁለት መንግሥታት ጋር በአንድነት ስንመለከት የሚከተለውን እናገኛለን።


	የእገሮች ስም		የናቡከደነፆር ሕልም/ምስል/		የዳንኤል ራእይና ሕልም
1	ግብፅ				
2	አሦር				
3	ባቢሎን	3	የወርቁ ራስ/ናቡከደነፆር/	1	አንበሳ የምትመስለው አውሬ
4	ፋርስና ሜዶን	4	የብረት ደረትና ክንድ/ቂሮስና ዳርዮስ/	2	ድብ የምትመስለው አውሬና ሁለት ቀንድ የነበረው በግ
5	ግሪክ	5	የናስ ሆድና ወገብ/ታላቁ እእስክንድር/	3	ነብር የምትመስለው አውሬና አንድ ቀንድ የነበረው ፍየል
6	ሮም	6	የብረት ጭኖች/የቀድሞው የሮም መንግሥት/	4	የምታስፈራውና የምታስደነግጠው አውሬ
					
7	1 2 3 4 5 6 7 8 9 10 10 መንግሥታት /ገና መንግሥትን ያልተቀበሉ አሥር መንግሥታት – ራእይ 17:12/	7	1 2 3 4 5 6 7 8 9 10 የብረትና የሸክላ እግሮችና አሥር የእግር ጣቶች/ዳን. 2:41-43/	7	1 2 3 4 5 6 7 8 9 10 አሥር ቀንዶች/አሥር ነገሥታት – ዳን. 7:7፣ 19-24፤ ራእይ 13:1-2/



ራሱ ጥሩ ወርቅ | ባቢሎን |
ደረቱና ክንዶቹ ብር | ፋርስና ሜዶን |
ሆዱና ወገቡ ነሀስ | ግሪክ |
ጭኖቹ ብረት | ሮም |
እግሮቹ እኩሉ ብረት እኩሉ ሸክላ | የአሰሩ መንግስታት መንግስት


ጥቁር ባህር
የካስፒያን ባህር
ሶሪያ
አርሜንያ
ከርከሚሽ
ቆጵሮስ
ሜዶን
የሜዲትራንያን ባህር
ሶርያ
ኤላም
ባቢሎን
ኢየሩሳሌም
ግብፅ
ሚምፊስ
የፋርስ ባህረ ሰላጤ
ቀይ ባህር
አባይ ወንዝ

የባቢሎን መንግስት


የሜዲትራንያን ባህር
አሌክሳንድርያ
ሲብያ
ሄልዮፖሊስ
ሚምፊስ
አባይ ወንዝ
ሄርሞፖሊስ
ኤል አማርና
ላይኛው ግብፅ
ሊኮንፖሊስ
ቴቢስ
የጨው ባህር
በርንቄ
Nile R.
አቡ ሲምበል
ኑብያ
የግብፅ መንግስት


የአሶር መንግስት
ጥቁር ባህር
የካስፒያን ባህር
ሰርዴስ
ፍርግያ
ኤቴና
ስፓርታ
ሊዲያ
ሚላጢን
ሃራን
ከርከሚሽ
ነነዌ
ሜዶን
ሶርያ
አሱር
ፊንቄ
የጢግሮስ ወንዝ
የኤፍራጥስ ወንዝ
ኤላም
ሱሳ
ፋርስ
ባቢሎን
ከለዳይ
የፋርስ ባህረ ሰላጤ
የሜዲትራንያን ባህር
ሊቢያ
ጢሮስ
ደማስቆ
ፍልስጤም
ኢየሩሳሌም
ግብፅ
ሜምፊስ
አባይ ወንዝ
ቀይ ባህር


የፋርስ መንግስት
አሰኩ-ቱሶች
መቀዶንያ
ትራስ
ጥቁር ባህር
ቦቢታንያ
አቴና
ስፓርታ
ሊዲያ
ፍርግያ
ቃፓዶቅያ
አርመን
ሚልቅያ
ኪፕሮስ
ሶርያ
አሶር
ፊንቄ
ሲብያ
ፍልስጤም
ግብፅ
ባቢሎን
ባቢሎንያ
ሱሳ
ሜዶን
ካስፒያን ባህር
ቀይ ባህር
የአረብ በረሃ
የፋርስ ባህረ ሰላጤ
ጌድሮሲያ
አረተስያ
ህንድ
ጋንድሃሬ
ቃርቴና
ግርጂያና
ባክትሪያ
ስግዲያና

የግሪክ መንግስት
ኤራል ባህር
የካስፒያን ባህር
ጥቁር ባህር
ሜዲትራንያን ባህር
የአረብ ባህር
ቀይ ባህር
327
325
329
330
331
333
334

የዞን 4 ሕዝብ ቤተ መጻሕፍት
Zone 4 Public Library

አሥሩ ነገሥታት

እነዚህ አሥር ነገሥታት በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በሰፊው ተጠቅሰው ይገኛሉ። በዳንኤል 7፡7 ላይ በተገለጸችው አውሬ ላይ የሚገኙ አሥር ቀንዶች፥ በራእይ 13፡1 ከባሕር በወጣው አውሬ ላይ ያሉት አሥር ቀንዶችና በዳንኤል 2፡41-43 የምንመለከታቸው አሥሩ የብረትና የሸክላ የእግር ጣቶች ከአራተኛዪቱ አውሬ/ከሮም/ የሚነሡ አሥር ነገሥታት ናቸው።

«አሥሩ ቀንዶች ከዚያ መንግሥት የሚነሡ አሥር ነገሥታት ናቸው»/ዳን. 7፡24/። ይህም ማለት ከድሮው የሮም ግዛቶች/The Old Roman Empire/ ተከፍለው የሚወጡ መንግሥታት ናቸው ማለት ነው። የድሮው የሮም መንግሥት ዛሬ ነጻነታቸውን አግኝተው የራሳቸውን መንግሥት የሚያስተዳድሩ በርካታ አገሮችን ያካተተ ነበር። በአሁኑ ጊዜ እነዚያ አገሮች ከዚያ ሰፊ ግዛት ተከፍለው ወጥተዋል። በትንቢተ ዳንኤል 2፡41-42 ንጉሡ ናቡከደነፆር ባየው ሕልም ውስጥ ከፊል ብረትና ከፊል ሸክላ እግሮችና አሥር ጣቶች የብረት ጭን ከነበረው ከድሮው ከታላቁ የሮም መንግሥት ተከፍለው የሚወጡት የአሥር መንግሥታት ነገሥታት ናቸው። እንዲሁም እነዚህ መንግሥታት ዛሬ እንደምናያቸው እኩሉ ብርቱ እኩሉ ደካማ ናቸው።

> *«እግሮቹና ጣቶቹም እኩሉ ሸክላ እኩሉም ብረት ሆኖ እንዳየህ እንዲሁ የተከፋፈለ መንግሥት ይሆናል። የእግሮቹም ጣቶች እኩሉ ብረት እኩሉም ሸክላ እንደነበሩ እንዲሁ መንግሥቱ እኩሉ ብርቱ እኩሉ ደካማ ይሆናል»/ዳን. 2፡41-42/።*

እነዚህ መንግሥታት የድሮውን የሮም መንግሥት አያቋቁሙም። ነገር ግን በድሮው የሮም መንግሥት ግዛት ብዙ አገሮች በውስጡ ተካተው ታላቅ መንግሥት እንዳደረጉት ሁሉ ሃያ አራት አገሮችን አጠቃሎ ከነበረው ከድሮው የሮም ግዛት ውስጥ እነዚህ አሥር አገሮች የየራሳቸውን አገር እየመሩ የድሮውን የሮም መንግሥት የሚመስል ታላቅ የመንግሥታት

ጎብረት ያቋቁማሉ። ምንም እንኳ እነዚህ አገሮች በብዙ ነገር ጎብረትና ተመሳሳይነት ይኑራቸው እንጂ እንደ ድሮው የሮም መንግሥት ሙሉ በሙሉ የተዋሐደ ግዛት አይሆኑም።

> «... ነገር ግን ብረት ከሸክላ ጋር እንደማይጣበቅ እንዲሁ እርስበርሳቸው አይጣበቁም»/ዳን. 2:43/።

ይህ ጎብረት ከመላው ዓለም በተውጣጡ አገሮች ሳይሆን ከድሮው የሮም መንግሥት ግዛት ማለትም ከደቡብ አውሮፓ፥ ከምዕራብ አውሮፓ፥ ከምዕራብ እስያና ከሰሜን አፍሪካ የሚውጣጡ አገሮች ጎብረት ነው።

እነዚህ አሥር ነገሥታት በአንድ ጊዜ እኩል ይነግሣሉ። አሳባቸውና አመለካከታቸው አንድ ዓይነት ይሆንና የግዛታቸውም ዘመን እኩል ያከትማል።

> «ያየሃቸውም አሥሩ ቀንዶች ገና መንግሥትን ያልተቀበሉ አሥር ነገሥታት ናቸው። ዳሩ ግን ከአውሬው ጋር ለአንድ ሰዓት እንደ ነገሥታት ሥልጣን ይቀበላሉ። እነዚህ አንድ አሳብ አላቸው፤ ኃይላቸውንና ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ይሰጣሉ»/ራእይ 17:12–13፤ 17:17/።

> «እነዚህ አሥር ነገሥታት አውሬው/ሐሳዊ መሢሕ/ ከመምጣቱ በፊት በአሥር መንግሥታት ላይ ይነግሣሉ/ዳ. 7:7–8፤ 7:19–24/።

በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን በመቃወም ከሚነሡት መንግሥታት የቁጥር ደረጃ በአውሬው የራስ ቁጥር ቅደም–ተከተል ሲሰጣቸው ሰባተኛውን ደረጃ ይይዛል። በራእይ 17:10 ላይ «የቀረውም ገና አልመጣም፤ ሲመጣም ጥቂት ጊዜ ሊቆይ ይገባዋል» ተብሎ የተጻፈውም ስለዚሁ ስለ ሰባተኛው መንግሥት ነው።

በዳንኤል 2:40–45 የተጠቀሱት አሥር ጣቶች፥ በዳንኤል 7:7–8 የተገለጹት አሥር ቀንዶችና በራእይ 13:1 የቀረቡት አሥር ቀንዶች ስለመመሳሰላቸው የሚከተሉትን ተጨማሪ ማስረጃዎች ልንመለከት እንችላለን።

1. ቁጥራቸው አንድ ዓይነት ነው/ራእይ 13:1፤ ዳን. 2:40–45፤ ዳን. 7:7–27/።

2. በአንድ ላይ ይኖራሉ፤ በአንድነትም ክርስቶስን በአርማጌዶን ይወጋሉ/ራእይ 17:14፤ ዳን. 2:34፥ 44-45፤ ራእይ 19:11-21፤ ዳን. 7:8-14፤ 7:21-27/።

3. ሁሉም ከድሮው የሮም መንግሥት በኋላና ከድሮው የሮም መንግሥት ግዛት የሚነሡ ናቸው/ራእይ 17:12-17፤ ዳን. 2:44-45፤ ዳን. 7:7-27/።

4. ሁሉም በአንድ ዓይነት ጊዜ ከአንድ አውሬ ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ/ራእይ 17:12-17፤ 19:19-21፤ ዳን. 7:8፥ 21-27/።

5. በዳንኤል 7:7-8፥ 19-24 የተጠቀሰው ትንሹ ቀንድና በራእይ 17:9-17 የሚገኘው አውሬ አንድ ዓይነት ናቸው። ሁለቱም ከአሥሩ ነገሥታት በኋላ ከእነርሱ መካከል የሚነሡ ናቸው/ራእይ 17:12-17፤ ዳን. 7:7-8፥ 23-24/።

6. የእግዚአብሔርና የክርስቶስ መንግሥት በምድር ላይ የሚመሠረተው እነርሱ በምድር በሚኖሩበት ዘመን ነው/ራእይ 17:14፤ 19:11-21፤ ዳን. 2:44-45፤ 7:7-27/።

7. ኃይላቸውን ለተመሳሳይ ሰው ማለትም ለተቃዋሚው ክርስቶስ ለተመሳሳይ የጊዜ ርቀት ይሰጣሉ/ራእይ 13:5፤ 17:8-17፤ ዳን. 7:23-25፤ 12:7/።

8. አሥሩ ቀንዶች በራእይ 17:8-17 እንዳለው እንደ ሰባተኛ መንግሥት ጋር አንድ ዓይነት ናቸው። ሁሉም ስድስተኛውን መንግሥት /ሮምን/ ይፈጽማሉ። ስምንተኛውን መንግሥት/ተቃዋሚውን ክርስቶስን/ ያዘጋጃሉ/ራእይ 17፤8-17። በዳንኤል 2:40-45 የተጠቀሱት አሥሩ ጣቶችና በዳንኤል 7:7-8፥ 23-24 የሚገኙ አሥር ቀንዶች ሁሉም ከስድስተኛው መንግሥት ከሮም የወጡ ናቸው። ከመካከላቸውም የሚወጣውን ትንሹን ቀንድ/ሐሰዊ መሢሕ/ ያስክትላሉ። በዚህ ሁሉም አንድ ዓይነት ናቸው።

9. በሁለቱም መጻሕፍት ማለትም በትንቢተ ዳንኤልና በዮሐንስ ራእይ የተጠቀሱት አሥሩ ቀንዶች ከትንሹ ቀንድ/ከሐሰዊ መሢሕ/ በፊትና በኋላ ይነግሣሉ። ከመምጣቱ በፊትና በከመጣ በኋላ የሚነሡበት ሁኔታ ይለያያል። ከመምጣቱ በፊት ራሳቸውን የቻሉና ሥልጣንና ኃይል በእጃቸው የሚኖራቸው ሲሆን፥ ከመጣ በኋላ ግን ኃይላቸውን ለተቃዋሚው ክርስቶስ ስለሚሰጡ በራሳቸው መንግሥት ላይ የርሱ ተወካዮች ሆነው ይቀመጣሉ። እነርሱ ሰባተኛውን

መንግሥት የሚቆጣጠሩ ሲሆን፥ እርሱ ደግሞ እነርሱን ጠቅልሎ ስምንተኛውን መንግሥት ይቆጣጠራል። ይህም አንድነታቸውን ያሳያል።

የግሪክ መንግሥት

«ከዚህም በኋላ እነሆ ነብር የምትመስል በጀርባዋም ላይ አራት የወፍ ክንፎች የነበሯት ሌላ አውሬ አየሁ፤ ለአውሬዪቱም አራት ራሶች ነበሩአት፤ ግዛትም ተሰጣት»/ዳን. 7:6/።

«እነሆም ከምዕራብ ወገን አንድ አውራ ፍየል በምድር ሁሉ ፊት ላይ ወጣ... »/ዳን. 8:5/።

«አውራውም ፍየል ራሱን እጅግ ታላቅ አደረገ፤ በበረታም ጊዜ ታላቁ ቀንዱ ተሰበረ፤ ወደ አራቱም የሰማይ ነፋሳት የሚመለከቱ አራት ቀንዶች ከበታቹ ወጡ። ከእነርሱም ከአንደኛው አንድ ታናሽ ቀንድ ወጣ። ወደ ደቡብም ወደ ምሥራቅም ወደ መልካሚቱም ምድር እጅግ ከፍ አለ። ከአራዊትና ክከዋብትም አያሌዎቹን ወደ ምድር ጣለ... አውራውም ፍየል የግሪክ ንጉሥ ነው። በዓይኖቹም መካከል ያለው ታላቁ ቀንድ የመጀመሪያው ንጉሥ ነው። እርሱም በተሰበረ ጊዜ በእርሱ ፋንታ አራቱ እንደተነሡ እንዲሁ ከወገኑ አራት መንግሥታት ይነሣሉ። ነገር ግን በኃይል አይተካከሉትም። በመንግሥታቸውም መጨረሻ ኃጢአታቸው በተሞላች ጊዜ እንቆቅልሽን የሚያስተውል ፊተ ጫካኝ ንጉሥ ይነሣል»/ዳን. 8:8–10፥ 21–23/።

ይህ የግሪክ መንግሥት ናቡከደነፆር ባየው የሕልም ምስል የናሱ ሆድና ወገብ ተደርጎ የተመለከተ ሲሆን/ዳን. 2:33/፥ በዳንኤል ሕልምና ራእይ ውስጥ ደግሞ ነብር የምትመስለው አውሬ/ዳን. 7:6/ እና ታላቁ ባለ አንድ ቀንድ ፍየል ሆኖ ተገልጾአል/ዳን. 8:5/።

ይህ የግሪክ መንግሥት ከመምጣቱ በፊት በምድር ላይ ኃያል የነበረውና እስራኤልን በማስጨነቅ ላይ የቆየው መንግሥት ናቡከደነፆር በሕልም ባየው ምስል በብር ደረትና ክንድ

የዞን 4 [illegible] መጻሕፍት
Zone 4 Public Library

ተምስሏል/ዳን. 2:32/፤ ዳንኤል በተመለከተው ሕልምና ራእይ ውስጥ ደግሞ ድብ በምትመስለው አውራ/ዳን. 7:5/ እና በባለ ሁለት ቀንድ በግ ተገልጸ ይገኛል/ዳን. 8:1-4/፤ ይህም የፋርስና የሜዶን መንግሥት ነው።

> «ዓይኔን አንሥቼ አየሁ፤ እነሆም ሁለት ቀንዶች የነበሩት አንድ አውራ በግ በወንዙ ፊት ቆሞ ነበር። ሁለቱም ቀንዶቹ ከፍ ከፍ ይሉ ነበር፤ አንዱ ግን ከሁለተኛው ከፍ ያለ ነበር»/ዳን. 8:3/።

ከነዚህ ሁለት የበግ ቀንዶች አንደኛው የሚያሳየው የሜዶን ንጉሥ ዳርዮስን ሲሆን/ዳን. 5:31/፥ ሁለተኛው ደግሞ የፋርስ ንጉሥ ቂሮስን ነው/2ኛ ዜና 36:22-23/። አንደኛው ቀንድ ከሌላው ከፍ ማለቱ የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ ከሜዶን ንጉሥ ከዳርዮስ ይልቅ ኃያል ስለነበረ ነው። የፋርስና የሜዶን ነገሥታት ባቢሎንን፥ ግብፅንና ሌሎችንም አገሮች አሸንፈው በምድር ላይ ታላቅ መንግሥታት ለመሆን በቅተው ነበር/ዳን. 8:4/።

> «ባየኸው በአውራው በግ ላይ የነበሩ ሁለቱ ቀንዶች እነርሱ የሜዶንና የፋርስ ነገሥታት ናቸው» /ዳን. 8:20/።

እነዚህ ነገሥታት በምድር ላይ ኃያልን በነበሩበት ዘመን ነበር አምስተኛው የግሪክ መንግሥት ወደ ድል አድራጊነት የመጣው። ይህ መንግሥት ፋርስንና ሜዶንን ድል ካደረገ በኋላ ኃያል መንግሥት ለመሆን ቻለ/ዳን. 8:5-8/።

በታላቁ ፍየል ግለትም በግሪክ መንግሥት ላይ የተመለከተው ታላቁ ቀንድ ታላቁን የግሪክ ንጉሥ የሚያመለክት ነው፤ ይህም ታላቁ አሌክሳንደር ነው። የፍየሉ ትልቁ ቀንድ እየተሰበረ ከ13 ዓመታት የአገዛዝ ዘመን በኋላ ታላቁ አሌክሳንደር ሞተ። ከዚያም ወደ አራቱ የሰማይ ነፋሳት የሚመለከቱ አራት ቀንዶች ከበታቹ እንደወጡ ሁሉ/ዳን. 8:8/፥ ከአሌክሳንደር ሞት በኋላ መንግሥቱ/የግሪክ መንግሥት/ በአራት ታላላቅ ክፍሎች ተከፈፍሎ በአራት ጀኔራሎች ይመራ ጀመር። እነዚህ ለአራት የተከፈሉት አራት መንግሥታት ግሪክ፥ ግብፅ፥ ሶርያና ቱርክ ናቸው። ዳንኤል በ7:6 ባያት ነብር በምትመሰለው አውሬ ላይ የሚገኙ አራት ክንፎችና አራት ራሶች እነዚህ አራት መንግሥታት ከግሪክ መውጣታቸውን የሚያሳይ ነው።

ከእነዚህ አራት ቀንዶች ከአንደኛው የሚወጣው አንድ ታናሽ ቀንድ እጅግ የከፋ ይሆናል፤ ይህም ታናሽ ቀንድ ከሠራዊትና ከከዋክብትም አያሌዎቹን የሚጥለውና የዘወትሩ መሥዋዕት እንዲሻር የሚያደርገው ተቃዋሚው ክርስቶስ ነው/ዳን. 8፡9-14፤ ዳን. 9፡27/።

እንግዲህ ተቃዋሚው ክርስቶስ የሚመጣው ከቀድሞው የግሪክ መንግሥት ግዛት አራት አገሮች ከአንደኛው ውስጥ ነው። እነዚህ አራቱ በግሪክ መንግሥት አለቃ/በሰይጣን መልአክ/ የሚመሩ አገሮች ነበሩ። አንደኛው ሲነሣ ሦስቱ ይወድቃሉ/ዳን. 8፡23/። በዳንኤል 7፡8 ከሚገኙት አሥር ቀንዶች መካከል የሚነቀሉትም ሦስት ቀንዶች በግሪክ መንግሥት አለቃ ከሚነሡት የግሪክ አገሮች ግብፅ፥ ግሪክ፥ ሶርያና ቱርክ በአንዳቸው ተቃዋሚው ክርስቶስ በግሪክ መንግሥት አለቃ ሲነሣ የሦስቱን መውደቅ ነው የሚያሳየው።

> *«... እነሆም በመካከላቸው ሌላ ትንሽ ቀንድ ወጣ፤ በፊቱም ከቀደሙት ቀንዶች ሦስቱ ተነቃቀሉ»/ዳን. 7፡8/።*
>
> *«ኃይሉም ይበረታል፤ ነገር ግን በራሱ ኃይል አይደለም... »/ዳን. 8፡24/።*

እነዚህ አሥሩ ቀንዶች በቀድሞው የሮም ግዛት የነበሩ የአሥር አገሮች ነገሥታት መሆናቸውን ባለፈው ትምህርት ተመልክተናል። ከግሪክ መንግሥት በኋላ ስድስተኛው መንግሥት በመሆን በምድር ላይ የመጣው የእስራኤል ተቃዋሚ የሆነው የሮም መንግሥት አገሮችን በጦርነት ሲይዝ የቀድሞውን የአሌክሳንደር ግዛትን ማለስተም ግሪክን፥ ግብፅን፥ ሲርያንና ቱርክን ጭምር ጠቅልሎ ይገዛ ነበር።

እንግዲህ ተቃዋሚው ክርስቶስ ከቀድሞው የሮም ግዛት ሥር ከነበሩ አሥር መንግሥታት በኋላ ከነርሱ ውስጥ ወጥቶ የሚመጣ ከሆነ/ዳን. 7፡7-8፤ 7፡23-25፤ ራእይ 13፡1/፥ እንደገናም ከቀድሞው የግሪክ ግዛት ውስጥ ከነበሩት አራት አገሮች ከአንደኛው ውስጥ የሚወጣ ከሆነ/ዳን. 8፡9-14፤ 9፡23-25፤ ራእይ 13፡2/፥ ይህ ተቃዋሚው ክርስቶስ የሚመጣው በግሪክ መንግሥት ዘመን የግሪክ ግዛት ከነበሩትና እንደገናም በሮም ግዛት ሥር ተጠቃለው ከነበሩት አራት አገሮች ማለትም ከግሪክ፥ ከግብፅ፥ ከሶርያና ከቱርክ ከአንዳቸው ነው ማለት ነው።

ትንሹ ቀንድ

«... ከእርሰዋም በፊት ከነበሩት አራዊት ሁሉ የተለየች ነበረች፤ አሥር ቀንዶችም ነበሩአት። ቀንዶችንም ተመለከትሁ፤ እነሆም በመካከላቸው ሌላ ትንሽ ቀንድ ወጣ፤ በፊኣም ከቀደሙት ቀንዶች ሦስት ተነቃቀሉ፤ እነሆም በዚያ ቀንድ እንደ ሰው ዓይኖች የነበሩ ዓይኖች በትዕቢትም የሚናገር አፍ ነበሩበት»/ዳን. 7:7-8/።

«... እርሱም ከፊተኞች የተለየ ይሆናል፤ ሦስቱንም ነገሥታት ያዋርዳል፤ በልዑልም ላይ ቃልን ይናገራል። የልዑልንም ቅዱሳን ይሰባብራል፤ ዘመናትንና ሕግን ይለውጥ ዘንድ ያስባል፤ እስከ ዘመንና ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም በእጁ ይሰጣሉ። ነገር ግን ፍርድ ይሆናል፤ እስከ ፍጻሜም ድረስ ያፈርሱትና ያጸኑት ዘንድ ግዛቱን ያስወግዱታል»/ዳን. 7:24-26/።

«ከእነርሱም ከአንደኛው አንድ ታናሽ ቀንድ ወጣ። ወደ ደቡብም ወደ ምሥራቅም ወደ መልካሚቱም ምድር እጅግ ከፍ አለ፤ እስከ ሰማዊም ሠራዊት ድረስ ከፍ አለ... እስከ ሠራዊትም አለቃ ድረስ ራሱን ታላቅ አደረገ፤ ከእርሱም የተነሣ የዘወትሩ መሥዋዕት ተሻረ፤ የመቅደሱም ሰፍራ ፈረሰ»/ዳን. 8:9-14/።

ከአሥሩ ቀንዶች መካከል እስራኤልን በመቃወም በአሕዛብ ዘመን የሚነሣው ስምንተኛውና የመጨረሻው መንግሥት የትንሹ ቀንድ/ሐሳዊ መሢሕ/ መንግሥት ነው። ይህ የአሕዛብ ንጉሥ ባለፉት ክፍሎች እንደተመለከትነው መጀመሪያ በአምስተኛው መንግሥት በግሪክ ውስጥ ከነበሩትና በኋላም በስድስተኛው መንግሥት በሮም ውስጥ ተጠቅልለው በኋላም በመጨረሻው ዘመን በቀድሞው የሮም መንግሥት ሥር ከነበሩት ሌሎች ስድስት አገሮች ጋር በመሆን ታላቁን የአሥር አገሮች ኅብረት /በአሕዛብ ዘመን በአሥር መንግሥታት በሚቋቋመው ሰባተኛው መንግሥት/ ከሚቋቋሙት አራት አገሮች ከግብፅ፥ ከግሪክ፥ ከሶርያና ከቱርክ ከእነዚህ ከአንዳቸው የሚወጣው ነው።

ይህ ንጉሥ ከመምጣቱ በፊት በአሥሩ መንግሥታት የሚመራው ሰባተኛው መንግሥት መምጣቱ የግድ ነው። ትንሿ

ቀንድ ከአሥሮቹ ቀንዶች መካከል/ዳን. 7፡8፤//ከቀድሞው የግሪክ መንግሥት ሥር ከነበሩት አራት አገሮች መካከል ከአንደኛው/ ዳን. 8፡8፥ 23/ /በቀድሞው የግሪክ ሥር ከነበሩት አራት አገሮች ከአንደኛው/ እንደወጣ ሁሉ አሥሩ ነገሥታት ከነገሡ በኋላ ከእነርሱ ከአንደኛው ውስጥ ከጥልቁ በሚመጣው በቀድሞው የግሪክ መንግሥት አለቃ/The prince of Grecia/ አማካኝነት ይነሣል።

ተቃዋሚው ክርስቶስ ከዚህ በፊት ካለፉት ስድስት ነገሥታት አንዳቸው ከሞት ተነሥተው የሚመጣ ወይንም እንደ ክፉ መንፈስ ሆኖ የሚገለጥ አይደለም። ይልቁንም በቀድሞው የግሪክ መንግሥት አለቃ የሚነሣና የሚሠራ ሰው ነው። ሰው ሰለመሆኑም የእግዚአብሔር ቃል የሚከተሉትን መረጃዎች ያስቀምጥልናል።

1. በአርማጌዶን በክርስቶስ መሸነፉ/ራእይ 19፡19-21/

2. ከሕዝብ መካከል የሚወጣ ንጉሥ መሆኑ/ዳን. 11፡36፤ ራእይ 17፡12-13/

3. በምድር ላይ የሚያደርገውን ሁሉ የሚያደርገውን በራሱ ሳይሆን በሰይጣን ኃይል መሆኑ/ዳን. 8፡24፤ ራእይ 13፡4-5/

ተቃዋሚው ክርስቶስን የሚያስነሣው የግሪክ መንግሥት አለቃ /ሰይጣናዊ መልአክ/ ነው።

> *«አሁንም ከፋርስ አለቃ ጋር እዋጋ ዘንድ እመለሳለሁ፤ እኔም ስወጣ እነሆ የግሪክ አለቃ ይመጣል»/ዳን. 10፡20/።*
>
> *«ከራሶቹ ላይ ለሞት እንደታረደ ሆኖ አንዱን አየሁ፤ ለሞቱ የሆነውም ቁስል ተፈወሰ»/ራእይ 13፡3/።*
>
> *«ያየኸው አውሬ አሰቀድሞ ነበረ፤ አሁንም የለም፤ ከጥልቁም ይወጣ ዘንድ አለው፤ ወደ ጥፋትም ይሄዳል... አውሬው አሰቀድሞ እንደነበረ አሁንም እንደሌለ ነገር ግን እንዳለ ሲያዩ ያደንቃሉ። ጥበብ ያለው አእምሮ በዚህ ነው። ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች ናቸው። ሰባት ነገሥታትም ደግሞ ናቸው። አምስቱ ወድቀዋል። አንዱም አለ፤ የቀረውም ገና አልመጣም፤ ሲመጣም ጥቂት ጊዜ ሊቆይ ይገባዋል። የነበረውና የሌለው አውሬ ራሱ ደግሞ ሰምንተኛው*

የዘን 4 ሕዝብ ቤተ መጻሕፍት
Zone 4 Public Library

ነው፤ ከሰባቱም አንዱ ነው፤ ወደ ጥፋትም ይሄዳል»/ራእይ 17፡8–11/።

ተቃዋሚው ክርስቶስ ከዚህ በፊት በምድር ላይ የነበረ ሰው ካልሆነ፥ «... አውሬው አስቀድሞ ነበረ፤ አሁንም የለም፤ ከጥልቁም ይወጣ ዘንድ አለው» ሲል ምን ማለቱ ነው? ወይስ በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቃል ስለማን ነው የሚናገረው?

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ያለፉት ኃጢአትን ያደረጉ ሰዎች ነፍስ በጥልቁ ገብታ እንደገና ከጥልቁ ወጥታ ወደ ምድር እንደምትወጣ የተጻፈበት አንድም ክፍል የለም። ነገር ግን በጥልቁ የታሠሩ የወደቁ መላእክት እንዳሉ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል/ይሁዳ 6፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡4/።

እንግዲህ በጥልቁ ያሉት የወደቁ መላእክት ከሆኑ ይኼ ከጥልቁ የሚወጣውም አውሬ ከወደቀው መልአክ አንዱ ነው ማለት ነው። ይህ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ የሰይጣን መልአክ /Satanic Angel/ ነው።

በራእይ 17፡8 የተገለጸው አውሬ ወደ ጥልቁ ከመግባቱ በፊት ዮሐንስ ራእዩን ካየበት ዘመን ቀደም ብሎ ከወደቁት አማት የአሕዛብ መንግሥታት በአንደኛው ዘመን በምድር ላይ የነበረ የመንግሥት አለቃ ነው/ዳን. 10፡13፥ 20/። በዮሐንስ ራእይ ዘመን ግን በጥልቁ ነበረና በምድር ላይ አልነበረም። አሥሩ ነገሥታት ከነገሡ በኋላ ግን ከጥልቁ ይወጣል።

ይህ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ/የሰይጣን መልአክ/ ከአሥሩ ነገሥታት መካከል የሚወጣው ትንሹን ቀንድ/ተቃዋሚው ክርስቶስን/ ያስነሣዋል። ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ተቃዋሚው ክርስቶስን የሚያስነሣበት መንፈስ ከዮሐንስ ዘመን በፊት ወድቀው ከነበሩት አምስት ነገሥታት በአምስተኛው የግሪክ መንግሥት መንፈስ ነው።

በዳንኤል 7፡6 የምናየው ስለ ግሪክ መንግሥት በራእይ የታየው አውሬ ነብር ይመስል ነበር። በራእይ 17 ከጥልቁ የሚወጣው በራእይ 13፡1–4 የምንመለከተውን አውሬ/ሐሳዊ መሢሕ/ በመልክ ይመስል ነበር። በራእይ 13፡1–4 የተመለከተው አውሬ/ተቃዋሚው ክርስቶስ/ ነብር ይመስል ነበር። ስለዚህ ይኼ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ተቃዋሚው ክርስቶስን በቀድሞው በግሪክ መንግሥት መንፈስ የሚያስነሣው የግሪክ መንግሥት አለቃ ነው።

በዳንኤል 8:8 የፍየሉ ቀንድ መሰበር የታላቁ አሌክሳንደርን መሞት ያመለክታል። ከዚህም በኋላ የግሪክ መንግሥት ተንኮታኮተ። የግሪክ መንግሥትም አለቃ ወደ ጥልቁ ገባ። በራእይ 13:3 ለሞቱ የነበረው ቁስሉ የተፈወሰለት አ7ደኛው ራስ የግሪክ መንግሥትን የሚወክለው ራስ ነው። የመንግሥቱ አለቃ ወደ ጥልቁ ገባ። ያ ራስ ሞተ ማለት ነው። ለሞቱ የሆነው ቁስል መፈወስ የቅድሞው የግሪክ መንግሥት አለቃ ከጥልቁ መውጣቱንና በቀድሞው መንፈስ አንዱን ራስ ብቻ ሳይሆን አውሬውን/ተቃዋሚው ክርስቶስን/ ማስነሣቱን ያሳያል።

እንግዲህ ተቃዋሚው ክርስቶስ በቀድሞው የግሪክ መንግሥት መንፈስ የሚመጣ ከሆነ፥ እርሱን የሚያስነሣው ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ የግሪክ መንግሥት አለቃ እንደሆነ ግልጽ ነው። በዮሐንስ ራእይ፥ «የነበረውና የሌለውም አውሬ ራሱ ደግሞ ስምንተኛው ነው ከሰባቱም አንዱ ነው» የሚል እናነባለን።

«ከሰባቱም አንዱ ነው» ያለበት ምክንያት በተቃዋሚው ክርስቶስ የሚሠራው የግሪክ መንግሥት አለቃ ከዚህ በፊት በቀድሞው የግሪክ መንግሥት ስለነበረ ከተቃዋሚው ክርስቶስ በፊት ካሉት ሰባት የአሕዛብ መንግሥታት ግብፅ፥ አሦር፥ ባቢሎን፥ ፋርስና ሜዶን፥ ግሪክ፥ ሮም፥ የአሥር ነገሥታት መንግሥት ከነዚህ አንዱ ሆኖ ስለተቆጠረ ነው።

«ስምንተኛው ነው» የተባለው በተቃዋሚው ክርስቶስ ሆኖ ከሰባተኛው ማለትም ከአሥሩ ነገሥታት መንግሥት ቀጥሎ ስምንተኛ ሆኖ ስለሚነግሥ ነው።

ሦስቱ ምልክቶች

ሐሰተኛው ነቢይ ሰዎች ያለ አውሬው ምልክት ሊገዙ ወይም ሊሸጡ እንዳይችሉ የተቃዋሚው ክርስቶስ መንግሥት ደጋፊዎች ሆነው ምልክትን እንዲቀበሉ የሚያደርግባቸው ሦስት ዓይነት ምልክቶች ናቸው።

1. ምልክት – ይህ ምልክት ከአውሬው ስም ወይም ከስሙ ቁጥር የተለየና ነገር ግን ሰዎች በሐሰተኛው ነቢይ በግምባራቸው ወይም በቀኝ እጃቸው ላይ እንዲያደርጉ የሚገደዱበት ልዩ የስሙ ምልክት ነው/ራእይ 13:16–17/።

ይህ ምልክት ምንልባት የተቃዋሚው ክርስቶስን መንግሥት ልዩ ምልክት ወይም ዓርማ የያዘ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፥ የናዚ መንግሥት እንደነበረው ሰዋቲስካ እንደሚባለው ምልክት።



የናዚ ስዋቲስካ

ተቃዋሚው ክርስቶስም የራሱ የሆነ ምልክት/ዓርማ/ አለው። ነገር ግን ምን ዓይነት እንደሚሆን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አልተገለጸም/ራእይ 13:16–17፤ 14:9–11፤ 15:2፤ 20:4/።

2. የአውሬው ስም/ራእይ 13:17፤ 14:11/ – ይህ የተቃዋሚው ክርስቶስ መጠሪያ ስም ነው። ብዙ ሰዎች ተቃዋሚው ክርስቶስ ከሞቱት ሰዎች አንዱ ተነሥቶ እንደሚመጣና ዳግም በምድር ላይ እንደሚኖር አድርገው ይገምታሉ። ለምሳሌ፥ የአስቆሮቱ ይሁዳ ከሞት ትነሥቶ ይመጣል የሚሉ አሉ። ሌሎችም እንዲሁ ሌላውን ያስባሉ።

ለምሳሌ ያህል፥ የቀድሞው የሮም ጳጳስ፥ ሞሶሎኒ፥ ሒትለር፥ ስታሊንና የመሳሰሉትን በተቃዋሚው ክርስቶስ ስፍራ ያስቀምጣሉ። ምንም እንኳ ከነዚህ ሰዎች የአንዳንዶቹ የስም ቁጥር በግሪክ 666 ቢሆንም፥ ይህ የሰዎች ግምት እንጂ የእግዚአብሔር ቃል የሚለው አይደለም፤ እንዲያውም ይህ ከእግዚአብሔር ቃል የወጣና ከእውነት የራቀ መላምት ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ተቃዋሚው ክርስቶስ የእርሱን ምንነት በሚገልጹ በብዙ መጠሪያዎች ከመጠራቱ በስተቀር ትክክለኛ ስሙ ማን እንደሆነ አልተገለጸም።

3. የስሙ ቁጥር 666/ራእይ 13:17–18፤ 15:2/ – ይህ ቁጥር የሰው ቁጥር ነው። የተቃዋሚው ክርስቶስ ስምና የስሙ ምልክት ማንና ምን ዓይነት እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ አልተገለጸም። ይሁንና፥ የስሙ ቁጥር ስንት እንደሆነ ተገልጾአል፤ ቁጥሩም 666 ነው/ራእይ 13:18/።

ዛሬ በዓለማችን የብዙ ሰዎች ስም ቁጥር 666 ሊሆን ይችላል። ብዙ የዕብራይስጣን የግሪክ ስሞች ቁጥራቸው 666 ነው። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ተቃዋሚው ክርስቶስ ናቸው ማለት አይደለም።

ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በፊት በቀድሞው የሮም መንግሥት ግዛት ሥር የሚቋቋሙት የአሥሩ ነገሥታት መንግሥት ዘመን ከመምጣቱ በፊትና ከመጨረሻው ሦስት ተኩል ዓመታት በፊት ማንም ሰው ስሙን፥ የስሙን ምልክትና የስሙን ቁጥር ሊወስድ አይችልም። የብዙ ሰዎች የስማቸው ቁጥር 666 ቢሆንም፥ እነዚህ ሰዎች ተቃዋሚው ክርስቶስ አይደሉም።

ዛሬ በብዙ ስፍራና በአንዳንድ ነገሮች ላይ ተጽፈው የምናያቸው የ666 ምልክት የሚያትሙና የሚጠቀሙ ሰዎች ተቃዋሚው ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ የስሙ ቁጥር ለሕዝቡ አስደንጋጭና አዲስ ነገር እንዳይሆን ከአሁኑ እንዲለማመዱትና ለነገሩ ትኩረት ባለመስጠት እንደ ቀላል እንዲያዩት ለማድረግ ሰይጣን ያዘጋጀው ማዘናገያ ነው።

ተቃዋሚው ክርስቶስ የመላው ዓለም ፈላጭ ቆራጭ ገዥ ወይስ የተወሰኑ አገሮች አስተዳዳሪ?

ስለ ተቃዋሚው ክርስቶስና ስለ አገዛዙ በሚናገረው በዮሐንስ ራእይ 13፥ «ምድር ሁሉ፥ ሁሉም» የመሳሰሉትን አባባሎች እናገኛለን።

ለምሳሌ በቁጥር 7 ላይ፥

> *«... በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው»*

የሚል እናነባለን።

> *«ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ መጽሐፍ ስምቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይሰግዱለታል»/ቁ. 8/።*
>
> *«... የስሙ ቁጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል»/ቁ. 17/።*

ይህም ሆኖ፥ ተቃዋሚው ክርስቶስ በተወሰነ የዓለም ክፍል እንጂ በመላው ዓለም ገዥ አይሆንም። ይህንንም እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1. በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በብዙ ስፍራዎች «ምድር ሁሉ» የሚል ሐረግ ተጠቅሷል። ይሁን እንጂ፥ ሐረጉ የተጠቀሰበትንና ድርጊቱ የተፈጸመበትን ሁኔታ ከእግዚአብሔር ቃል ስናጠና ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት መላውን ዓለም የሚያመለክት ሳይሆን ድርጊቱ የሚፈጸምበትን አካባቢ ብቻ ነው። ለምሳሌ፥ በሮሜ 1፡8፥ «እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለተሰማች... » የሚል እናነባለን።

እንዲሁም ናቡከደነፆር በሕልም ስላየው ምስል ፍች ስንመለከት ናቡከደነፆርን አስመልክቶ፥ «በሚቀመጡበትም ስፍራ ሁሉ የሰው ልጆችንና የምድር አራዊትን የሰማይ ወፎችንም በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል። *ለሁሉም ሥር ነህ*» ይላል/ዳን. 2፡38/።

ስለ ግሪክ መንግሥትና ስለ ታላቁ አሚክሳንደር፥ «... ከዚያም በኋላ በምድር ሁሉ ላይ የሚገዛ ሌላ ሦስተኛ የናስ መንግሥት ይነሣል»/ዳን. 2፡39/ ሲል ይገልጽልናል።

ስለ ሮም፥ «አራተኛዪቱ አውሬ በምድር ላይ አራተኛ መንግሥት ትሆናለች፤ እርሱም ከመንግሥታት ሁሉ የተለየ ይሆናል። ምድሪቱንም ሁሉ ይበላል። ይረግጣታል፤ ያደቅቃትማል»/ዳን. 7፡23/።

የነዚህን ነገሥታት ታሪክ ስንመለከት፥ እንዳቸውም ከተወሰነ ክፍል በስተቀር በመላው ዓለም ገዥ አልነበሩም።

2. በራእይ 13 የተቃዋሚው ክርስቶስ መንግሥት በዳኤል 7፡23-24 እንደተገለጸው ከቀድሞው የሮም መንግሥት በወጡ አጅር መንግሥታት ላይ የተመሠረተ እንደሆነና በአሥሩም ላይ እንደሚሠለጥን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። አውሬው ያሉት አሥር ቀንዶች ብቻ ነው/ራእይ 13፡1/።

3. በራእይ 17፡12-13 አሥሩ ቀንዶች /አሥሩ ነገሥታት/ ብቻ የመንግሥታቸውን ኃይል ለተቃዋሚው ክርስቶስ አሳልፈው እንደሚሰጡ ይናገራል።

4. ተቃዋሚው ክርስቶስ ከእስራኤል ጋር የሚያደርገውን የሰባት ዓመታት ቃል ኪዳን ካፈረሰ በኋላ የእስራኤልን ምድርና ሌሎች ብዙ አገሮችን በጦርነት ይይዛል። ሆኖም ግን ከነዚህ አገሮችም ብዙዎቹ ሕዝቦች ከእጁ ያመልጣሉ። ለምሳሌ፥ በቀድሞ ስማቸው ኤዶምና ሞዓብ የዛሬዎቹ ዮርዳኖስና ሳውዲ ዓረቢያ ከእጁ ይድናሉ። ይሁንና፥ ከእስራኤል ጎረቤት አገሮች ብዙዎች ይያዛሉ።

> «... ወደ መልካሚቱም ምድር ይገባል፤ ብዙ አገሮችም ይወድቃሉ። ነገር ግን ኤዶምያስና ሞዓብ ከአሞንም ልጆች የበለጡት ከእጁ ይድናሉ»/ዳን. 11፡41/።

በራእይ 13፡15–16 ሐሰተኛው ነቢይ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንደሰጠው ምስሉም የማይሰግዱለትን ተናግሮ እንደሚያስገድል ሰዎች ሁሉ ምልክትን እንዲያደርጉ እንደሚያስገድድ ተገልጸአል።

በራእይ 14፡10–11 ደግሞ ምልክቱን በቀኝ እጁ ወይም በግምባሩ የሚቀበልና ለምስሉም የሚሰግድ በእሳት ባሕር ውስጥ እንደሚጣል የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። እንግዲህ ተቃዋሚው ክርስቶስ በመላው ዓለም የሚገዛ ፈላጭ ቆራጭ ገዥ ከሆነና በዓለም ሁሉ ላይ ሥልጣን ካለው፥ በዚያን ጊዜ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁለት ምርጫ ብቻ ይኖራቸዋል። ምርጫዎቹም፥

> አንደኛ፥ ምልክቱን ተቀብለው በሕይወት መኖር።
>
> ሁለተኛ፥ ምልክቱን አንቀበልም፤ ለአውሬውና ለምስሉም አንሰግድም ብለው በተቃዋሚው ክርስቶስ መገደል።

ይህ ማለት እንግዲህ ጌታ ኢየሱስ ሺህ ዓመት ለመንገሥ ወደ ምድር ሲመጣ ምልክቱን ያልተቀበሉ ሁሉ ተገድለው ስለሚቆዩት በሕይወት የሚያገኛቸው ሁሉ የአውሬውን ምልክት የተቀበሉና ለምስሉ የሰገዱት ብቻ ናቸው ማለት ነው?

እውነቱ ግን ተቃዋሚው ክርስቶስ በአሥሩ መንግሥታት ላይ እንደሚነግሥና ሌሎች የተወሰኑ የሜካባቢውን አገሮች በጦርነት እንደሚይዝ ነው። በእነዚያ አገሮች የሚኖሩ ሁሉ ለምስሉ እንዲሰግዱ ምልክቱንም ካልተቀበሉ ሊሸጡ ወይም ሊገዙ እንዳይችሉ ሕግ ይወጣል። ከዚያም በመቀጠል በያዛቸው አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ምክንያት የዓለምንም ኢኮኖሚ ለመቆጣጠርና ሌሎች አገሮችም በኢኮኖሚው ዘርፍ ከእርሱ ጋር ጎብረት እንዲኖራቸው ምልክቱን እንዲቀበሉና የእርሱም ተከታዮች እንዲሆኑ ለማድረግ ይሞክራል።

ከእስራኤል ጋር ያደረገውን የሰባት ዓመታት ቃል ኪዳን ካፈረሰ በኋላ እስራኤልንና የአካባቢውን አገሮች ይይዛል። ከዚያም ከክርስቶስ ጋር ለመዋጋት አርማጌዶን ወደተባለው ስፍራ ጦሩን

ሁሉ ያስከትታል/ዳን.8፡9-13፤ 24-25፤ 9፡26-27፤ ራእይ 16፡16/።

ተቃዋሚው ክርስቶስ በዘንዶው ኃይል የሚሠራ ቢሆንም፥ ከሕዝቡ መካከል የሚወጣ ሰው/Human being/ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው በሦስት ዓመት ተኩል የግዛት ዘመኑ በመላው ዓለም በጦርነትና በአጋንንት ኃይልና ምልክት የራሱን አዲስ ሃይማኖት ማስፋፋትና ማዳረስ እጅግ ከባድና የማይሞከር ነገር ነው።

ወንጌል በጌታ ኢየሱስ፥ በሐዋርያት፥ ያለፉትን ቅዱሳን ጨምረን በብዙ ሚልዮን በሚቆጠሩ ቅዱሳን፥ በመላእክት፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፥ በድንቅና በተአምራት ተሰብኳል። ወንጌላችን ቢያንስ ለ1990 ዓመታት ተሰብኳል። ሆኖም ግን እስከ ዛሬ ድረስ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ወንጌልን አልሰሙም። ብዙዎችም የጌታ ኢየሱስን ስም እንኳን ሰምተው አያውቁም። ይልቁንም በሰይጣን ኃይል የሚመራ ሰው ሲነሣ አሥር መንግሥታትን የያዘው አንድ ሰው እንዴት በሦስት ዓመት ተኩል ውስጥ የራሱን አዲስ ሃይማኖት በመላው ዓለም ሊያስፋፋ ይችላል? ሐቁ እንግዲህ ተቃዋሚው ክርስቶስ በጦርነት ከያዛቸውና ከተቆጣጠራቸው አገሮች ውስጥ እንኳን የአውሬውን ምልክት ሳይቀበሉ፥ ባለመቀበላቸውም በአውሬው ሳይገደሉ የሚያመልጡ ሰዎች እንደሚኖሩ ነው።

> *«እጆን በአገሮች ላይ ይዘረጋል፤ የግብፅም ምድር አታመልጥም»/ዳን. 11፡42/።*
>
> *«በኢየሩሳሌም ላይ ከመጡት ከአሕዛብ ሁሉ የቀሩት ሁሉ ለንጉሡ ለሠራዊት ለጌታ እግዚአብሔር ይሰግዱ ዘንድ የዳስ በዓልንም ያከብሩ ዘንድ በየዓመቱ ይወጣሉ... የግብፅም ወገን ባይወጣ ወደዚያም ባይመጣ እግዚአብሔር የዳስ በዓልን ያከብሩ ዘንድ የማይወጡትን አሕዛብ የሚቀሰፍበት ቸንፈር በእርሱ ላይ ይሆናል... »/ዘካ. 14፡16-19/።*

ተቃዋሚው ክርስቶስ የግብፅን ምድር እንደሚይዝ በዳንኤል 11፡42 ላይ ተገልጾአል። ነገር ግን ከግብያውያን እንኳን በተቃዋሚው ክርስቶስ ዘመን ምልክቱን የማይቀበሉና የማይሰግዱ በዚህም ምክንያት በአውሬው የማይገደሉ በሺህ ዓመቱ መንግሥት ለሚነግሠው ለንጉሡ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሰግዱ ዘንድ ከግብፅ ወደ ኢየሩሳሌም የሚወጡ አሉ። ከምድር አሕዛብ ሁሉ እንደዚሁ ለንጉሡ ለሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይሰግዱ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣሉ። ስለዚህ ተቃዋሚው ክርስቶስ በተወሰነ አገሮች ላይ የሚሠለጥን እንጂ የመላው ዓለም ፈላጭ ቆራጭ ገዥ አይሆንም።

5
አሦራዊው

«አሦራዊውም ወደ አገራችን በገባ ጊዜ ምድራችንንም በረገጠ ጊዜ ሰባት እረኞችና ስምንት አለቆች እናስነሣበታለን። የአሦርንም አገር በሰይፍ የናምሩድንም አገር በመግቢያው ውስጥ ያፈርሳሉ። አሦራዊውም ወደ አገራችን በገባ ጊዜ ዳርቻዎቻችንንም በረገጠ ጊዜ እርሱ ይታደገናል» /ሚክ. 5:5-6/።

ተቃዋሚው ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከተጠራበት መጠሪያዎች አንዱ አሦራዊ የሚለው ነው።

አሦራዊው ማነው?

በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ አሥራ አንድ የእግዚአብሔር ቃል በተለያዩ ዘመናት ስለተነሡት የሁለት አገር ነገሥታት ማለትም የሰሜንና የደቡብ አገር ነገሥታት ይናገራል። የእግዚአብሔር ቃል «የሰሜን ንጉሥ» ሲል ከእስራኤል በስተሰሜን ያለው አገር ንጉሥ ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው። ከእስራኤል በስተሰሜን ቢያንስ ሦስት ወይም አራት አገሮች አሉ። እነርሱም ቱርክ፥ ሶቭየት ኅብረት፥ ዩክሬይንና ሩሲያ ናቸው።

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በተለያዩ መጠሪያዎች የተጠቀሰው የሰሜኑ ንጉሥ /የመጨረሻው ዘመን ተቃዋሚው ከርስቶስ/ የሚመጣው ከየትኛው የሰሜን አገር ነው? ከአሦር? ከቱርክ? ወይስ ከሩሲያ? በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ አሥራ አንድ ያለውን የትንቢት ቃል ዛሬ ባለንበት ዘመን ላይ ሆነን ስናየው በሁለት ተከፍሎ እናገኘዋለን።

ከቁጥር 1–34 የተፈጸመ ትንቢት

ከቁጥር 35–45 ገና ያልተፈጸመና የምንጠብቀው ትንቢት

ዳንኤል ትንቢቱን በተናገረበት ዘመን ሙሉው ምዕራፍ ያልተፈጸመ ሲሆን፥ ከዚያ በኋላ ግን እስከ ቁጥር 34 ያለው ተፈጽሞ እናገኘዋለን።

የተፈጸመ ትንቢት

/ዳን። 11፡1–34/

«አሁንም እውነትን አሳይሃለሁ። እነሆ፥ ሦስት ነገሥታት ደግሞ በፋርስ ይነሣሉ። አራተኛውም ከሁሉ ይልቅ እጅግ ባለጠጋ ይሆናል። ባለጠግነቱም በበረታ ጊዜ በግሪም መንግሥት ላይ ሁሉን ያስነሣል። ኃያልም ንጉሥ ይነሣል። በትልቅ አገዛዝም ይገዛል። እንደ ፈቃዱም ያደርጋል። እርሱም በተነሣ ጊዜ መንግሥቱ ይሰበራል። ለዘሩ ግን አይከፋፈልም። እንደ ገዛበትም አገዛዝ አይሆንም። መንግሥቱ ይነቀላልና ከነዚህም ለሌሎች ይሆናልና» /ዳን. 11፡2–4/።

ይህ ክፍል የሚያሳየን፥ በፋርስ ላይ ከሚነሡት አራት ነገሥታት ጀምሮ ለአራት በተከፋፈለው የግሪም መንግሥት ላይ እስከ ነገሡት አራቱ የአሌክሳንደር ጄኔራሎች ዘመን ድረስ ያለውን ነው።

የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ እስከሞተበት እስከ 527 ዓ.ዓ የነገሠ ሲሆን፥ ከርሱ ሞት በኋላ ልጁ ካምቢሰስ ከ527–520 ዓ.ዓ ድረስ ነግሦ አል።

ከዚህ በኋላ ዳርዮስ አንደኛ ከ520–485 ዓ.ዓ. ለ35 ዓመታት ሦስተኛው የፋርስ መንግሥት ንጉሥ ሆኖ ሲነግሥ፥ ከርሱ

በኋላ አራተኛው የፋርስ ንጉሥ በመሆን ንጉሥ አርጤክስስ ከ485–464 ዓ.ዓ. ለ21 ዓመታት ነግሦ አል።

የእግዚአብሔር ቃል በቁጥር ሦስት ላይ እንደሚናገረው፥ ከዚህ በኋላ በታላቅ አገዛዝ የገዛው ኃያል የሆነው የግሪክ ንጉሥ ታላቁ አሚክሳንደር ሲሆን፥ በቁጥር 4 ላይ እንደተገለጸው ከአሥራ ሦስት ዓመታት አገዛዝ በኋላ ታላቁ እስክንድር ሲሞት የግሪክ መንግሥት ለአራት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፋፍሎ በአራት የአሌክሳንደር ጄኔራሎች ተገዝቷል።

1. ፕቶልሚ – ግብፅን ጨምሮ ደቡባዊ የአሌክሳንደርን ግዛት

2. ሴሉከስ – ሶርያንና ምሥራቃዊ የአሌክሳንደርን ግዛት የነበረውንና የቀድሞውን ባቢሎን

3. ካሳንደር – ግሪክንና ምዕራባዊውን የአሌክሳንደር ግዛት

4. ሊስማኩስ – ቱርክንና ሌሎቹን የሰሜን ግዛት ይዘው ነግሠዋል።

ከታላቁ አሌክሳንደር ጀምሮ የነዚህ ነገሥታትና የተከታዮቻቸው መንግሥት ዘመን በሮማውያን «ሄለኒስቲክ የአሌክሳንደራውያን ዘመን» በመባል የሚታወቅ ነው። በዓለም ላይ ስድስተኛ ሆኖ እስከመጣው እስከ ሮማውያን መንግሥት ድረስ /ከ336–100 ዓ.ዓ./ ቆይተዋል። በመጨረሻም የሮም መንግሥት ከሴሉኩስ አንዳንድ ምሥራቃዊ ግዛት በስተቀር ሶርያን ጨምሮ የሁሉንም ግዛት ወስዶ የቀድሞው የሮም መንግሥት ግዛት አድርጓቸዋል።

የደቡብና የሰሜን ንጉሥ

«የደቡብም ንጉሥ ከአለቆቹም አንዱ ይበረታሉ፤ እርሱም ይበረታበታል፤ ይሰለጥንማል። ግዛቱም ታላቅ ግዛት ይሆናል። ከዘመናትም በኋላ ይጋጠማሉ። የደቡቡም ንጉሥ ሴት ልጅ ታል ኪዳን ለማድረግ ወደ ሰሜን ንጉሥ ትመጣለች። የክንድዋ ኃይል ግን አይጸናም፤ እርሱና ክንዱም አይጸናም። እርስዋና እርስዋን ያመጡ የወለዳትም በዚያም ዘመን ያጸናት አልፈው ይሰጣሉ»/ዳን. 11:5–7/።

የእግዚአብሔር ቃል የደቡብ ንጉሥ ብሎ የሚጠራው የግብፅ ንጉሥ ፕቶልሚና የሰሜኑ ማለትም የሶርያ ንጉሥ ሴሉኩስ

ይበረታሉ። የሰሜኑ ንጉሥ ግን ከደቡቡ ይልቅ ኃያል ይሆናል። ከዘመናትም በኋላ የደቡብ ንጉሥ ሴት ልጅ በርንቄ ከሦስተኛው የሰሜን ንጉሥ አንትኮስ ጢኦስ ጋር ጋብቻ በመመሥረት ቃል ኪዳን ያደርጋሉ። ሆኖም ግን አንቲኮስ በርንቄን ለማግባት ብሎ የቀድሞ ሚስቱን ላኦድቅን በማባረሩና ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላም መልሶ አምጥቷት አብራው በመኖሯ አንቲኮስንና በርንቄን ከነልጃቸው በመርዝ ገድላ በ280 ዓመተ ዓለም የራሷን ልጅ ዳግማዊ አንቲኮስ ብላ በሶሪያ ላይ አንግሣዋለች። ይህም በመሆኑ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው በደቡብ ንጉሥ ሴት ልጅና በሰሜን ንጉሥ መካከል የተደረገው የጋብቻ ቃል ኪዳን ሳይጸና ይቀራል።

> *«ነገር ግን ከሥርዋ ቁጥቋጥ አንዱ በሰፍራው ይነሣል። ወደ ሠራዊቱም ይመጣል። ወደ ሰሜንም ንጉሥ አምባ ይገባል። በላያቸውም ያደርጋል። ያሸንፍማል። አማልክቶቻቸውንና ቀልጠው የተሠሩትን ምስሎቻቸውን ከብርና ከወርቅም የተሠሩትን ዕቃዎች ወደ ግብፅ ይማርካል። እሰከ ጥቂትም ዓመት ድረስ ከሰሜን ንጉሥ ጋር ሳይዋጋ ይቀመጣል»/ዳን. 11:7-8/።*

ከበርንቄ ሞት በኋላ ከርሷ ጋር አንድ ሥር የሆነው ወንድሟ የግብፅ ንጉሥ ፕቶልሚ ሦስተኛ ለእህቱ በቀል በ246 ዓ.ዓ. ሶርያን ይወጋል። ያሸንፍማል። ይህም ሆኖ፥ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የሶርያ ንጉሥ አንቲኮስ የግብፅ ንጉሥ ፕቶልሚ 4ኛን ወግቶ ያሸንፋል። ከዚህም ድል በኋላ የሰሜን ንጉሥ አንቲኮስ ወደ አይሁድ ምድር ይገባል /ዳን. 11:13-16/።

ምንም እንኳ ግብፅን በጦርነት ያሸነፉት ቢሆንም፥ የግብፅ ንጉሥ ፕቶልሚ እንዲገዛት ሲል ሴት ልጁን ይሰጠዋል። እርሷ ግን የእግዚአብሔር ቃል በቁጥር 17 እንደሚለው የአባቷን አሳብ ለማስፈጸም ከአባቷ ጋር አትጸናም። የደቡብ ንጉሥ ከሆነው ባሏ ጋር በመተባበር የአባቷን አሳብ ትቃወማለች።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ የሶርያ ንጉሥ አንቲኮስ ሴሉኩስ ይሞታል። በስፍራው አንቲኮስ ኤፒፓነስ ይነግሣል። ኤፒፓነስም ወደ ግብፅ በመዝመት ግብፅን ይወጋታል። የግብፅ ንጉሥ ምንም እንኳ ታላቅ ሠራዊት ቢኖረውም፥ በመካከሉ ሰዎች ስለ ከዱትና ስለ ገደሉት ሠራዊቱ ይሸነፋል።

> *«... ነገር ግን አሳብ በርሱ ላይ ይፈጥራሉና አይፀናም። መብሉንም የሚበሉ ሰዎች ይሰብሩታል፤ ሠራዊቱም*

ይጎርፋል፤ ብዙዎችም ተገድለው ይወድቃሉ» /ዳን. 11:21-26/።

በዚህ ስፍራ የምናገኘው የሰሜን ንጉሥ አንቲኮስ ኤፒፓነስ ከእስራኤል ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን በማፍረሱና ቅዱሳንን በመግደሉ በመጨረሻው ዘመን ከሚመጣው የሰሜን ንጉሥ ማለትም ተቃዋሚው ክርስቶስ ጋር ይመሳሰላል።

ከዚህ በላይ የቀረበው የዳንኤል 11:2-34 ትንቢት አስቀድሞ ከላይ ባየዊው መልኩ የተፈጸመ ሲሆን፥ ከቁጥር ሠላሳ አምስት ጀምሮ ላለው ያልተፈጸመ ትንቢት የእግዚአብሔር ቃል የሰሜንና የደቡብ ንጉሥ ብሎ የሚናገረው ስለ እነማን እንደሆነ ግንዛቤ እንዲኖረን ይረዳናል።

ከዳንኤል 11:35 ጀምሮ የምናገኘው የሰሜን ንጉሥ የእግዚአብሔር ቃል ስለ እርሱ የሚናገረው የመጨረሻው ዘመን ተቃዋሚው ክርስቶስ መሆኑን እንረዳለን።

የዳንኤል አሥራ አንዱ የሰሜን ንጉሥ ባሕርይ በዳንኤል 7:25፤ 8:25፤ ራእይ 13:6 ከተባለው የተቃዋሚው ክርስቶስ ባሕርይ ጋር ይመሳሰላል።

> «ንጉሡም እንደ ፈቃዱ ያደርጋል። ራሱንም ከፍ ከፍ ያደርጋል። በአማልክት ሁሉ ላይ ራሱን ታላቅ ያደርጋል። በአማልክትም አምላክ ላይ በትዕቢት ይናገራል። ቁጣም እስኪፈጸም ድረስ ይከናወንለታል»/ዳን. 11:36/።
>
> «በልዑሉም ላይ ቃልን ይናገራል፤ የልዑልንም ቅዱሳን ይሰብራል»/ዳን. 7:25/።
>
> «በመታለሉ ተንኮልን በእጁ ያከናውናል፤ በልቡም ይታበያል... »/ዳን. 8:25/።
>
> «እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይም የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ»/ራእይ 13:6/።

ስለዚህም በዳንኤል 10:35-40 የተገለጸው የሰሜኑ ንጉሥ በመጨረሻው ዘመን የሚመጣው ተቃዋሚው ክርስቶስ መሆኑን እንረዳለን።

አሦራዊው የሰሜኑ ንጉሥ የሚመጣው ከየት ነው?

በአሕዛብ ዘመን እስራኤልን በመቃወም ከተነሡት መንግሥታት ሁለተኛውን ቁጥር የያዘው የአሦር መንግሥት ነው። የዚህም መንግሥት ግዛት ግብፅንና ሶርያን የቀድሞውን የባቢሎን ግዛት የሚያጠቃልል ነበር። በትንቢተ ሚልክያስ ምዕራፍ 5:5-6 በመጨረሻው ዘመን የሚመጣውንና እስራኤልንም ለማስጨነቅ ወደ ተስፋዱቱ ምድር የሚገባውን ተቃዋሚው ክርስቶስን የእግዚአብሔር ቃል «አሦራዊው» ይለዋል።

ሀ. የአሦር ንጉሥ

የቀድሞው የአሦራውያን ግዛት ከላይ ያየናቸውን አገሮች የሚያጠቃልል ከሆነ አሦራዊው ከየትኛው ክፍል ነው የሚመጣው? ከግብፅ? ከሶርያ፥ ከኤራን ወይስ ከኤራቅ? የዚህን ጥያቄ መልስ ለማግኘት የሚከተለውን እንመለከታለን።

1. ግብፅ

ተቃዋሚው ክርስቶስ የሰሜን ንጉሥ ተብሎ ተጠርቷል/ዳን. 11:40/። ግብፅ ግን በቀድሞው የአሦር ግዛት ሥር ብትሆንም በዳንኤል አሥራ አንድ ላይ የደቡብ መንግሥት ተብላ ተጠርታለችና የሰሜኑ ንጉሥ ግዛት ልትሆን አትችልም/ዳን. 11:6-8/። ከዚህም ሌላ ግብፅ ራሷ በተቃዋሚው ክርስቶስ የምትወጋ አገር ነች/ዳን. 11:42/።

2. ባቢሎን

ባቢሎን በአሦራውያን መንግሥት ግዛት ሥር የነበረች አገር ብትሆንም የምትዋሰነው በምሥራቅ እንጂ በሰሜን አይደለም። ስለዚህም ከዳንኤል ምዕራፍ አሥራ አንዱ የሰሜን ንጉሥ ጋር አንድ የሆነው አሦራዊ የሚወጣበት አገር ልትሆን አትችልም።

ለ. የሰሜን ንጉሥ

የእግዚአብሔር ቃል በዘመኑ መጨረሻ ላይ የሚመጣውን ተቃዋሚው ክርስቶስን/ዳን. 11፡35–45/ «የሰሜን ንጉሥ» ብሎ ይጠራዋል። የእግዚአብሔር ቃል ይህን ሲል ከእስራኤል በስተ–ሰሜን ያለው አገር ንጉሥ ማለት ነው። ሶርያ፥ ቱርክና ሩሲያ ከእስራኤል በስተ–ሰሜን የሚገኙ አገሮች ናቸው። እንግዲህ የሰሜኑ ንጉሥ አገር ማነው?

1. ሩሲያ

ተቃዋሚው ክርስቶስ ከቀድሞው የግሪክ መንግሥት ሥር ከሚወጡት አራት መንግሥታትና እነዚህን መንግሥታት አጠቃሎ ከያዘው ከቀድሞው የሮም መንግሥት ሥር ከሚወጡ አሥር መንግሥታት መካከል እንደሚወጣ የእግዚአብሔር ቃል በዳንኤል ምዕራፍ ሰባት እና ስምንት ይናገራል። ሩሲያ ግን በቀድሞዎቹ የግርክና የሮም መንግሥታት ሥር የነበረች አገር አይደለችም።

ተቃዋሚው ክርስቶስ አሦራዊው ተብሎ ተጠርቷል። ሩሲያ በቀድሞው የአሦር ግዛት ሥርም አልነበረችም። ሩሲያ የሰሜን መንግሥት ትሁን እንጂ የሰሜን ንጉሥ ተብሎ የተጠራውን የተቃዋሚው ክርስቶስን ታሪክ በያዘው በዳንኤል 11፡2–34 በተፈጸሙት ትንቢቶች ታሪክ ውስጥ የለችም። በዚያ ስፍራ የሚገኘው ትንቢት የተፈጸመውና በታሪክ የሚታወቀው የሰሜንና የደቡብ ነገሥታት የሶርያና የግብፅ ነገሥታት ናቸው። ስለዚህ ሩሲያ የሰሜኑ ንጉሥ አገር ልትሆን አትችልም።

2. ቱርክ

ቱርክ በቀድሞዎቹ የግሪክና የሮም መንግሥታት ሥር የነበረች አገር ብትሆንም፥ በዳንኤል 11፡2–34 ውስጥ ያለው የሰሜንና

6

የመጨረሻው መጨረሻ

ዛሬ በሬድዮ፥ በቴሌቪዥን፥ በጋዜጦች፥ በመጽሔቶችና በሌሎችም የመገንኛ ብዙሃን በገሃድ ከምንከታተላቸው ነገሮች የእግዚአብሔር ቃል ስለ መጨረሻው ዘመን የሚናገራቸውን ለሚያነብና ለሚመራመር ሰው ዓለማችን ወዴት እያዘመመች እንዳለች መረዳቱ አቀበት አይሆንበትም።

> *«ምሳሌንም ነገራቸው እንዲህ ሲል፦ በለስንና ዛፎችን ሁሉ እዩ፤ ሲያቆጠቁጥ ተመልክታችሁ በጋ አሁን እንደቀረበ ራሳችሁ ታውቃላችሁ። እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይህ ሁሉ መሆኑን ስታዩ የእግዚአብሔር መንግሥት በደጅ እንደቀረበ እወቁ» /ሉቃስ 21:29-31/።*

ጌታችን እንደተናገረው እንደዚህ ቃል ጌታ ኢየሱስ ከሐዋርያቱ ጋር ስለ ዳግም ምጽአቱና ስለ ዓለም መጨረሻ ምልክቶች የተናገረውና ዛሬ በዓለማችን እየሆኑ ያሉትን ስንመለከት፥ ይህ ትውልድ «የመጨረሻው መጨረሻ» ላይ እንዳለ ያመለክተናል።

- የእስራኤልና የመካከለኛው ምሥራቅ ሁኔታ
- የአውሮፓ ወደ አንድነት የመምጣት ሂደት

- በዓለማችን በተለያዩ ክፍሎች ያሉትን ጦርነቶች፥ ረሃብ፥ በሽታ፥ የምድር መናወጥ፥ ጎርፍና የመሳሰሉት አደጋዎች
- የእስያውን ክፍለ ዓለም ጨምሮ የዓለም በከፍተኛ ፍጥነት በቴክኖሎጂ ማደግ
- በቴሌቪዥን፥ በመጽሔትና በጋዜጦች የምንመለከታቸውና በዓለማችን በተለያዩ ክፍሎች የሚከናወኑ ሰይጣናዊ አሠራሮች፥ ይልቁንም ይህ ሰይጣናዊ አሠራር በግልጽ መካሄዱና ደጋፊዎች እያበዙ መሄዱን ስናይ፥ እያንዳንዱ ነገር ወደ መጨረሻው ዘመን እየፈጠነ እንዳለ እንረዳለን። ከዚህም በላይ፥ በዚሁ የመጨረሻ ዘመን የሚገለጠውን የተቃዋሚው ክርስቶስን መምጣት እያመቻቸና እያዘጋጀ መሆኑን እንገነዘባለን።

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 13 የአውሬው ቁጥር የሌለው ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንደማይችል እናነባለን። የሰይጣን አሠራርና ኃይሉ በማታለልና በማስመሰል ነው። ሰይጣን ሁልጊዜ የእግዚአሔር የሆነውን ነገርና አሠርሩን አስመስሎ በማቅረብ፥ ሰዎችን እያታለለ እንደ እግዚአብሔር ለመመለክ ይጥራል። አገልጋዮቹም እንዲሁ ያደርጋሉ።

> *«ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና» /2ኛ ቆሮ. 11:24/።*

እግዚአብሔር አብ ወልድ ልጁን ወደ እኛ እንደላከ፥ መንፈስ ቅዱስም በኢየሱስ የተነገረውን ወንጌል እውነትና የኢየሱስን አምላክነት በድንቅና በምልክት በመመስከር እንደሚያጸና ከቅዱሳት መጻሕፍት ዘገባ እንረዳለን። ይህንን በሚመስል አሠራር ዘንዶው /ሰይጣን/ በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ አሥራ ሦስት ከባሕር የወጣውን አውሬ ሥልጣን በመስጠት ወደዚህች ዓለም ይልከዋል።

> *«ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው» /ራእይ 13:2/።*

በአሥራ አንደኛው ቁጥር ላይ ከምድር ሲወጣ የምናየው አውሬም በፊተኛው አውሬ ሥልጣን በሰዎች ፊት ምልክት በማድረግ ለአውሬው ያሰግዳቸዋል።

«በፊተኛውም አውራ ሥልጣን በእርሱ ፊት ሁሉን ያደርጋል። አሳትንም አንኳ ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ ታላላቆችን ምልክቶች ያደርጋል። በአውሬውም ፊት ያደረግ ዘንድ ከተሰጡት ምልክቶች የተነሣ በምድር የሚኖሩትን ያስታል... » /ራእይ 13፡12፥ 13-14/።

እንደዚሁም ጌታ ከእስራኤል የተመረጡትን 144,000 አይሁዶች ምድርና ባሕርን ሊጎዱ ሥልጣን የሰጣቸው አራቱ መላእክት እንዳይጎዱቸው የጌታ መሆናቸውን የሚለይ ምልክት በግንባራቸው እንደሚያደርግላቸው ሁሉ፥ ሰይጣንም የራሱ የሆኑትን ሰዎች የሚለይበትና በኃይል አስገድዶ ለማስመለክ የሚጠቀምበት ምልክት አለው /ራእይ 7፡2-3፤ 13፡16-17/።

ይህን ምልክትም ሰዎች እንዲቀበሉ በሥጋ ለመኖር በሚያስፈልጓቸው ነገሮች ማለትም ምልክቱ የሌለው እንዳይገዛና እንዳይሸጥ በማድረግ ያስገድዳል። ይህ ምልክት የአውሬው ስም ወይም የስሙ ቁጥር ያለበት ነው። ስለሆነም ሰዎች ያለዚያ ምልክት ሊገዙ ወይም ሊሸጡ እንዳይችሉ በማድረግ ለአውሬው ምስል እንዲሰግዱ የሚያስገድድበት ነው። ዛሬ በዓለማችን እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ማቆጥቆጥ ጀምሯል።

በዓለማችን የሥልጣኔ ቁንጮ በሆኑት በአህጉረ አሜሪካና በአውሮፓ አገሮች የገንዘብ ካርድ አጠቃቀም ከተጀመረ ዓመታትን አስቆጥሯል። ይህም አሠራር በአሁኑ ዘመን ለሰው ልጅ የሚጠቅም በሚመስል ሁኔታ እነርሱ ዕድገትና መሻሻል በሚሉት መንገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ በመሄድ ላይ ይገኛል።

ሰዎች በገንዘብ ማውጫ ካርድ በማንኛውም ሰዓት ላይ ከባንክ ውጭም ይሁን ውስጥ በግድግዳ ላይ ከሚገኝ የገንዘብ ማውጫ ማሽን ገንዘብ ያወጣሉ። እንዲሁም በልዩ ልዩ የመገበያያ ቦታዎች፥ በቤንዚን ማደያዎች፥ በመኪና ማከራያዎች፥ በሕዝብ ቴሌፎኖችና በመሳሰሉት ስፍራዎች ያለምንም የገንዘብ ልውውጥ የገንዘብ ካርዳቸውን የኮምፒዩተሩ ማሽኑ ውስጥ በመክተትና የራሳቸውን የምሥጢር ቁጥር በመጠቀም ይገበያያሉ - ይገዛሉ፤ ይሸጣሉ።

ዛሬ የገንዘብን ልውውጥ የሚጠይቁ ማናቸውም የባንክና የንግድ ክፍሎች በሙሉ አሠራራቸውን ወደ ካርድ ሲስተም እየቀየሩ

ነው። ይህ በካርድ የመግዛትና የመሸጥ ዘዴ አሁን ባለበት ያቆም ይሆን ወይስ በቴክኖሎጂ ማደግ ሽፋን መልኩን እየቀየረ ይሄድ ይሆን? ይህና ይህንን የመሳሰለው አሠራር የሰው ልጅ ለችግሩ መፍትሔ ለማግኘት በሚያደርገው ጥረት የተከሰተ የዕድገት ውጤት ይሆን ወይስ ከጅርባ ሆኖ ይህንን ሁሉ የሚያቀናጅ ሌላ ኃይል ይኖር ይሆን? ይህ ነገር ወዴት ይሆን የሚያመራው? ሩጫውስ የሚገታው የቱ ጋ ነው?

በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ይልቁንም በአሜሪካንና በአውሮፓ የዚህ የገንዘብ ካርድ አሠራር እስከ አሁን ከነበረበት ሁኔታ ወደ ፊት ፈቀቅ ማለት እንደጀመረ ይስተዋላል።

ምንም እንኳን የገንዘብን ካርድ መጠቀም ገንዘብን ለመሥራት ከሚወጣው ወጪ ጊዜን ከመቆጠብና ከሌሎችም አንፃር ያበረከተው ድርሻ ቀላል ባይሆንም፥ አሁንም በሥልጣኔ ሊሻሻሉ የሚችሉ ችግሮች እንዳሉበት ይነገራል።

የካርድ መጥፋት፥ መሠረቅና ሌሎችንም ይልቁንም አዛውንቶችን ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ለማቃለል ሰዎች ምንም ካርድ ሳይዙ በካርዱ ሊያገኙ የሚችሉትን አገልግሎት ሁሉ የሚያገኙበት ሌላ አሠራር በአሜሪካ አገር ሙከራው ተሳክቶ አገልግሎት ለመጀመር እየጠበቀ ነው።

ይኸውም መንገድ በካርድ ውስጥ የምትገኘውንና ዋነኛውን ሥራ የምትሠራውን ትንሽ የኮምፕዩተር መሣሪያ በአንድ የሰውነት ክፍል ለምሳሌ በግንባር ወይም በእጅ ላይ በመቅበር ሰዎች መሣሪያዋ የተቀበረችበትን የሰውነት ክፍላቸውን ብቻ በባንክም ይሁን በሱፐር ማርኬቶች ለዚሁ አገልግሎት ለተዘጋጁት የኮምፕዩተር መሣሪያዎች በማሳየት የሚፈልጉትን ነገር መፈጸም ነው። ይህ ጥናት በአሜሪካን አገር በበግና በውሻ ላይ ተሞክሮ የተፈለገውን ውጤት አስገኝቷል። በሰው የሰውነት ክፍል ውስጥም ቢቀበር ለጤና ምንም ጉዳት እንደሌለው ተረጋግጧል።

ይኸው ጥናት በአውሮፓው ኅብረት መዲና በብራስልስ ተጠንቶ ውጤታማነቱ ስለታመነበት በተግባር ሊውል በዝግጅት ላይ ይገኛል።

አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንደነገሩኝ በአውሮፓ ኅብረት (EU) ውስጥ የሚሠራ የቤተ ክርስቲያናቸው አገልጋይ በሰውነት ውስጥ ለመቅበር ጥናት ተደርጎ ያለፈውንና የተዘጋጀውን ትንሽ

መሣሪያ አምጥቶ እንዳሳያቸውና ትንሿ መሣሪያም ምሥጢራዊ ቁጥር እንደተሰጣት፥ ያም ቁጥር «666» እንደሆነ አጫውተውኛል።

በሌላ ጊዜ እኚህን በEU የሚሠሩትን ከርስቲያን ወንድም አግኝቻቸው እንዳጫወቱኝ በአሁን ጊዜ ከገንዘብ ካርድ ሌላ *Smart Card* የተባለ ካርድ ተሠርቷል። ካርዱ በውስጡ የያዘውን የሕክምና መረጃ ሳይቀር ሙሉ ማንነቱንና ሌሎችንም ስለዚያ ሰው ለማወቅ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ የመዘገበ ሲሆን፥ ካርዱ ለርሱ በተዘጋጀ የኮምፕዩተር መሣሪያ ውስጥ ሲከተት ስለዚያ ግለሰብ ማንኛውንም መረጃ ይሰጣል። ይህ ካርድ የሚያከናውነው ተግባርና የሚሰጠውም ግልጋሎት (Samart) የተባለውን ስም ሊያሰጠው ችሏል። በአሁኑ ሰዓት የአውሮፓ ኅብረት ሠራተኞች በሙሉ የዚህ ካርድ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፥ በአሜሪካና በሌሎችም የአውሮፓ አገሮች የሚገኙ ታላላቅ ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች Smart Card መጠቀም ሳይጀምሩ እንዳልቀሩ ይገመታል።

እኚሁ ሰው በመቀጠል እንዳጫወቱኝ ውሻቸው ትከከለኛ ቦታውን በማያውቁት የአካል ክፍሏ *ማይክሮ* ቺፕስ የተቀበረላት ሲሆን፥ በዚያ ትንሽ መሣሪያ ውስጥ የውሻዋ ስም፥ ዕድሜ፥ አድራሻና የመሳሰሉ ሌሎችም መረጃዎች ተመዝግበዋል። ውሻዋ ብትጠፋ እንኳን በተቀበረላት ቺፕስ አማካኝነት በኮምፕዩተር ተመርምራ ሙሉ ማንነቷ የሚታወቅ መሆኑን ገልጸውልኛል።

ነገር ግን መሣሪያው ምናልባት በጆሮዋ ላይ እንደተቀበረ ከመገመት በስተቀር የት እንደተቀበረ የሚያውቁና በሰውነት ከፍሏ ላይ ምንም የሚታይ ምልክት እንደሌለም ገልጸውልኛል።

ይህ በውሻ የሰውነት ክፍል ውስጥ በመቅበርና ለሰዎች ደግሞ በ*Smart Card* አማካኝነት ስለ አንድ ሰው ማንነት ሙሉ መረጃን ለማግኘት የተጀመረው አሠራር ዛሬ ወዴት እያመራ ነው ያለው? ነገስ የት ይደርሳል?

ከእነዚህ ነገሮች እንደምንረዳው በሰውነት ውስጥ ለመቅበር የታሰበው *micro Chips* ዓላማ የገንዘብን ልውውጥ ለተመለከተ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፥ አንድን ሰው ሙሉ ማንነቱን

በማወቅ ለሚቆጣጠረው ኮምፕዩተር እስረኛና ተገዢ የማድረግም አሳብ አለው።

ሰዎች ይህንን ቺፕሰ ከተቀበሉ ወደፊት ተሠርቶ በማዕከላዊነት በሚቀመጠው ኮምፕዩተር ቁጥጥር ሥር ይወድቃሉ። ሲበሉ፥ ሲጠጡ፥ ሲሠሩ፥ ሲተኙ ሁሉ ኮምፕዩተሩ ይቆጣጠራቸዋል። ምልክቱን የሚቀበሉ ሁሉ የግል ነፃነት አይኖራቸውም። ለኮምፕዩተሩ ከተነገረው ከዚያን ዘመኑ ገዢ ፈቃድ ውጪ መሄድ አይችሉም። አንድ ቦታ ተቀምጠ የሚቆጣጠራቸው ኮምፕዩተር ስለ እነርሱ እንቅስቃሴ ይናገራልና።

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 13 ላይ የምናገኘውና ለርሱ የማይሰግዱለትን የሚያሰገድለው ትንፋሽም የተሰጠው የአውሬው ምስል ይኼ በዘመናችን ሊሠራ ያለው ታላቁ ኮምፕዩተር ይሆን?

የአውሬው ምስል ተጠሪነቱ ለአውሬው ነው። ለምስሉ የሚሰግዱ ለአውሬው ሰገዱ ማለት ነው። ወደዚህ ኮምፕዩተር አሠራርም ስንመጣ ኮምፒዩተሩ የሚሞላው ገዢው በሚፈልገው አሳብ ሆኖ፥ የገዢውን ፈቃድ ብቻ ነው የሚፈጽመውና የሚያስፈጽመው። በገዢው ውስጥ ያለ ፈቃድና ፍላጎት በኮምፒተሩ ውስጥም አለ።

ስለዚህም ለዚህ ኮምፒተር ፈቃድ የማይታዘዙና ኮምፕዩተሩ ሊያየው ከሚፈልገው መንገድ ውጪ የሚሄዱትን ሁሉ ለፈቃዱ እንዳልተገዙ (እንዳልሰገዱለት) በመገንዘብ ለአውሬው ወይንም ለዚህ ሥራ ለተዘጋጁት ክፍሎች ያሳውቅና ያስቀጣል።

ለኮምፕዩተሩ ፈቃድ ያልተገዙ (ያልሰገዱ) አሳቡን በውስጡ ላስቀመጠው ገዢ ፍቃድ አልተገዙም ማለት ነውና።

«የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሊያሰገድላቸው ለአውሬውም ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው። ታናናሾችና ታላላቆችም ባለጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቁጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ» /ራእይ. 13፥15-17/።

ከላይ ያቀረብሁት አሳብ የአውሬውና የምስሉ መገለጥ በቀጥታ በዚህ መልክ ይሆናል ለማለት ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል

የተጻፈውን እውነት አሁን በዓለማችን እየተፈጸሙ ካሉ ነገሮች አካሄድ ጋር ስናገናዝበው ምናልባት እንዲህ ሊሆን ይችላል ለማለት ነው። በርግጥም ሊሆን ይችላል።

የመጨረሻው ዘመን አውሬ የስሙ ቁጥርና ምልክት አሠራር ጅማሬ ሰዎች በመገደድ እንዲቀበሉት የማያደርግና የአምልኮ መልክም ያልያዘ ሊሆን ይችላል። በሥልጣኔ መልክ፥ ገንዘብ በሚቆጥብ ወይንም ለገዢውም ሆነ ለሻጩ ከጊዜም ሆነ ከሌሎች ወጪዎች ቁጠባ፥ ብሎም ከሌሎች ለጊዜው በሰው አእምሮ መልካም ከሚመስሉ ምክንያቶች አንጻር ሰዎች ራሳቸው በሚፈልጉትና በፈቃዳቸው በሚመርጡበት መንገድ የሚሠራ ሊሆን ይችላል። ይህ ሆኖ፥ አጀማመሩም ሆነ ፍጻሜው በሰይጣን የታቀደ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው፥ ሰዎች በግድ የአውሬው ተከታይና አምላኪ እንዲሆኑ ወደሚያደርጋቸው አሠራር (System) እየመራቸው ይገኛል።

ይህ ገንዘብን የማግለል አሠራር ለጊዜው አንዳንድ የፖለቲካ ሰዎችንና የሀሺሽ ነጋዴዎችን ደስ አላሰኘም። የፖለቲካ ሰዎቹ ለሚቀበሉት ጉቦና ሕጋዊ ያልሆነ የገንዘብ አጠቃቀም ስለማያመቻቸው ሲሆን፥ የሀሺሽ ነጋዴዎችም ንግዳቸው በጥቁር ገበያ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ገንዘብ የሌለበትና ባንኮችን ማዕከላዊ የሚያደርግ የንግድ ልውውጥ ስለሚያመቻቸው ነው።

ነገር ግን የዓመፅ ሰው የሆነው የተቃዋሚው ክርስቶስ መንግሥት ለነዚህ ክፍሎች የአመፅ አሠራር መፍትሔ የሚያጣላቸው አይመስልም።

አውሬው አገሮችን በጦር ኃይል እንደሚይዝ ሁሉ በሚቆጣጠራቸው አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት አማካኝነት ሌሎች አገሮችንም ሆነ በየዛችው አገሮች ውስጥ የሚኖሩትን ሕዝቦች የኢኮኖሚው ጥገኛ ለማድረግ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች ዋነኛው የስሙ ቁጥሩና ምልክቱ አሠራር ነው። ይህንንም ከሚያመቻችለት መንገድ አንዱ ባንኮችን በቀላሉ ለመቆጣጠር እንዲችል ትላልቅ ባንኮችን አንድ ማድረግ ነው። ይህንንም ለማድረግ አንዳንድ ባንኮች በዝጅግት ላይ ይገኛሉ።

በቅርቡ አንድ እኔ የማውቀው ባንክ ለደንበኞቹ በሙሉ አንድ ደብዳቤ ልኳል። በደብዳቤውም የሰፈረው ፍሬ ሀሳብ፥ ባንኩ ከሌሎች ሁለት የታወቁ ባንኮች ጋር ውኅደት ለመፍጠር

እንዳሠበና ይህ አሠራሩ አገልግሎቱን በፈት ያሠጠው ከነበረው በላይ ውጤታማ እንደሚያደርገው ያመነበት መሆኑን በመግለፅ ደንበኞቹ በሙሉ ለዚህ አሠራሩ ያላቸውን ድጋፍ በላከው ተመላሽ በሚሆን ወረቀት ላይ አስፍረው እንዲልኩለት የሚጠይቅ ነበር። በአሁኑ ሰዓት ውህደት አድርገውና ስማቸውን ለውጠው በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

አሁንም ይህ አካሄድ ወዴት ነው የሚያመራው? ወደ አድገት? ወይስ ወደ ዘመኑ ፍጻሜ አሠራር? ለመሆኑ በዚህ ባለንበት የዘመን መጨረሻ ላይ የሳለማችን በአስደናቂ ፍጥነት በቴክኖሊጂ መምጠቅ ከየት'ና እንዴት የመጣ፣ ወዴትስ የሚሄድ ይመስልዎታል?

"U.F.O." እየተባሉ ስለሚጠሩት ፍጥረቶች ምን ያስባሉ?

በጡረታ ላይ ያሉ ዊልያም ኩፐር የሚባሉ የአሜሪካን የባሕር ኃይል የመረጃ መኮንን ሻለቃ ጆንሊር (አባታቸው የሊር ጄት ኮርፖሬሽንን የመሠረቱት) እና ዊልያም እንግሊዝ የተባሉ የአየር ኃይል መኮንን ለብዙ ዓመታት በአሜሪካ መንግሥት ለአሜሪካም ሆነ ለሌላው የሳለም ሕዝብ ተደብቆ የቆየውን መረጃ ገሃድ አድርገውታል። እኝህ ግለሰብ፣ «መንግሥት ይህን የቆየ ምሥጢር ለሕዝብ ማውጣት አለበት (enough is enough)» በማለት ስለ U.F.O የጻፉትና በ1997 መጀመሪያ ላይ ከኢንተርኔት የተገኘው ጽሑፍ የሚከተለው ነው፣

ይህንን ጽሑፍ ያወጡት ሰዎች እስከ ሕይወትም መሥዋዕትነት ድረስ ለመክፈል ቆርጠው ስለ U.F.O ('የሌላ ዓለም ፍጥረታት' እየተባሉ ስለሚጠሩት) እውነታውን ፈልፍለው ለሕዝብ ሊያሳውቁ ሞክረዋል። እነዚህ ሰዎች ምሥጢራዊ በሆኑ ፕሮጀክቶች ውስጥ የሠሩ ሲሆን፣ ከፍተኛ የሆነውን ምሥጢራዊ ጉዳይ የመመርመር ዕድል ያገኙ ናቸው። ተይዘው የነበሩትን ፍጥረታትና ይዘውት የመጡትንም አስደናቂ ቴክኖሊጂ በዓይናቸው አይተዋል።

ጹሑፉ እንዲህ በማለት ይጀምራል፣

ይህ መረጃ ሕይወትዎንና ነፃነትዎን ሊያድን ይችላል። መረጃውም የሌላው ዓለም ፍጥረታት በመሬት ላይ መገኘታቸውን የሚያሳይ ነው።

የሕዋ ጦርነት ለምን ተከሰተ? ለምን የሕዋ ምርምርና በድንገት የኮሚኒዝም መፈራረስ ተነዳኝ?

እየተካሄደ ያለው ነገር ምንድርነው? አንድ በጣም የሚያስፈራ ነገር እየሆነ ነው። የሕዝቡ አስተያየቶች እንደሚያሳዩት ዘጠና ከመቶው (90%) በላይ የሚሆነው የአሜሪካን ሕዝብ ስለ U.F.O ያውቃል። ከነዚህ ውስጥ 95% /ዘጠና አምስት ከመቶ/ የሚሆኑት ደግሞ መንግሥት ይህንን ነገር ከሕዝብ በምሥጢር እንደሚደብቀው ያምናሉ። ግን ለምን? መንግሥት ለምን ይፋዊ መግለጫ ለመስጠት ይፈራል? ምናልባት ሕዝቡ እንዳይረበሽ ይሆን? አይመስለንም። በተለይም የዚህ ዓይነቱ መግለጫ የጋለ ስሜትና ፍላጎት፡ ብሎም ከአብያተ ክርስቲያናት አካባቢ ጥያቄ ቢያስከትል እንጂ አያሸብርም። እንግዲያስ ለምን ተደበቀ?

ሰለ ዩፎዎች በታሪክ በተለያየ ወቅት ተጠቅሷል። እንደ በራሪ ወፍና ያልታወቀ አካል በማለት በተለያየ የታሪክ መረጃ ተጠቅሷል።

በ1940ዎቹ ውስጥ የነዚህ ፍጥረታት በርካታ በራሪ አካላት በአሜሪካና በሌሎች አገሮች ተመተው ወድቀዋል። ከነዚህም E.B.E. የሚል መጠሪያ በተሰጠው በአንዱ ውስጥ ጥቂት የሞቱና አንድ ደግሞ በሕይወት ተገኝቷል።

እ.አ.አ. በ1953 ዓ.ም. የጠፈር ተመራማሪዎች ከጠፈር ወደ ምድር እየተምዘገዘገ በመውረድ ላይ ያለ አንድ አካል ይመለከታሉ። በመጀመሪያ አስትሮይድ የሚባል በማርስና በጁፒተር መካከል ሆኖ በፀሐይ ዙሪያ የሚዞር ኮኮብ የሚመስል አካል መስሏቸው ነበር። በኋላ ግን በተጠናከረው መረጃ መንኮራኩር ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ። ፕሮጄክት ሲግማና ፕሮጄክት ፕላቶ የፍጥረታቱን የሬድዮ ግንኙነት በኮምፒተር ቋንቋ በመጠቀም ይጠልፉታል። ወደ መሬትም እንዲያርፍ በማመቻቸት ከነዚህ ፍጥረታት ጋር ፊት ለፊት ለመገናኘት በቅተዋል።

ከጥቂት ጊዜ በኋላም እነዚህ ሰው-መሰል ፍጥረታት ከአሜሪካ መንግሥት ጋር በመገናኘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እንዲያደርጉ ይጠይቃሉ።

> 1ኛ. ራሳችንን የምናጠፋበት መንገድ ስለሆነ የኒውክሌር መሣሪያዎቻችንን እንድናጠፋ

2ኛ. እርስ በርስ መገዳደላችንን እንድናቆም።

3ኛ. መሬትን መበከልንና ሀብቷን መቦጥቦጥን እንድናቆምና እርስ በርሳችን በመስማማት እንድንኖር። ሆኖም እነዚህን ጥያቄዎች ፕሬዚዳንት አይዘነሐዋር ሳይቀበሉት ቀርተዋል።

ከዚህ በኋላም እ.አ.አ. በ1954 ዓ.ም. ዜታ ራቲሱሉ ከሚባለው የሕዋ ክልል አካባቢ ነን የሚሉና ግሬይስ በመባል የሚታወቁት የነዚህ ፍጥረታት ዘር በሆሎማን አየር ኃይል ማረፊያ ላይ ያርፋል። እነዚህም ፍጥረታት፥ የሚኖሩበት ዓለም እየጠፋ መሆኑን ገልጸው፥ ዘራቸውን ለማዳን የሚችሉበትን የጄኒቲክ ምርምር ለማካሄድ በምድር ላይ ክልል እንዲሰጣቸውና እነርሱም የዚህን ለውጥ ቴክኖሎጂ እንደሚሰጡ ይናገራሉ። ፕሬዚደንት አይዘነሐወርም ተገናኝተዋቸው ከዚህ በታች ባሉት ስምምነቶች ይፈራረማሉ።

1. እነርሱ በእኛ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገቡ እኛም በእነርሱ ጉዳይ ጣልቃ እንዳንገባ።

2. በምድር ላይ ያለውን ኑሮአቸውን በምሥጢር እንድንጠብቅ።

3. እኛም በቴክኖሎጂ በከፍተኛ ሁኔታ እንድናድግ እንዲያደርጉን።

4. ለምርምር የሚያስፈልጉዋቸውን ሰዎች በተወሰነ ደረጃ አፍነው እንዲወስዱና ምርምራቸውን ከጨረሱ በኋላ ሰዎቹ መወሰዳቸውን እንኳን ሳያውቁ ከተወሰዱበት ቦታ እንዲመልሷቸው።

5. የመኖሪያ ስፍራ ከመሬት በታች በአራት ማዕዘናዊ ቦታ ማለትም በኡታህ (Utah)፥ ኒው ሚክሲኮ (New Mexico)፥ ኦሪዞና (Arizona) እና ኮሎራዶ (Colorado) እንዲገነባላቸው ሲሆን፥ ሌላም ድሪም ላንድ (Dream Land) በመባል የሚታወቅ ከክልል 51 ደቡብ 7 ማይልስ ርቆና S-4 በመባል የሚታወቅ በኔቫዳ (Nevada) እንዲገነባላቸው ተጠይቋል። ይህንኑም ግንባታ ለማካሄድ፥ «በጦርነት ጥቃት ጊዜ ፕሬዚዳንቱንና ሌሎች ባለሥልጣናትን ለመጠበቅ ከመሬት በታች የሚሠራ መኖሪያ» በማለት በነጩ ቤተ መንግሥት

ወታደራዊ ጽ/ቤት በብዙ ቢለዮን ዶላር ወጪ የሚሆንበት ሁኔታ ተወጥቶአል።

ይህን ጉዳይም የሚከታተል (Majority Twelve) (MJ 12) ብዙሃን 12 የሚባል ቋሚ ኮሜቴ በፕሬዚዳንቱ የተቋቋመ ሲሆን፥ ይህም የF.B.I ዳይሬክተር የሆኑትን ጄ. ኤድጋር ሁቨርንና በውጪ ግንኙነት ክፍል በአመራር ላይ ያሉትን «ብልሆቹ ሰዎች» በመባል የሚታወቁትን ስድስት ሰዎች ይጨምራል። በኋላም ሌሎች ከትሬካተራል ኮምሽን ውስጥ ገብተዋል። ጆርጅ ቡሽ፥ ጉርደን ዲንና ብሬዘዚንስኪም ከእነዚህ መካከል ነበሩ።

ይህ ኮሜቴ እንዳረጋገጠው ለእነዚህ ፍጥረታት ፕሮጀክት ማስኬጃ ለሚያስፈልገው ገንዘብ ማግኛ ዘዴ አንዱ መንገድ ሕገ ወጥ የዕፅ ንግድ ማካሄድ እንዲሆን የአመራሩ ኃይላት ወስነዋል።

የውጪ ግንኙነት ምክር ቤት አባል የሆነው አንድ ግለሰብ ይህን ሥራ በተቀላጠፈ ሁኔታ ሊያደርገው ራሱን አቅርቧል። ስሙም ጆርጅ ቡሽ ይባላል። አሠራሩም ከደቡብ አሜሪካ ተጭኖ በዓሣ ጀልባዎች ወደ አሜሪካ ግዛት እንዲገባና ከዚያ በመኪና ማጓጓዝ ነው። ይህም አሠራር ከፊታሾችና ከጉምሩክ ሠራተኞች ቁጥጥር ውጪ ነበር።

ዛሬ በዓለም ላይ የሚካሄደውን ሕገ ወጥ የዕፅ ንግድ C.I. A. ይቆጣጠራል። ነገር ግን አንድ ነገር ሊታወስ ይገባል። ለልጆቻችን በመጀመሪያ ዕፅ የሸጠው ጆርጅ ቡሽ ነው። ገቢውም የሚውለው ለፍጥረታቱ ከምድር በታች ለሚሠራው የመኖሪያ ሰፈር ነው።

እነዚህ ፍጥረታት ሰውን የሚበሉ ከሚባሉ ኪሌሎች ፍጥረታት ዓለምን ሊያድኗት እንደመጡ ይናገራሉ። ይህ ግን ከእውነት የራቀ ነው። ራሳቸው ሰው በላ ናቸው። ዋናው ዓላማቸው ዓለምን በሙሉ በአንድ መንግሥት ወደሚመራ አንድነት ለማምጣት ነው። አዲስ የዓለም አስተዳደር ሥርዓት። ጥቂት ዓለም አቀፍ ባንኮችን በመያዝና የዓለምን የገንዘብ ሲስተም ወደ አንድ በማምጣት በገንዘብ ሲስተሙ አማካኝነት ዓለምን ለመቆጣጠር ይፈልጋሉ።

ከዚህ በላይ ያቀረብኩት ጽሑፍ እነዚህ የቀድሞ መኮንኖች ከጻፉት የተወሰደ ነው።

እነዚህ ከሌላ ዓለም የመጡ ተብለው በነዚህ አሜሪካውያን መኮንኖች ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ፍጥረታት እነማን ናቸው? ሌሎች ፍጥረታትን የያዘ ሌላስ ዓለም አለ ወይ?

እግዚአብሔር አምላክ ዓለማትን ሁሉ እንደፈጠረ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። «ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» /ዕብ. 11÷3/።

የክዋክብት ተመራማሪዎች፥ እኛ የምንኖርባት ምድር ባለችበት Solar system ውስጥ 9 ትላልቅ ፕላኔቶችና 31 ሳተላይቶች እንዳሉና በዚህ ክልል ውስጥና ከክልሉም ውጪ ሀልቁመሳፍርት የሌላቸው ከዋክብት እንዳሉ ይናገራሉ።

የእግዚአብሔርም ቃል ከቁጥር በላይ የሆኑ ከዋክበት እንዳሉ ይናገራል።

> *«ወደ ሜዳም አወጣውና፦ ወደ ሰማይ ተመልከት። ከዋክብትንም ልትቆጥራቸው ትችል እንደሆነ ቁጠር አለው» /ዘፍጥ. 15÷5/።*

ጌታ ፀሐይን፥ ጨረቃን፥ ከዋክብትንና ዓለማትን ሁሉ ሲፈጥር እኛ ከምንኖርባት ዓለም ውጪ በሌላ ዓለም እንስሳን ወይም ሌሎች ፍጥረታትን እንደፈጠረ የእግዚአብሔር ቃል አይናገርም። ከዚህች ዓለም ውጪ ሰውም ሆነ ሰው-መሰል ፍጡር እንዳለ በእግዚአብሔር ቃል ተጽፎ አናገኝም። የእግዚአብሔር ቃል «ሠራዊት» ብሎ የሚጠራቸው 3 ነገሮች አሉ።

1. ሰዎችን

የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር ሠራዊት ተብለው ተጠርተዋል።

> *«እንዲህም ሆነ አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ከተፈፀመ በኋላ በዚያ ቀን የእግዚአብሔር ሠራዊት ሁሉ ከግብፅ ምድር ወጣ» /ዘፀ. 12÷41/።*

2. መላእክትን

«ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ» /ሉቃስ 2÷13/።

3. ከዋክብትን

«አይኖችህን ወደ ሰማይ አንሰተህ አምላክህ እግዚአብሔር ከሰማይ ሁሉ በታች ላሉት አሕዛብ የሰጣቸውን ፀሐይንና ከዋክብትንና የሰማይን ሠራዊት ሁሉ ባየህ ጊዜ ሰግደህላቸው አምልከሃቸውም እንዳትሰት ተጠንቀቅ» /ዘዳ. 4÷19/።

ከዚህ ውጪ ያሉት ሰይጣንና መላእክቱ ናቸው።

ስለዚህ U.F.O በመባል የሚታወቁት ፍጥረታት ሰይጣን ሰዎችን እያታለለ ዓላማውን ለመፈጸም ራሱን የገለጸበት አንድ የአሠራር መንገዱ ነው እንጂ ሌላ ምንም ዓይነት ፍጥረታት ሊሆኑ አይችሉም። አስቀድመን እንዳየነው ሰይጣን የዓለምን የገንዘብ አሠራር (System) ወደ አንድ በማምጣት የአውሬው ምልክት የሌለው ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል አዲስ ትእዛዝ ለሚያወጣው ለተቃዋሚው ክርስቶስ አሠራር በሥልጣኔ ሽፋን ዓለምን እያዘጋጀትና ለዚህም በዓለማችን ላይ አንድ ቁንጮ የሆነችውን አሜሪካንና የአውሮፓን ኅብረት እየተጠቀመ መሆኑን እንረዳለን።

ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር÷ «ምሳሌውንም ከበለሱ ተማሩ። ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቆጠቁጥ ያን ጊዜ በጋ እንደቀረበ ታውቃላችሁ። እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ በደጅ እንደቀረበ እወቁ» /ማቴ. 24÷32-33/ በማለት የዳግም ምጽአቱን ምልክት በጥንቃቄ እንዲጠብቁ አስጠንቅቋቸዋል። ለመሆኑ ከፍጻሜው ቋፍ ላይ ቆሞ ብዙ ምልክቶችን በመታዘብ ላይ የሚገኘው ይህ ትውልድስ ማስጠንቀቂያውን እንዴት ይመለከተዋል?

«ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ሰለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ በምድር ሁሉ ላይ በሚቀመጡ ሁሉ ላይ እንደ ወጥመድ ይደርስባቸዋልና ። እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ

ለማምለጥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ሰትጸልዩ ሁልጊዜ ትጉ» /ሉቃ. 21:34-36/።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተዘጋጅተን እየጠበቅነው ነው? ጌታችን እንደተናገረው ባላሰብናት ሰዓት ይመጣልና በምድር ያለንን ማንኛውንም የኑሮ ዕቅድ «ጌታ ዛሬ ቢመጣስ!» እያልን በማሰብና በመዘጋጀት እናድርገው።

ወንድሜ – እህቴ ሆይ፥ ጌታ ኢየሱስን ክርስቶስን በማመን የሚገኘውን የዘላለም ሕይወት አግኝተሃል/ሻል? የእግዚአብሔር ቃል በኢየሱስ ያላመነ የዘላለም ሕይወት እንደሌለው ይናገራልና በኢየሱስ ክርስቶስ ካላመንህ/ሽ የመዳን ቀን ዛሬ ነውና ወደ ጌታ ና/ነይ?

«በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።» (ዮሐ. 3፥36)

ጌታ ኢየሱስ ይመጣል!

«ይህንን የሚመሰክር፦ አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና» /ራእይ 22፥20/።

የመጨረሻው መጨረሻ በዮሐንስ ራእይ 1:3፥ «ዘመኑ ቀርቧልና የሚያነበው የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁ ብፁዓን ናቸው» የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ደወል ከጆሮአችን ላይ ያቃጭላል። ይህ መጽሐፍ በመጨረሻው ዘመን በምልክት የሚፈጸሙትን ጉዳዮች እያነሣ ጠቃሚ ማብራሪያዎችን ያቀርባል። በመሆኑም፥ አጽንኦት ሰጥተው ለሚያነቡት በዘመናችን የሚፈጸሙትን ክስተቶች ሁሉ ለማጤንና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ምን ያህል እንደተቃረበ ለማስተዋል ያስችላል።

ፓስተር በቀለ ላቀው

* * *

በአውሮፓ ኅብረት (EU) ውስጥ የሚሠራ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በሰውነት ውስጥ ለመቅበር ተጠንቶ ያለፈውን ትንሽ መሣሪያ አምጥቶ እንዳሳያቸው አንድ መጋቢ አጫውተውኛል። አከለውም ትንሹ መሣሪያ ምሥጢራዊ ቁጥር እንደተሰጠውና ያም ቁጥር «666» እንደሆነ ገልጸውልኛል።

... በአሁኑ ጊዜ ከገንዘብ ካርድ ሌላ *Smart Card* የተባለ ካርድ ተሠርቷል። ካርዱ በውስጡ የያዘውን የሕክምና መረጃ ሳይቀር ሙሉ ማንነቱንና ሌሎችንም ስለዚያ ሰው ለማወቅ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ የመዘገበ ሲሆን፥ ካርዱ ለርሱ በተዘጋጀ የኮምፕዩተር መሣሪያ ውስጥ ሲከተት ስለ ግለሰቡ ማንኛውንም መረጃ ይሰጣል... በአሁኑ ሰዓት የአውሮፓ ኅብረት ሠራተኞች በሙሉ የዚህ ካርድ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፥ በአሜሪካና በሌሎችም የአውሮፓ አገሮች የሚገኙ ታላላቅ ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች *Smart Card* መጠቀም ሳይጀምሩ እንዳልቀሩ ይገመታል...

(ከመጽሐፉ የውስጥ ገጾች የተጨለፈ)

* * *

ዋጋው፣

አገር ውስጥ 10፡00

ከአገር ውጭ $6:00

በለርቴስቲክ ማ/ድርጅት ታተመ